# የኢትዮጵያ ረሀብና የምዕራብ ጋዜጦች አስተያየት

ቀሪቾ ፈይሣና ጓደኞቹ
ሰሜን አሜሪካ

## መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያለው ሥነጽሑፋዊ ማስረጃ የሚቀርብለት ታላቅ ጥንታዊ ሥልጣኔ ያላት ታሪካዊ አገር ለመሆኗ በርካታ የታሪክ ሊቃውንት የመሰከሩት ጉዳይ ነው። እንዲያውም በአንድ ወቅት በዓለም ከታወቁት ሦስት ወይም አራት ግዛተ አፄ (KINGDOM) ኃያል አገሮች አንዷ እንደነበረች ይተረካል። ይሁንና ኢትዮጵያ በታሪኳ ደግሞ ድርቅ፣ ረሀብና ጦርነት (እንዲሁ ኑ አይከፋ እንጂ) አጥታ አታውቅም። እንደውም እንደአንዳንዶች ተቺዎች አስተያየት የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው ቢባል ከእውነት በብዙ መራቅ አይሆንም። የቱርኮች፣ የግብፆች፣ የፋሽስት ኢጣልያ ወረራዎች፣ የዐድዋ ጦርነት፣ የግራኝ መሀመድ (ጅሐድ) ጦርነት፣ የዘመነ መሣፍንት (እርስ በርስ) ጦርነት፣ወዘ.ተ. እንደምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ። እንዲሁም አያሌ የአውሮፖ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ኢትዮጵያን በሀይማኖት ሰቢያና ቢቻልም ሙሉ በሙሉ አጠቃለው የቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ጥረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ሆኖም የተወሰኑ ክፍሎቿን ቆራርሰው በቁጥጥራቸው ስር አውለዋል። ከታወቁት የአውሮፓ ኮሎኒያሊስት አገሮች አንዷ ጣሊያን በዱቼ ሙሶሊኒ አገዛዝ ሥር በነበረችበት ጊዜ በአብሪት ተወጥራ የኢትዮጵያን ከተሞችና አውራ መንገዶች ይዛ እንደነበር የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ገጠሩንማ፣ ዱሩንማ አባት አርበኞች ይዘውት ስለነበር ጣልያኖች ከከተማና ከአውራ መንገድ ሊወጡ አልቻሉም።

ለመሆኑ ኢትዮጵያን ቢቻል ማንነቷን ለማውደም፣ ባይቻል ግን ቀስ በቀስ አካሏን እየቆራረሱ ለማዳከምና ፍጹም በቁጥጥር ስር ለማዋል ይህ ሁሉ የኮሎኒያሊስቶች የዘመናት ትግል ለምን ተካሄደ?! ኢትዮጵያውያንስ እንደምን በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በሥልጣን ሽሚያ፣ በግዛት ድርሻ ላይ የተመሰረቱ የውስጥ ቅራኔዎቻቸውን ለጊዜው አስዝበው እንደምን እንደአንድ ሰው በመቆም በመጣው የባህር ማዶ ጠላት ላይ ተረባረቡ? ለነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ እንዲሰጡን ሀቀኛ የተሪክ አዋቂዎችን መጋበዝ ግዴታ ቢሆንም ለጊዜው የኢትዮጵያን ታሪክ በአፍሪካና በሌላው ጥቁር ሕዝብ የታሪክ ክልል(context) ውስጥ በማስገባት መመልከቱ የነገሩን ፍንጭ ለማግኘት ያህል ባይጠቅመን

አይቀርም።

ከአፍሪቃ አህጉር በባርነት የተሸጡት ዝርያ ጥቁር-አሜሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንዲሁም ከባርነት ሽያጭ ቢድኑም ከዚያው በሚወዳደር የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ሲማቅቁ የነበሩ አፍሪቃውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ኢትዮጵያንና ሰንደቅ አላማዋን የትግላቸውና የነፃነታቸው አርማ አድርገው ለመመልከታቸው አያሌ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል። ዛሬ ልብ ብለን ብናስተውል በተለይ በጃማይካ ራስተፈሪያን የሚባሉ ማህበረሰቦች የኛን ሰንደቅ ዓላማና አገራችንን ኢትዮጵያን በኩራት ሲታዩበት ነገሩ ለእኔ ኃይለሥላሴ ካላቸው ግላዊ ፍቅር ብቻ የመነጨ ይምሰል እንጂ ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ባደረጉት ትግል ውስጥ የአንድ «ኢትዮጵያ የምትባል ነፃ የጥቁር አገር» መሰው አፍሪቃ በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ስር በወደቀበት ወቅት መኖር ሁኔታ ጋር የተያያዘ ከባድ የነፃነት ፍላጐት ስሜት (emotion) ጋር የተቆራኘ ጉዳይ ነው። አንዳንድ የሰሜን አሜሪካ ጥቁሮችና እስካሁን በነጭ የበላይነት የሚገዙት የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በቤተ ክርስቲያናቸውና በሌሎች መሰብሰቢያ ሥፍራዎቻቸው ሁሉ ከማሳየት አልፈው ቤተክርስቲያኖቻቸውን ሳይቀር « church of Abyssinia» ብለው መሰየማቸው ከጥልቅ የነፃነት ፍላጐት ስሜት የመነጨ ድርጊት መሆኑን ያስገነዝበናል።

እነሆ ዛሬ እንኳ በነፃው ሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ ጥቁሮች ከአራት መቶ ዓመት ባርነት በኃላ መብታቸውን ለማስከበር በሕይወት ብዙ መስዋዕትነት ከከፈሉ በኃላ በወረቀት ላይ ብቻ ሰብአዊ መብታቸው ከተከበረ እነሆ ገና ሃያ ዓመት ሆነው። ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን በዘር ጭቆናውና ከነጭ እኩል መብት ባለማግኘታቸው ለሚያደርጉት ትግል በሚሰበሰቡባቸው የጥቁር ማህበሮች (Negro Community Centers ) የእምዬ ምኒልክን ምሥል «ታላቁ አፍሪካዊ ንጉሥ፤ በወራሪ የአውሮፖ ኮሎኒያሊዝም ላይ የአድዋን ድል የተቀዳጀው የጥቁር ንጉሥ» በለው ጽፈውበት በየስብሰባ አዳራሾቻቸው ያሰያሉ። አንዳንድ የሥውር ቅኝ አገዛዝ (Neo- Colonial) በሽታ የተጠናወታቸው ነጭ ደራሲያንና (በሰሻሊዝም ስም ጭምር እየማሉ) አፍሪካዊነታቸውን የዘነጉ ግለሰቦች ጭምር የአፍሪካዊውን ጀግና እጤ ምኒልክን ለባሪያ ግዢና ለጥሬ ሀብት፣ እንዲሁም ለሸቀጥ መቸርቸሪያነት ቅኝ ግዛት ከተቀዳጁ የአውሮፖ ወራሪዎች እኩል «በወራሪነት» ወንበር ላይ እንድናስቀምጥ ይጋብዙናል። ለነዚህ መልሳችን «አሽፈረን» እናዳምጣችሁም ብቻ ነው። ኧረ ለመሆኑ ነፃነት የጠማቸው ጥቁር ሕዝቦች ለምን ኢትዮጵያን የነፃነታቸው ተስፋ ማድረጊያና አለኝታ አድርገው ለማየት ፈለጉ?! ለዚህ መልሱ አጭር ይመስለናል። ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ጥንታዊያን አባቶቻችን በቋንቋ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ሳይለያዩ ስጊዜው ያላቸውን የውስጥ ቅራኔ ረገብ አድርገው ጠላትን እንደቀትር ንብ ተረባርበው

በመናደፍ በአገራቸው ላይ የነጭ አገዛዝ እንዳይመሰረት በመታገሏቸውና ለነፃነት ያሏቸው ቀናኢነት በሰንደቅ ዓላማቸው ሕብረቀለማት በመላው ጥቁር ሕዝብ ዘንድ እንደ ቀስተ ደመና ኅልቶና ከፍ ብሎ እንዲታይ በማድረጋቸው ነው። ጀግኖች አበቶቻችን ኢትዮጵያውያን በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለሚማቀቁ ወንድሞቻቸው የነፃነት ሰንደቃቸውን ከፍ አድርገው በማውለብለብ በአፍሪካ ምድር የመጀመሪያ ነፃ አገር (ጥንታዊቷን አቢሲኒያ የዛሬዋን ኢትዮጵያን) በዘረኛ የአውሮፖ እብሪት የማትደፈር፣ ብቸኛ ነፃ የጥቁር አገር በመገንበታቸውና አለኝታ በመፍጠራቸው ነው። ይህንን የኢትዮጵያ የነፃነት አለኝታነት ዛሬ የነገይቷን ነፃ ደቡብ አፍሪካ ለመመሥረት የሚታገሉትና የሬዲዮ ፕሮግራም ለሕዝቦቻቸው ከአዲስ አበባ ሬዲዮ ጣቢያ የሚያስተላልፉት የነፃነት ታጋዮች ከማንም የበለጠ ያውቁታል።

ይህ የኢትዮጵያ በለታሪክነትና የሥልጣኔ ሀገርነት የማይዋጥላቸው የነጭ የበላይነት አስፋፊ  የአውሮፖ የፖለቲካ፣ የፍልስፍናና የሥነፍጥረት ሊቃውንት ኢትዮጵያ የምትባል አዋኪ (Problematic) አገር የነሱን የነጭ የበላይነት ንድፈ-ሀሳብ የምታፋልስና ብሎም የምታከሽፍ (ለጥቁር ሕዝብ ጥንታዊ ሥልጣኔ ቀርቋሪነትና ባነቤትነት በጉልህ ማስረጃነት የምታቀርብ) አገር በመሆኗ ስለጥቁር ስልጣኔ-ቢስነት ድምዳሜ በየፋበት ብእራቸው ኢትዮጵያን እንደሚከተለው ይገልጧታል።እንጠቅሰለን፤

> ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ልዩ ክስተት ነች። ኢትዮጵያና ግብጽ ታሪካቸው ሳይቆራረጥ እስክ ጥንቱ ዘመን ድረስ ሊጠቀሱ የሚችሉ ብቸኛ አፍሪካዊ አገሮች ናቸው። ግብጽ በተከታታይ (በአረቦችና በአውሮፖውያኖች) ወራሪዎች ምክንያት ቀስ በቀስ ከራሷ ታሪክ እየራቀች ወደመሄድ ስትቃረብ ኢትዮጵያ ግን ለአጭር ጊዜ በኢጣልያን ከመወረሩዋ በስተቀር ጥንታዊ («ኦርጅናሌ»)መልኳን እንደያዘች ለዘመናት ቆይታለች። በሌላ አነጋገር፣ ኢትዮጵያ ልዮ የሆነ ባህሏን ለዘመናት ጠብቃ ለማቆየት በቅታለች። ይህም ልዮ በሀል ሁለት የተፈጥር ተሰጥኦ ካላቸው (Gifted) ሕዝቦች ተራክቦና ኂላም መዋሃድ የመነጨ ነው። እነዚህ (የዛሬይቱን ኢትዮጵያን የመሰረቱ) ሕዝቦች ኩሾች ወይም ቆዳቸው ጥቁር የሆነ  የነጭ ነገድ ዝርያዎች ምናልባትም የምድሪቱ አብር በቀል (indigenous) ሲሆኑ ሌላው ወገን ደግሞ ሴማውያን ምናልበትም ከአረብ ምድር ፈልሰው የመጡ ሳይሆኑ አይቀርም። (1) (እጽንኦት የነዚህ ፀሐፊዎች ነው)።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የነጭ ዘር የበላይነት ፈላስፎች ነጭ ቀለም ያለበሰ ሕዝብ ( የነጭ ዝርያ ያልሆነ ጥቁር) ሥልጣኔ ሊኖረው እንደማይችል ነው የሚነግሩን። ነጮቹ ፈላስፎች የሚነግሩን ይህንን ብቻ አይደለም። ጥቁር ህዝብ ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከተው አንዳችም ነገር እንደሌለ እንደተፈጠረ ያለ (barabrian ወይም Primitive) ነው ብለው

ሊያሰም ኑን ይጥራ ሉ። በነሱ አስተያየት «ኋላ ቀሩ ጥቁር ሕዝብ» ሥልጡኑ ነጭ የሰጠውን ጥበብና እውቀት እንኳን በአግባቡ ለመጠቀም የአእምሮ ዝግጅት፣ የአስተዳደር መዋቅርና ችሎታ የለውም። እዚህ ላይ ልብ ብለን ማስተዋል ያለብን ፍጹም ጥቁር አፍሪካዊት የሆነችውን አገር (ኢትዮጵያ) የስልጣኔ ባለቤትነቷን የተጎናፀፈችው በጥቁር ሕዝቧ ጥበበኛነት ምክንያት ሳይሆን ሕዝቧ በጥቁር ቀዳቸው የተለጉመ የነጭነት ባህርይ «በመታደላቸው» ሆኖ መቅረቡን ነው። ይህ አሳፋሪ የሆነ የአውሮፖ «ሳይንሳዊ» ትንተና ኢትዮጵያን ከጥቁርነት ወደ ነጭነት መድበ የጥቁር ህዝቦችን የስልጣኔ ቅርስ ባለቤትነት ለመንጠቅ የተዘጋጀ «እውቀት» ነው። የግብጽንና የኢትዮጵያን (የአፍሪካ) ሥልጣኔ መስራችነት ነጭ ቀለም ቀብቶ ጥቁር ሕዝብ በታሪክ ውስጥ የስልጣኔ መስራችነት የለውም ብሎ የሚደነግገው አብሪተኛ አስተሳሰብ ከተራ የሕፃናት እንቆቅልሽ ጨዋታ ምንም ያልተሻለ ቢሆንም በአውሮፖውያን «ሊቃውንት» ተደርቧልና ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካን በሚያህል የእውቀት ማህደር ውስጥ ሥፍራ መሰጠቱ ትንሽም ቢሆን ለታዛቢ ሳያስገርም አይቀርም። በዚሁ አንፃር ግን የምዕራባውያን ፍልስፍናና «ዘመናዊ ትምህርት»(modern education) ስናገበሰብስ ያደግን አበሾችና ሌሎች አፍሪካውያን ምንኛ በእውቀት ስም ሐሰት በንቀስም እንደነበረ ይህ ምሳሌ አነስተኛ መረጃ መሆ ኑን እንረዳለን።

ዛሬ የአፍሪካ ሕዝቦች አስተዳደር ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋትና መደበር አመቺ ሆኖ አለመገኘት ዓይነተኛው ምክንያት ዘረኛ ፈላስፎች እንደሚተርኩት የጥቁር ሕዝብ ንጥረ-አእምሮ (IQ ) ዝቅ በማለቱ ሳይሆን የአውሮፖ ኮሎኒያሊስቶች የአፍሪቃንና የሌሳውንም ሦስተኛ ዓለም ክፍሎች በዘረኛ ርእዮተዓለም የተመሠረተ ቅኝ ግዛታቸውን መስርተው በተለይ በእንዳንድ የአፍሪካ ክፍሎች (ለምሳሌ እንደሞዛምቢክና አንጎላ እንዲሁም ደቡብ አፍሪካ) እስከ 500 ዓመት ድረስ ሲቆዩ ሕዝቡን"አደንቁረህ ግዛ"በተባለ ፈሊጣቸው ትምህርት እንዳያገኝ በማድረጋቸው ነው። ለምሳሌም ያህል በጦፈ የዘረኝነት ፍልስፍናቸው በጣም የታወቁት የቤልጂግ ኮሎኒያሊስቶች ለምን በቅኝ አገዛዛቸው ሥር ለሚገኘው የአፍሪካ (ኮንጎ) ሕዝብ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት እድል እንደሚነፍጉት ሲገልጡ እንዲህ ብለዋል።«የከፍተኛ ትምህርት የቀሰመ አፍሪካዊ የራሱን ወገኖች (አፍሪካውያንን) ሊያገለግል አይችልም።» ስለሆነም፣ እንደቤልጂጎቹ አባባል «አፍሪካውያንን ማሰልጠን ቀስ በቀስ» ነው። የሁለተኛ ደረጃ ወይንም የከፍተኛ ትምህርት ለአፍሪካዊው (ጥቁር ፍጡር ) ማቅረብ ማለት "ገንፎ ሊውጥ የሚገባውን (ጥርስ ያላበቀለ) ህፃን ልጂ ሥጋ አኝክ ብሎ እንደመጋበዝ ይሆናል«(2)እነሆ በዚህ ዓይነቱ ስንኩል እምነት ላይ በተመሠረተ አገዛዝ ሥር የቆየችው የቀድሞዋ" ቤልጂጋዊት "ኮንጎ ነፃነቷን በተጎናፀፈችበት ዓመት ፲፫ ሚሊዮን በመሃይምነት የሚማቅቅ ሕዝብና

በራሳቸው የግል ጥረት የተማሩ ፲፯ የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን ብቻ ነበሩዋት። አፍሪካ ለአውሮፖ በሰረከበችው ወርቅ፣ እንቁ፣ እርከሽ ጉልበትና ጥሬ ሀብት ምትክ ያገኘችው ቅርስ ማሃይምነትንና ኃላቀርነትን እንዲሁም ድህነትን ነበር።

አገራችን ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አህጉር ጨርሶ ከቅኝ አገዛዝ መላቀቅ አስተዋጽኦ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለመላው የአፍሪካ ጥቁር ሕዝብ የሥልጣኔ ባለቤትነት ቀዋሚ ሐውልት ሆና መገኘቷም ጭምር የሚያስጠላቸውና የሚያስደነግጣቸው ዘረኛ የአውሮፖ ፈላስፋዎች ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ መንግሥት በአውሮፖ አቆጣጠር በ1974 ዓ.ም «የኢትዮጵያ መንግሥታዊ መመሪያ ሶሺሊዝም ነው። እኛም መሪዎቿ ኮሚዩኒስቶች ነን» የሚል መፈክር አንግቦ ብቅ ሲል የጥላቻቸው ንረት የሰማዩን ጣሪያ ዘንጥሎ ሊወጣ መከጀሉን ላለፉት ፲፫ ዓመታት አፈ ቀላጤዎቻቸው በልዩ ልዩ ዜና ማሰራጫዎች (ጋዜጦች፣መጽሔቶች፣ መጽሐፎች፣ ሬዲዮዎች፣ ቴሌቪዥኖች) አማካኝነት ከሚሰነዝሩት ጨዋነት የጎደለው ተራ አሽከለሌና ዱልዱም ትችቶች መገንዘብ ይቻላል።

ኢትዮጵያ ዛሬ ለደረሰችበት ችግር ከበቂት ዋነኛ ምክኒያቶች አንዱ የቀድሞ መሳፍንትና መኳንንት፣ እንዲሁም ዛሬ በስልጣን ላይ ያለውና በውጭ መልኩ ሶሻሊስት በአሠራሩና በባህርዩ ግን ፍጹም ፊውዳላዊነት የሚያጠቃው የፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ ጭምር ቢሆንም የኢትዮጵያን ማንነት (identity) ለመደምሰስ ከውጭ የታገሉ በርካታ ኃይሎችም ዓይነተኛ ሚና እንዳላቸው መገንዘብ የሀቀኛ ኢትዮጵያውያን ተገቢ ድርሻ ይመስለናል።

የኢትዮጵያ ነገሥታት ክርስትናን ከተቀበሉበት ዘመን ጀምሮ የእስልምና ሃይማኖት በሳኡዲ አረቢያ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ሙሉ ለሙሉ ሰላም አግኝታለች ብሎ መናገር ባይቻልም እስልምናን ማስፋፋት ተግባራቸው አድርገው በተቀበሉ ዐረብ ጎረቤቶቿ ዓይን እስከአሁን ድረስ በጎሪጥ መታየቷ ደግሞ በገሀድ የሚታይ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያን አዘውትረው በሚገላምጡ እስላማውያን ዐረቦች አስተያየት የኢትዮጵያ አብዮት በ1974 ዓ/ም እስከፈነዳበት ጊዜ ድረስ አገሪቱ « በእስልምና ባህር ውስጥ የምትገኝ የክርስቲያን ደሴት» ሆና ትቆጠር ነበር። ከለውጡ ወዲህ ደግሞ ከግልምጫም አልፎ አልፎ አልፎ በአገሪቱ ላይ በቀይ ባህር አሸጋግረው ቅዝምዝማቸውን እስከመወርወር ደርሰዋል። በዐረብ እስላማውያን ዘንድ አሁን ኢትዮጵያ « በወግ አጥባቂ (ኮንሰርቫቲቭ) ባህር ውስጥ የምትገኝ የኮሚዩኒዝም ደሴት» ነች። አሳዛኝ ነገር ግን ቀድሞም ሆነ አሁን ኢትዮጵያውያን እስላሞች በሀገራቸው መኩራት ብቻ ሳይሆን

በኢትዮጵያ ላይ የተሰነዘረውን ወረራ ሁሉ በመመከት የአገራቸውን ክብር ከመጠበቅ አልፈው ጎሰና ሃይማኖትን ተንተርሰ የሚመጣውን ጥቃት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጎን በቆራጥነት በመሰለፍ ማክሸፋቸውን ሁሉ እነዚህ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችና ፀሐፊዎቻቸው ለመገንዘብና ለማመን አይፈልጉም። በበኩላችን የሀገር ፍቅር ያላቸው ታሪክ አዋቂዎች ይህንን የታሪክ ሀቅና እንዲሁም እኒህ የጎረቤት ጠላቶች ኢትዮጵያውያን በውስጥ ግጭት የተዳከሙበትን ወቅት ጠብቀው እንደአደፈጠ ተኩላ አገራችንን መተናኮላቸውን ከግብፆችና ከቱርኮች ወረራ ጀምሮ ያለውን ጊዜ እንደሚያተኩሩበት ያለንን ተስፋ እንገልጻለን።

በመሠረቱ የዚህ ጽሑፍ መነሻ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪካዊነት በመዘብዘብ አንባቢያንን ለማታከት ሳይሆን ዛሬ የኢትዮጵያን ማንነት ለማጥፋት ርብርብሽ የሚያደርጉ ኃይሎችና ድምፃቸውን ጎላ አድርገው የኢትዮጵያን ውድቀት የሚዘምሩ ጋዜጠኞች ለምንና በምን ሁኔታ ከቀድሞ ጀምሮ ኢትዮጵያን የሚፃረሩበትን የታሪክ ጭብንጭል ለማሳየት ስንል ነው። ይህ ጽሑፋችን በዚህ ታሪካዊ መሠረት ላይ ካልተዋቀረ ደግሞ የትኛው ጋዜጣ ለምን በሚፃፍበት ዘይቤ እንደሚፃፍና ዛሬ ማንም ሊንቃት የቃጣውን ለኛ ግን ክቡር የሆነችውን አገራችንን« ጠብ ያለሽ በዳቦ» በሚል ፈሊጥ እንደሚተነኩሷት የቀድሞውን ታሪክ ከአሁኑ አፃፃፋቸው ጋር ለማዛመድ አይቻልም። የምዕራቡ ጋዜጣ አዘጋጆቻችና ጽሑፍ የሚያበረክቱ ቃል አቀባዮችም (ሪፖርተሮች) ከአባቶቻቸው ከሎኒያሊስቶች የተረከቡትን ኢትዮጵያን የማጥላላት ዘመቻ ዛሬ ኢትዮጵያ በደረሰባት አሳዛኝ ማህበራዊ ቀውስ (ረሀብ፣ ጦርነት፣ወዘተ)ሳቢያ በማስታከክ ነባር ቂማቸውንና አዲስ ርእዮተ ዓለማዊ ጥላቻቸውን ለመወጣት በጽሑፎቻቸው ሁሉ መከርከም ብቻ ሳይሆን ከዓለም ካርታ ላይ ሊፍቋት እንደቃጡ ለማስተዋል ደግሞ የዛሬውን ከጥንቱ ሁኔታ ጋር አጣምሮ የሚያሳየንን የታሪክ መነጽር ለማጥለቅ ስንችል ብቻ ነው።

## ኢትዮጵያ በምዕራባውያን ጋዜጠኞች ዓይን ስትታይ

ለዚህ ሐተታችን እንዲያገለግሉን ብለን ያገለበጥናቸው የእንግሊዝ፣ የአሜሪካ፣ የካናዳ ጋዜጣዎች የተሰበሰቡት በነሲብ (randomly) ነው። የሰበሰብናቸው ጋዜጣዎች በኢትዮጵያ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር የ1984 ዓም ረሀብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይህ ጽሑፍ እስከተዘጋጀበት ቀን ድረስ ነው።

በሬዲዮዎች፣ በቴሌቪዥኖች፣ በሴሚናር አዳራሾች ስለኢትዮጵያ የቀረቡ ዝግጅቶችንና እንዲሁም በሌሎች አገሮችና አህጉራት በእንግሊዝኛና በሌሎች ቋንቋዎች የተፃፉ ጋዜጦችን አልተመለከትንም። እነዚህን በሙሉ

ለወደፊት ተመራማሪዎችና ለእናት ኢትዮጵያችን ተቆርቋሪ ለሆኑ ሐበሾች ሁሉ ጽሑፎቹን እንዲሰበስቧቸው እንዲያጠኑዋቸውና፣ ከቶም ከተቻላቸው፣ በሰምና ወርቅ አማካኝነት የጥናቶቻቸውን ውጤቶች እንዲያከፍሉን እንጋብዛቸዋለን። በኛ በኩል ግን እስካሁን ከሰበሰብናቸው ኢትዮጵያና አፍሪቃ ነክ የጋዜጣ አርእስት ውስጥ አንድ እንኳ ስለአፍሪቃም ሆነ ስለኢትዮጵያ ቀና (positive) የሆነ አስተያየት ይዞ የቀረበ አላጋጠመንም።

ወደ ተነሳንበት ፍሬ ነገር ትንታኔ ከመግባታችን በፊት ግን ምንጊዜም ቢሆን ሚዛናዊ (objective) ነን ብለው የሚለፍፉ የምዕራብ ጋዜጣዎች አዘጋጆች በአጠቃላይ አሠራራቸው የካፒታሊስት ሥርዓትን ዓለማቀፋዊ የበላይነትና ገናናነት ለመቀዳጀት የሚጠቀሙባቸው መሠሪ (subtle) ዜዴዎች ጥቂቶችን እናስተውላለን። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለማስታወስ የምንፈልገው ጉዳይ የሶሻሊስት አገሮች ጋዜጣዎችም ቢሆኑ የዚያን ሥርዓት የበላይነትና ሥልጣን ለይ ያሉትን ፓርቲዎች ፍጹም ወሳኝነት የሚያስጠብቁ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ መሆናቸውን ነው። እዚህ ላይ በሶሻሊስቶችና በካፒታሊስቶቹ ጋዜጦች መካከል አንድ ሙያ ጠቀስ የሆነ መሠረታዊ ልዩነት መኖሩንም ልንጠቅም ይገባል። ይኸውም ሶሻሊስት ጋዜጦች ግልጽ በሆነ መንገድ የሥርዓቱ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች መሆናቸውን ሲያስታውቁ፣ የካፒታሊስት ጋዜጦች ግን እኛ ለሁሉም የማናደላ «ሚዛናዊ» ፍጡር ነን ብለው ድፍን የምዕራቡን አንባቢ ያደናግራሉ። በመሰረቱ እነሱም ቢሆኑ ለሥርዓቱ የቆሙ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች ለመሆናቸው ዋነኛ ምስክሩ የየእለቱ ድርጊታቸው ነው። ይህንን ድርጊታቸውን የሚሸፍኑበት ዘዴ ግን በግልጽ ለማን ወገን እንደቆሙ አለመናገራቸው ነው። በእርግጥ ለማን እንደቆሙ ግን የነቃው አንባቢና እራሳቸው አዘጋጆቹና ከበርቴ ባለቤቶቻቸው በማያሻማ ሁኔታ ያውቁታል። ምዕራባዊ ጋዜጦች የዋሁን አንባቢ እኛ ዓላማችን ዲሞክራሲን ለማስከበርና ሕዝቡም ለማሳወቅ (to inform) ነው ብለው ያሳምኑታል። የሚያስከብሩት ዲሞክራሲ ግን የማን ዲሞክራሲ እንደሆነ እናውቀዋለን፣ እነሱም ያውቁታል።

ሊብራል (ለዘብተኛ) የሆኑ የምዕራብ ዲሞክራሲያዊ መንግሥታት በመወያየትና በማሳመን (Through consensus) እንጂ በማስገደድና በማስፈራራት (Through coersion) አገር አያስተዳድሩም። ይህ የቆየ የፓለቲካ ባህላቸው ለመሆኑ አይከድም። ይሁም እንጂ በተለይ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣና ሌሎችም የዜና ማሰራጫ ዘዴዎች (mass media) ሕዝቡን ከማሳወቅ ባሻገር በሕዝቡ ዘንድ የገኙ መደቦች የፖለቲካ ፍላጎት እንዲሰርጽ እጅግ በረቀቀ ዘዴ እንደሚጠቀሙ ደግሞ አሌ ሊባል የማይገባ እውነት መሆኑን አያሌ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ጥበብ አዋቂዎች ይናገራሉ።(3) ጊትሊን በተባሉት በዚህ

መስከ እዋቂ አገላለጥ የምዕራባውያን «mass media» እምብርት ተግባራቸው ያሉትን ሥርዓቶች እንዳሉ የሚቀጥሉ ነገሮች ሆነው በሕዝብ ልቡና እንዲቀረጹ የሚረዱ እጅግ ኃይለኛ መሣሪያዎች ናቸው።

እዚህ ላይ አንድ አጥብቀን ልናጤነው የሚገባን ጥያቄ በአንድ ጋዜጣ ላይ አንድ ድርጊት /ክስተት ዜና ሆኖ እንዲቀርብ በበላይነት ማን ይወስናል የሚለው ነው። የትኛው የጋዜጣ ገጽ ላይ በየትኛው አምድ ውስጥ ከምን ዓይነት ዜና ጎን ይቀመጣል?። የዜናው ርእስ ፊደሎችስ ምን ያህል ጎልተው ይፃፋሉ? ለዜናው አሰማኝ ድጋፍ የሚሰጡ ሥዕሎች ምን ዓይነትና መጠናቸውስ ምን ያህል ነው? እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ጥያቄዎች ሁሉ የጋዜጦች ባለቤቶችና አዘጋጅዎቻቸው ከፍተኛ የህትመት ፖሊሲ ውሰኔ የሚሰጡባቸው ናቸው። በሌላ አነጋገር የትኛውም ዜናና ምሥል በዘፈቀደ እንደተገኘ የሚፃፍና በጋዜጣው አከል ውስጥ በአጋጣሚ የሚቀመጥ አይደለም። አልፎ አልፎ የምዕራብ ጋዜጣዎችን አቀራረብ ለምሳሌ ያህል ልብ ብለን ብናስተውል፤ የፍልስጥኤሞች ንቅናቄ መሪ የሆኑት አቶ ያሲር አረፋትና የሊቢያው መሪ ኮሎኔል ጋዳፊ ምሥሎች አስቀያሚ ሆነው እንዲቀርቡ በጥንቃቄ ይዘጋጃሉ። ይህ ብቻ በቂ አይደለም። ከምሥላቸውም ስር የሚፃፈው ማብራሪያ እኒያን ግለሰቦችና የሚመሩትን ድርጅት ወይም አገር የተራ ወንጀለኞችና ሽብር ፈጣሪዎች ማህበር አድርጎ ለማቅረብ ሆን ተብሎ ቃላቱ ተመርጠውና ተመጥነው ይፃፋሉ። ይህ ታዲያ ባጋጣሚ የተደረገ የሚመስለን ብዙዎች ብንሆንም ድርጊቱ ሆን ተብሎ ለመደረጉ የስነ ጽሑፍና የጋዜጠኝነት ሙያ የቀሰሙ ሁሉ አበክረው ይረዱታል።ስለአህጉራችን (አፍሪቃ) እና ስለሌሎች የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች የሚወጡ ዜናዎች ሁሉ አጉልተው የሚያሳዩት የኢኮኖሚ ውድቀት፣ የሽብር መስፋፋት፣ የረሀብ መስፈንን ነው። እኒህም በሚገባ ተመርጠው ነው እንጂ ከአፍሪቃም ሆነ ከሌላ የሦስተኛው ዓለም ከነዚህ የተሻሉ የኢኮኖሚ ልማትና የማህበራዊ እድገት ዜናዎች ሳይገኙ ቀርተው አይደለም። በምዕራቡ ዓለም የዚህ ዓይነቱ የሦስተኛው ዓለም የውድቀት ዜና መቅረብ ለገዥው መደብ በሰላም ተደላድሎ መኖር ዓይነተኛ አስተዋጽኦ አለው። በአፍሪቃ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቢኖሩም በሰፊው የሚፃፍባቸው ምክንያት ለአፍሪቃ ችግር መፍትሔ በመሻት ላይ ያተኮረ ቀና ስሜት ሳይሆን የውድቀቱ ዜና የምዕራቡን ዓለም ሠራተኛ ሕዝብ (working class) ባለው ረክቶ «ተመስገን አምላኬ የባሰ እንደ አፍሪቃ ያለም አለና» ብሎ ብዙ መብት ከቀጣሪዎች ዲታዎች እንዳይጠይቅ ለማድረግ የታቀደ ጭምር ነው። በተጨማሪም «ለኢትዮጵያ የ40 ሚሊዮን ብር ስንዴ በ2 ሳምንት ውስጥ ላክን» የሚለው ዓይነት የአሜሪካ ዜና የምዕራቡ ሕዝብ ተራ ብሄራዊ ኩራትን (እኛ እብሪተኛነት የምንለውን) እንዲጎናጸፍ ለማድረግ የታሰበ ይመስላል። ሌላው በቅርብ ልናጤነው የሚገባ ጉዳይ የምዕራቡ የጋዜጠኝነት

ሥርዓተ ትምህርትና አወቃቀር ነው። የሙያ ትምህርት አሰጣጥም ቢሆን የሚያተኩረው ዜናዎቹ ድርጊቶችንና ክስተቶችን እንዳሉ ፍንትው አድርጎ በሚቀርብበት ሁኔታ ላይ ሳይሆን በመሠረ ትንታኔ (subtle analysis) በጉዳዮቹ ላይ ብይን (judgement) በማሰለፍ የገኙውን መደብ ፍላጎት የሚያንጸባርቁበት ሁኔታ ላይ ነው። የነዚህ ዓይነት ጋዜጠኞች የሙያ ጥበብ (profession) አልፋና ኦሜጋ በጭሩ ይህንን ይመስለል።(4) ዛሬ በእንግሊዝ አገር በወ/ሮ ማርጋሬት ታቸር፣ በአሜሪካ በአቶ ሮናልድ ሬገን፣ በካናዳ በአቶ ብራያን ምሮኒ መሪነት የሚገዙት ወግ አጥባቂ (ኮንሰርቭቲቭ) መንግሥታት የየራሳቸው የፖለቲካ ልሳን ቢኖራቸውም «ለሕዝብ ከሚያገለግሉት» ጋዜጣዎች መካከል የመንግሥታቱን (የገዢውን ከበርቴ መደብ) ፍላጎት የሚያንጸባርቁ ያስፈልጉዋቸዋል። እነዚህ ዓይነት ጋዜጣዎች ለከበርቴው መደብ የበላይ ገዥነት የቆሙና በቡርዥዋዎች ባለቤትነት ቁጥጥር ስር ያሉ «ነፃ ነን» በይ የባለቤቶቻቸውንና የበላይ ጠባቂዎቻቸውን (መንግሥታት) ፍላጎትና ጥቅም ማርካት ዕለታዊ ተግባራቸው ነው። የፖለቲካና የኢኮኖሚ እንዲሁም የማህበራዊ ኑሮ «እከክ» ሲያጋጥም ጋዜጣው የመንግሥቱን፣ መንግሥቱም የጋዜጣውን «ጀርባ ማከክ ቸው» አይቀርም። ይህ ማለት ግን ጋዜጣዎቹ በሥልጣን ላይ ያሉትን መንግሥታት አይነቅፉም ማለት አይደለም። አሰምረው ይነቅፏቸዋል። ይሁንና ነቀፋቸው ግን እስከዚህ የሥልጣናቸው መሠረት እስኪናጋ ድረስ የጠነከረ አይደለም። መንግሥታቱም ይህንን ውስጣዊ መተሳሰብ ስለሚያም ኑበት ጋዜጦችንና አዘጋጅዎቻቸውን አይተናኮሉዋቸውም። በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ከዳበሩት ሰባት የምዕራብ አገሮች የእነዚህ የሦሥቱን ስሜቶች ከሚያንፀባርቁት በርካታ ጋዜጣዎች ውስጥ ሦስቱን ዋና ዋና «ነፃ» ጋዜጣዎች እንጠቅሳለን።

እነዚህም አንደኛ The New York Times (5) በአሜሪካ፤ ሁለተኛ The London Times በእንግሊዝ፤ ሦስተኛ The Globe and Mail በካናዳ ይገኛሉ።

በአገራችን በኢትዮጵያ ዛሬ የፕሬዚደንትነት ሥልጣን የጨበጡት የቀድሞው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበርና የአሁኑ «የሠርቶ አደሮች ፓርቲ» መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም ሶቪየት አቀፍ አቋም በመያዛቸው በኢትዮጵያ ጥቅምና ወታደራዊ ክልል (base) ያጡ የምዕራብ መንግሥታትና የወግ አጥባቂ፣ እንዲሁም የሊብራል ጋዜጦች የነቀፉ ብቻ ሳይሆን የዘለፋ ውርጅብኝ ጭምር ተያያዙዋቸው። እጅግ አስገራሚ የሆነው ግን «ሶሻሊስት ነን» የሚሉት አፈሙሊ የግራ ክንፍ ጋዜጦች ሁሉ ሳይቀሩ ወንጭፋቸውን ወደኢትዮጵያ መሰንዘራቸው ነው። እንደኢትዮጵያ ያሉ የአፍሪቃ አገሮች ሶቪየታዊውም ሆነ አሜሪካዊ ድጋፍ ሲያገኙ የሚችሉት የእነዚህ ዓይነት አገሮችን የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ እንዲሁም የዲፕሎማቲክ ጥቅም እስከሰጠበቁ ድረስ ብቻ ነው። ለዚህም ነው አፍሪቃውያን የፈለገው የውጭ ድጋፍ በወታደራዊም ሆነ በፖለቲካ አስታክ

ሲመጣ በጥርጣሬ መቀበል ያለባቸውና በተለይ እርዳታው የወንድማማቾችን መጫረስ የሚያስከትል ከሆነ እርዳታውን «አሽፈረን እንቀበልም» ማለት ያለባቸው። ለሰላም እንጅ ለጦርነት የሚበጅ እርዳታ ለማንም አይበጅምና!

ከላይ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው አንዳንድ የምዕራብ ዓለም የግራ ክንፍ ጋዜጣና መጽሔት አዘጋጆች ሳይቀሩ ዛሬ ኢትዮጵያ በየአግጣጫው ጣዕረ-ሞት በሚተናነቃት ወቅት በሰላም ምላሳቸው «እንደወደቀ ግንድ» የሚረባረቡበት ምክንያት በእኛ የግል አስተያየት የኢትዮጵያ ወታደራዊ ደርግ የፖለቲካ አመራሩን ሶቪየቶቹን ገለል አድርጎ ከነሱ በለመቀበሉ ይመስለል። እነኢህ ጋዜጠኞች «በደከማዋ» ኢትዮጵያ ላይ የሚደረድሩት የነቀፋ ውርጅብኝ የሚሰነዘረው ረሀብንና አስፈላጊ ያልሆነው የሰሜን ኢትዮጵያ የወንድማማቾችን መጫረስ በማስታከክ ቢሆንም የጽሑፋቸው ዋነኛ ዓላማ የተደበቀ የፖለቲካ ቂማቸውን ለመወጣት የታቀደ ይመስለናል። «ጅብን ሲወጉ በአህያ ተከልሎ ነው» ይበል የለ! ይህ ግላዊ ግምታችን እንጅ ለጊዜው ተጨበጭ መረጃ የለንም። ፈልገንም አላገኘንም።

እዚህ ላይ ግን አንባብያን ልብ ብለን ማስተዋል ያለብን ጉዳይ የዚህ ሁሉ የቀኝ፣ የመሐል-ሠፋሪና የግራ ወገን ጋዜጣ ሁሉ ዒላማ ያቺው «ደከማዋ»፣ «ኋላቀሩዋ»፣ «ወንጀለኛዋ» -«ሶሻሊስታዊዋና» ሲያሻቸውም «ኮሚዩኒስታዊዋ» የሚሏት ኢትዮጵያ ናት። የወለደች እናት የፈለገውን ቀለም የያዘ ቀሚስ ብታጠልቅ፣ ያሻትን እንጀራ አበት በአባወራነት ብትይዝ፣ እናት ነችና ልጆቿ እንደማይጠሏት ሁሉ ከእናት አገራችን ከርሰ ምድር የፈለቀ ምርጫችን ጠልቀን የጠጣንና በእፈሩዋ ላይ የበቀለውን ጥሬ የቃምን ልጆቿ ሁሉ አገራችንን «የራሷ ጉዳይ» ብለን ልንተዋት አንችልም!! የምዕራብ ጋዜጣዎችና ጅምላ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው ኃይሎች ሁሉ ግን ፍላጎታቸው አገራችንን እስከወዲያኛው ክደን እንድንተውና እኛም በየስደት ባለንበት ሁሉ እንደጠላት የጎሪጥ እየተያየን እንድንተላለፍ ነው። ዛሬ ግን ይህንን ደባ ማክሸፍ የእውነተኛ ዘረ-ሐበሻና ኢትዮጵያዊ ሁሉ ግዴታው ነው። ሌላው ቀርቶ ሰላምታችን በ«ሰላም» ይጀምራል። በመላው ዓለም ላይና ዛሬ ደግሞ በመላው አፍሪቃ የአፍሪቃንም ቀንድ ጨምሮ ሽው በማለት ላይ የሚገኘው ይኸው መልካሙ ቃል «ሰላም» በኢትዮጵያም ውስጥ በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲነፍስ ብዙዎቻችን እንደምንሽ ጥርጥር የለውም። ታዲያ ኢትዮጵያውያን ብንተዋወቅም ባንተዋወቅም ራሳችንን ዝቅ አድርገን «ሰላም»ታ ተለዋውጠን መተላለፋ በሀገራችን እንዲሰፍን ለምንመኘው ሰላም መምጣት አንድ ጠቃሚ እርምጃ ይመስለናል።

ዛሬ በስደትና በሥራ፣ በጉብኝትና በትምህርት ሳቢያ በምዕራብ አውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ትላልቅ ከተሞች እንደጨው ዘር ተበትነን

የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የምዕራብ ዜና ማሠራጫወች (ጋዜጣዎች፣ ሬድዮች፣ ቴሌቪዥኖች ወ.ዘ.ተ.) በደረሱብን እኛነታችንን በሚገዘግዝ ሚዘናዊ ያልሆነ ነቀፋ-ኢትዮጵያ ምክንያት እንገታችንን ደፍተን፣ ሐዘንና ንዴታችንን ውጠን እንድንኖር ለመደረጉ የየእለት ሕይወታችን ቋሚ ምስክር ነውና የሰቀ ተጨባጭ ማስረጃ እንድናቀርብበት የሚጠየቅበት ጉዳይ አይመስለንም። በምዕራቡ ዓለም የዜና ማሠራጫዎች አቀራረብ ኢትዮጵያ «ኮሚዩኒስት»፣ «ምስኪን»፣ «ድሃ»፣ «ለማኝ»፣ «በምጽዋት የተሰጠን እህል እንኳ በአግባቡ ለማዳረስ የአስተዳደር ችሎታ የሌላት» እጅግ ኋላ ቀር አገር ናት። የጋዜጦኞቹ አቀራረብና ቋንቋ ለሰሳሰና ገራም መስሎ ቢታይም ውጤታቸው በአንድነት ሲደመር ስለኢትዮጵያውያንና ስለመሳው ጥቁር ዘር የሚሰጡት ሥዕል እጅግ ለጤነኛ አእምሮ የሚቀፉና አበሻዊ ኩራትን ብቻ ሳይሆን ሰብአዊነትን የሚያደሽቅ ምዕራባዊ ድምጽ-የለሽ ርእዮተዓለማዊ መሣሪያዎች ናቸው።

ዛሬ ስለኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪካዊነትና ስለሕዝቧም ትክክለኛ ማንነት ለማሳወቅ የሚከጅል ሁሉ ኢትዮጵያን በማናናቅና በማጥላላት ብቻ ካልተከረ በስተቀር ዝግጅቱን የሚያሰማበትና ጽሑፉን የሚያቀርብበት መድረክ የለውም። ዛሬ በአንዳንድ የምዕራብ አካዳሚክ ተቋሞች እንኳን የኢትዮጵያን ማንነት እንዳልነበረ አድርጎ ማቅረብ የጊዜው አካዳሚክ ፊሊጥ (Fashion) እንዲሆን ለማድረግ የሚጥሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ቁጥር ቀላል አይደለም። የገንዘብና የሞራል ድጋፍ የሚለግሷቸውም ምዕራባዊ የፖለቲካ ቡድኖች ግራ ቀኝ ሳይባል በርካታዎች ናቸው። የዚህ ሳይኮሎጂካዊ ድሽቀት ውጤቱ አበሻው እርስ በእርሱ እንኳን ለመገናኘት እንዳይችል የማንኙነቱ ማያያዣ ሲሚንቶ የሆነው ኢትዮጵያዊ ኩራቱ በብርቱ ስለተመታ የራሱን ወገን እስከመጥላት ደርሶ «የሐበሻ ዓይን አታሳዩኝ» እስከሚባልበት ደረጃ አድርሶታል። ቢያንስ እኛ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢዎች በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ እንዲሁም በሰሜን አሜሪካ ያገኘናቸውን አበሾች ስናናግር የብዙዎቹ አስተያየት «የአገርን ነገር እንደበርኔጣ አውልቆ ማኖር ነው» የሚል አሳዛኝና ተስፋ አስቆራጭ ስሜት ነው ያጋጠመን። ይህ ማለት ግን ይህ አስተያየት ውሎ አድሮ አይለወጥም ወይም የሁሉም አበሻ አስተያየት ይኸው ብቻ ነው ማለት አይደለም። እዚህ ላይ እኛ ለማሳየት የመንሞከረው የዜና ማሠራጫዎች በምዕራብ ዓለም በተሰደድን አንዳንድ አበሾች ላይ ባደረሱት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ እንዴት ድል ሊያደርጉና ሊማርኩን እንደቻሉ ነው። ለምሳሌ ያህል በያለንበት ተሰባስበን እንኳን ኢትዮጵያ ዛሬ የሚያንዣብብባትን የሞት ጥላ ለመግፈፍ ቀርቶ በየምንኖርበት የአውሮፓና የአሜሪካ ከተሞች በማህበር ተደራጅተን እለት በዕለት የሚደርስብንን የነጭ ዘረኝነት እንደሌሎች ጥቁር ወንሞቻችንና የሦስተኛው ዓለም ሰዎች ሁሉ ለመቋቋም የሚረዳን የጋራ መድረክ መፍጠር አልቻልንም። ባህላዊና

ታሪካዊ ኩራታችንን ለመጠበቅ እንኳ እንዳንችል የስሜት እግረሙቅ ገብቶብን ከመሰብሰብ ይልቅ መበተንን የመረጥን ይመስላል። ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው የኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ በተነቀፈ ቁጥር እኛነታችን (ኢትዮጵያዊነታችን) ለከስ የቀረበ መስሎን የምንሸማቀቀው ቁጥር ቀላል አይደለም!! በእኛነታችን እስክናፍር ድረስ ለሞራል ውድቀት ያበቁን የምዕራብ ጋዜጣዎች በእኛ አስተያየት ለሕዝብ ፍርድ መቅረብ ያለባቸው ርህራሄ ቢስ ወንጀለኞች ናቸው።

የዚህ ትችታችን ዋነኛ ዓለማ በእኛነታችን ሙሉ እምነት እድርብን ስመጥር የሆኑ እናት አባቶቻችንና አያቶቻችን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪቃና ለጥቁር ሕዝብ ሁሉ መኩሪያና መመኪያ የሆኑበትን ታሪክ ካወቅን ላላወቀው ነጭ እንድናካፍልና ካላወቅንም ከሚያውቁና ከመጽሐፍት በመማር የሀገራችንን አኩሪ ባህልና ቅርስ እንድናሰውቅ ለማበረታታት ጭምር ነው። የኮሎኔል መንግሥቱን መንግሥት በወንጀለኛነት በመጥቀስ የእኛን ማንነት እንድናፍርበት የሚፈልጉትን ወገኖችና ጋዜጦኞች ሁሉ እኛም ያንን አገዛዝ ለለመቀበል የምንወዳትን አገራችንን መልቀቃችንን በመጠቆም ጋዜጠኞቹ እንኳን በወሬ በጦር ሜዳም ቢሆን ሄደው ሰይፍ ለመማዘዝ ፍጹም አቅሙና ችሎታው ስላላቸው የኛን አእምሮና ማንነት የጦር ሜዳቸው እንዲያደረጉ እንደማንፈቅድላቸው መግለጡ ጠቃሚ ይመስለናል። ኢትዮጵያዊነታችንን ግን እንደሠረቀ ሰው ልንሸማቀቅበት የሚገባ ጉዳይ አይደለም። እዚህ እንኳን ያለነው አበሾች እንዳንተባበር አንዳንድ Neo-colonial ደራስያን በርካታ ከሆኑት መመሳሰሎቻችን ይልቅ ጥቂት ወደሆኑት ልዩነቶቻችን በማትከር መጽሐፍት ሰይቀር ስለሚያሳትሙ ያንን የትክክለኛ ሊቃውንት ሥራ መስሎን እንዳለ ያለትችት በመቀበል ጽሑፋቸውን እንደሕግ ተቀብለን መለያየት ጀምረናል። ይህ ሁኔታ አሳዛኝና ለሰሚው ግራ ነው። ሊሆን አይችልም እንጂ የሚሆን ቢሆን ኖሮ የተለያየ ቋንቋ መናገራቸው በአንድነታቸው ጥያቄ ላይ ያላለያያቸው ስመጥሩ ኢትዮጵያውያንን ለአንድ አፍታ እንኳ ከመቃብራቸው መስከት ብቅ ብለው የኛን የልጆቻቸውንና የልጅ-ልጆቻቸውን «በፈረንጅ» በተፃፉ መጽሐፍትና ጋዜጣዎች አፃፃፍ ሳቢያ ለመጣጣምና ዛሬ አገር የደረሰባትን ችግር በጋራ ለመፍታት አለመሞከር ቢያዩ ምንኛ በኛነታችን ባፈሩ ነበር። እዚህ ላይ ትግርኛ ተናጋሪዎቹን ጀግኖች አብራሃም ደበጭን፣ ዘርአይ ደረስንና ጀግናው አሉላ አባነጋን፣ አሮምኛ ተናጋሪ የነበሩትን የምኒልክ የጦር ሚኒስትርን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዎርጊስን (ሀብቴ አባመላ)፣ ጉራጌኛ ተናጋሪውንና የጠላት መብረቅ የነበሩትን ባልቻ አባነብሶንና ሌሎችንም በብዛት መጥቀስ ይቻላል። እኒህ ክቡር ሰዎች ኢትዮጵያን የገነቡት በሰማበለው እግካኝነት እየተወያዩ ጭምር ሳይቀር ለመሆኑ እንዳንድ አዘውንት ይናገራሉ። እኛስ በፈረንጅ አገር ያለን አበሾች የሀገር ጉዳይ እንኳ ቢቀር በየምንኖርበት አገር

ለግል ጥቅማችንና ለክብራችን፣ ለመብታችን የምንከራበት ነገር እንኳ ማቋቋም ሲያቅተን እንደምን የነዚህ ስመ-ጥሩ ጀግኖና ኩሩ ዝርያዎች ነን ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር እንችላለን። ዛሬ ይህንን እንዳንገናኝና እንዳንረዳዳ የተጋረደብንን ጊዜያዊ (temporary) ሥነልቡናዊ (psychological) ጽልመት ገላልጠን በስደት ያለን የኢትዮጵያ ልጆችና የሐበሻ ዝርያዎች ሁሉ «በበሌ የወጣውን ጀግና፣ በበሌ የወጣውን ፈሪ» እያልን መከፋፈሉን ትተን እጅ ለእጅ ተያይዘን ቢያንስ በፈርንጅ አገር የሚደርስብን የአውሮፓና የአሜሪካ (አፓርታይድ መሰል) የዘር ጭቆናና የኢኮኖሚ ብዝበዛ ለመቋቋም የምንችልበትና፣ ታሪክ ያለን ሕዝብ መሆናችንን የምናሳውቅበት ሕብረት መፍጠር ይኖርብናል። እቁብ፣ እድር፣ ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ፣ እነዚህና ሌሎች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና፣ የማህበራዊ ተቋሞች ለአበሻ ሕዝብ እንግዳ ነገር አይደሉምና በዚህ መልክ እንኳ ግንኙነታችንን መወጠኑና ማጠናከሩ ማለፊያ መነሻ ይመስለናል። እለበዚያ እንኳን ለአገራችን መመኪያ ልንሆን ቀርቶ ለራሳችንም ፋይዳ የማይኖረን በባህር ውስጥ እንደተበተነ ጨው ደብዛችን የማይገኝ ፍጡራን ሆነን እንደምንቀር ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

እስከሁን በቀረብነው ሐተታ የተመለከትነው የምዕራብ ጋዜጦች (ቀኝ፣ ግራ፣ ማህል ሰፋሪን ደምሮ) በግልም ሆነ በቡድን የኮሎኒል መንግሥቱን አመራር በማጥቃት ሳቢያ ምን ያህል በአገራችንና በእኛነታችን ላይ ለረጅም ጊዜ የማይሽር የፐሮፓጋንዳ ነቀርሳ እንደተከለና የእኛንም ሞራል እንደነኩ ነው። እዚህም ላይ ልናስታውሰው የሚገባ ጉዳይ፣ መንግሥት፣ ግለሰብ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ሁሉ የሚያልፉ፣ የሚለወጡ፣ ወይም የሚሞቱ ነገሮች መሆናቸውን ነው። አገር ግን የዚህ ዓይነት አደጋ ሲደርስባት የሚይገባ ስለሆነ በያለንበት ለሀገራችንና ለነፃነታችን መቆም ማለት ስለአገራችን የሚፃፉትን ጋዜጦችና መጽሔቶች እንብቦ ከትክክለኛው ማንነታችን ጋር ማነፃፀርና የሚነቀፈውን መንቀፍ ጽሑፍንም መሰብሰብ ጭምር ይመስለናል። ስለሆነም እኛ በነሲብ (randomly) የሰበሰብናቸውን የጋዜጣ ጽሑፎች ኢትዮጵያን በተመለከተ አቀራረባቸው ይዘት በመመራት ብቻ እንደሚከተለው በሦስት ዘርፍ መድበናቸዋል።

ሀ) ቀኝ ክንፍ (ወግ አጥባቂ) ጋዜጣዎች፣
ለ) ለሥላሴ (ማህል ሠፋሪ ወይም ሊብራል) ጋዜጣዎች፣
ሐ) ግራ ክንፍ (ሸሽሊስታዊ ባህርይ ያላቸው) ጋዜጣዎች፣

በነዚህ ሦስት እርእስት ሥር የመደብናቸው ኢትዮጵያ ነክ ጽሑፎች ረሀብን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ጉዳዮች የሚነኩ 120 እርእስት በ፲፫ የምዕራብ ጋዜጦች የወጡ ናቸው። ለዚህ ሐተታ የመረጥናቸው ግን 17 እርእስት ሲሆኑ እነሱም ረሀብ ጠቀስና ለረሀብና ለድርቅ ጉዳይ ቀረብ የሚል

እስተያየት ያላቸው ናቸው። በዚህ ትንታኔያችን በአብዛኛው የምንመረምረው ጽሑፎቹን ብቻ ሲሆን አልፎ አልፎም ደራሲዎችንም ጭምር ለማስተዋል እንሞክራለን። የነዚህ የመረጥናቸው ጽሑፎች አርእስት በሚጌት (ጣእም) በትርጉም ሳቢያ እንዳይለወጥ ስለስጋን በተፃፉበት ቋንቋ እንዲቀመጡ መረጥን (7)።

ሀ) <u>ቀኝ ክንፍ (ወግ-አጥባቂ) ጋዜጣዎችና ኢትዮጵያ-ነክ ድርሰቶቻቸው</u>።

የድርሰቶቹን አርእስት! እንደሚከተለው ከደረደርን በኋላ ወደ ትንታኔው እንገባለን

፩ «Draught Spreads Death Across Africa» <u>The New York Times</u>, Nov. 4, 1984, p.3.
፪ «Man, Not Nature, Blamed for Many Disasters» <u>The New York Times</u>, Nov, 18, 1984.
፫ "Relief Official Accuses Ethiopia of 'Biting the Hand' that Feeds It" <u>The New York Times</u>, Dec 13, 1984, p. A1 & 13
፬ «Ancient Holy City Starves» <u>The New York Times</u> Dec. 27, 1984 p. A8.
፭ «Human Stupidity, Mismanagement Behind Tragedy in Ethiopia» <u>The Ottawa Citizen</u> January 8, 1984
፮ «Americans Give $40 Million in Two Months To Aid Ethiopia» <u>The New York Times</u> Jan. 1, 1985, A5.
፯ «Playing Games With Starvation» <u>The Washington Post</u> June 16, 1985, P.15.
፰ «Aid Floods Ethiopia, But It Isn't Feeding Its Hungry,» <u>The Gazette</u>, July 6 1985, P.B6.
፱ «Ethiopia Faces Disaster Again, Relief Officials Say» <u>The Globe & Mail</u>, Nov. 13, 1987, P.A13.

ከላይ ከተዘረዘሩት አርእስት ውስጥ በቁጥር ፩ እቅጣጫ የሠፈረውን ጽሑፍ ያቀረቡት በሮም ከተማ የተመደቡ የኒውዮርክ ታይምስ ቃል አቀባይ የሆኑ ሄንሪ ካም (Henry Kamm) የተባሉ ግለሰብ ናቸው። ይህ ጽሑፋቸው የኢትዮጵያ ወቅታዊ እክሎች (ረሀብና ድርቅ) እንደወረርሽኝ በሽታ ወደሌሎች የአፍሪቃ አገሮች በመዛመት ላይ መሆናቸውን ይጠቁማል። የዚህ ጽሑፍ ስውር ዓላማው ግን ኢትዮጵያን የችግር ተላላፊ በሽታ አዛማች አገር ምስል (image) መስጠት መሆኑን ከይዘቱ እንገነዘባለን። ደራሲው ሶማሊያን (የዛሬ የአሜሪካ የፖለቲካ አጋር ነችና) ድርቅና ችግር የማታውቅ አገር ይመስል የሶማልያን ችግር የሚያጠናክረው «ከኢትዮጵያ የተሰደዱ ኢትዮጵያውያንን መቀለቡ ነው» ይላሉ። ጋዜጠኛው በሶማሊያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ

ክሚሽንና ልዩ ልዩ የምዕራብ ርጥባን ሰጪና የሃይማኖት ድርጅቶች እርዳታ መስጠታቸውንና እንዳውም ሶማሊያ እልፍ እልፍ «በስደተኞች ስም ትነግዳለች» ተብላ መከሰሷንም ይሸሽጋሉ። ደራሲው ቁልጭ ያለ ዓላማቸው ኢትዮጵያን የችግር ሁሉ እመንጪ አድርጎ ለማቅረብ ነውና የሶማሌ የድርቅ ችግር የተነሳው በአፍሪካ ከደረሰው የዝናብ እጦት መሆኑ እየታወቀ ከኢትዮጵያ የተሰደዱትን ግለሰቦች ለሶማሊያ የድርቅ ችግር ከዋነኛ ምክንያቶች እኩል ተጠያቂ ያደርጋሉ። የዚህ ክርክር ግልባጭ እንጋገር እኮ «ኢትዮጵያ ስደተኛ አመንጪ አገር ባትሆን ኖሮ የሶማሊያ ችግር መሠረታዊ መንሥኤው በአፍሪካ ከተሠራጨው ድርቅ መሆኑን ቁልጭ አድርገው አያሳዩንም። ነገሩ ጠፍቶአቸው ሳይሆን የጽሑፉ ዓላማ የኢትዮጵያን ውድቀት ማጉላት ስለነበር ነው። እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ግን አብዛኛውን ጊዜ ለምዕራብ ጋዜጠኞች «የአፍሪቃ ውድቀት» ሁሉ ምርጥ ምሳሌአቸው ኢትዮጵያ ነችና ስለአፍሪካ ጉዳይ ባወሩ ቁጥር ነገሩ ባይመለከታትም ጽሑፋቸውን ለምጠው የኢትዮጵያን ስምና «ውርደትዋንም» በመዘርዘር የሀገሪቱ ስም በተጠቀሰ ቁጥር ለአደጋጭ ወይም ለአንባቢ ረሀብ፣ እልቂት፣ ውድቀት፣ መከራ፣ (by association) ትዝ እንዲል የሚያከሂዱት ሳይከሎጂካዊ ጦርነት (warfare) አንዱ ምሳሌ ይህ ጽሑፍ መሆኑን ነው።

በቁር ፰ (8) እግጣጫ የሠፈረውና በዊልያም ሻውክሮስ (William Shawcross) የተፃፈው ድረሰት በኢትዮጵያ ምስለ-ምድር (map)ና በአንድ በጣም በከሳና እፊቱ ላይ ስቃይና ተስፋ መቁረጥ በሚነበብበት ህፃን ምስል የተደገፈ ነው። የጽሑፍ መነሻ ምክንያት ምግብ ለረሀብተኞች በተፈለገው ጥድፊያ አለመድረሱ ይምስል እንጂ ስውሩ እምብርት ዓላማ ግለሰቡ በኢትዮጵያ ሰሻሊስትነትና በወታደራዊው አመራር ላይ ያላቸውን ርእዮተዓለማዊ (ፀሐፊው ወግ አጥባቂ ናቸውና) ቂም መወጣት ይመስላል። ጽሑፋቸው ግን በግል ጥላቻ ብቻ የተሞላ እንዳይሆንና በሕዝብም (አንባቢ) ዘንድ ድርሰቱ «ሚዛናዊና እውነተኛ» ሆኖ እንዲታይ አድርጉ ማቅረብ «የሙያ ግዴታቸው» ነው። ስለዚህም ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው «ማርክሰዊ አመራር» በሞት አፋፍ ላይ ለሚገኙ ረሀብተኛ ኢትዮጵያውያን ደንታ የለውም የሚለውን (ለምዕራብ ጆሮ የሚጥም) መልእክት ለማስተላለፍ እንዲያመቻቸው መቀመጫቸው ከኢትዮጵያ የሆነ የምዕራብ አገር ዲፕሎማቶችንና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን እንደ ዜና ምንጫቸው በመጥቀስ እንዲህ ሲሉ ይጽፋሉ። «በርከታ የኢትዮጵያ ከባድ የጭነት መኪናዎች በንግድ ዘርፍ ይሠማራሉ ወይም ለመንግሥቱ የጦር ዘመቻ ተመድበዋል። ይበልጡ ደግሞ አወዛጋቢ ለሆነው አዲስ የሠፈራ ፕሮግራም ዘመቻ ተወስደአል።» ይህ ዓይነቱ ዜና በምዕራቡ ዓለም ዛሬ ደህና ገበያ አለው። የሠፈራውን ፕሮግራም ግን ከለውጡ በፊት የነደፉት የምዕራብ መንግሥታት እርዳታ ለጋሽ «የልማት» ድርጅቶች ናቸው። ይኸውም ከለውጡ በፊት

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የዓለም ባንክ ስለኢትዮጵያ ሰሜናዊ የድርቅ ችግር ባጠኑት ጥናት ሁሉ የአካባቢው ችግር ዓይነተኛና የዘለቄታ መፍትሔ ከሕዝቡ ከፊሉን ሕዝብ በብዛት ወደአልሠፈረባቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች ማዛወር ነው ብለው ለመደምደማቸው በርካታ ተጨባጭ መረጃዎች አሉ። ምዕራባውያን ትላንት (ከለውጥ በፊት) መፍትሔ ብለው ያቀረቡትን የሠፈራ እቅድ ዛሬ የወቅቱ መንግሥት «ኰሚዩኒስት በመሆኑ» ብቻ ይቃወሙታልና የዚህ ዓይነቱ ጋዜጠኛ ሥራና ሥነ-ጽሑፍ ይጥማቸዋል። ምዕራባውያን በሥውርና በግልጽ ከሚያካሂዱት የዲፕሎማቲክና ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ በተጨማሪ የዊልያም ሻውክሮስ ዓይነቱ የጋዜጠኛ ቃላት ጦርነት እንጀታቸውን ያርሰላቸዋል። እንንዲህ ዓይነቱን ጋዜጠኛ የዚህ ዓይነቱ ወሬ ጥም ያላቸው አንባቢዎች «ዊልያም ጉሽ፣ አበጀህ! ያሰድግህ፣ ግመን ድገመን» ብለው ካንጀት መመረቃቸው አይቀርም።

በቁጥር አራት እንዳር በክሊፎርድ ሜይ (clifford D. May) የተፃፈው ዘገባ ደግሞ ከሰባቱ የዓለም አስደናቂ ነገሮች እንደ አንዱ ሆነው ሊቆጠሩ ይገባል ተብለው በብዙ ሊቃውንት የሚነገርላቸውንና የምንኮራባቸውን ከቋጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩ ቤተመቅደሶች ያሉባትን የላሊበላን ምድር የረሀብተኞችና የድኩማን መናኸሪያ መሆኗን የሚያበስር ነው። ደራሲው ጽሑፉን ያቀረቡት ከላሊበላ ከተማ «ሆኜ ነው» ቢሉንም ከዚያ ሁሉ የረሀብ፣ የጭንቀት፣ የደዌ፣ የመከራና የሥቃይ ሐተታቸው ውስጥ ስለዚህ አስደናቂ የኢትዮጵያ የሥልጣኔ ቅርሶች (ማለት የቅዱስ ላሊ.በላ አድባራት) አንድ ዓረፍተ ነገር እንኳ አልጨመሩም። ጉድ ነው ሚዛናዊነት፣ የምዕራቡ ጋዜጠኝነት! ትርፉ ትዝብት ነው እንጂ እኒህ ጋዜጠኛ ስለነዚህ መቅደሶች ፃፉም አልፃፉም ታሪካዊ ደረጃቸው አይቀንስም፣ አይጨምርም። አቶ ክሊፎርድ ሜይ የምዕራቡ ጆሮ አቆብቁቦ የሚጠብቀው ስለኢትዮጵያ ውድቀት ብቻ ለመስማት እንጅ እንዲህ ያለውን እጹብ ድንቅ ታሪካዊ ሥራ የሚያደንቀውን አለመሆኑን አበክረው ያውቃሉ። እንደውም የወቅቱ የምዕራብ ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ የሚያደርጉት እሽቅድምድም ይበልጥ አስቃቂና የሚዘገንን የረሀብ ቀበሌ (pocket) በመፈለግ ለምዕራብ አድማጮቻቸው «ሶሺሊዝም የሚፈጽመው ጭካኔ ይህን ይመስላልና ፊታችሁን ወደዚያ እንዳታዞሩ» የሚለውን መሠሪ (subtle) መልእክት ለማስተላለፍ ይመስል ነበር። ስለሆነም የኢትዮጵያ ታላቅ የሥልጣኔ ቅርስ ሥፍራም (ላሊበላ) ቀና (positive) ነገር ቢፃፍበት የዚህችን «አስቀያሚ ኮሚዩኒስት» አገር ምሥል (image) በምዕራቡ አንባቢ ዘንድ ከመቀየር አልፎ ሥፍራውን እንጎብኝ የሚለው ቱሪስት ስለሚበረክት ጥንቃቄ ያደርጋሉ። እንግዲህ እዚህ ላይ የጋዜጠኛው ተልእኮ ጥንድ መሆኑን ነው። ስለላሊበላ አስቀያሚ ዜና በማውጣታቸው «ሶሻሊስት ኢትዮጵያ» ምን ያህል አስቃቂ አገር እንደሆነች በሚደረገው የፕሮፖጋንዳ ጦርነት የራሳቸውን የቃላት ጥቃት ለመፈፀም

ያስችላቸውል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከቱሪስቶች ጉብኝት ልታገኝ የምትችል የነበረውን ገበያ በዚህ ጽሑፋቸው አማካኝነት ይደፍኑበታል። «በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል» ይሉ የለ ምዕራባውያን በተረታቸው። ግን አንድ ብልህ አንባቢ የዚህ ዓይነቱ (የጋዜጠኛ ክሊፎርድን) ጽሑፍ በነበበ ጊዜ ሊጠይቀው የሚገባ ጉዳይ አለ። ይኸውም ጋዜጠኛው ስለቅዱስ ላሊበላ ህንፃዎች ምንም ያልፃፋት የጹሑፍ ዓላማ የላሊበላን ከተማ የረሀብ ችግር ለማጉላት ብቻ ስለሆነ ነው እንዳይባል ጋዜጠኛው ከተማዋ በፀረ-መንግሥት ተዋጊ ኃይሎች ተይዛ እንደነበር በዚሁ ጽሑፍ ሐተታቸውን አቅርበዋል። ስለዚህ ጋዜጠኞቹ በኢትዮጵያ ላይ በመድረሱ የተደሰቱበትን ጉዳይ ሁሉ ይጽፋሉበታል።

በኢትዮጵያ ሊያዩ ያልፈለጉትን ደግሞ ጨርሶ እንዳልነበር ሁሉ (እንደላሊበላ ሕንፃ ጉልህ ቢሆንም) ያልፋታል። ከተማ በፀረ-መንግሥት ወያኔዎች ተይዛ እንደነበር መግለጡ ግን ለጋዜጠኞቹ ሥውር ተልእኮ አንድ ተጨማሪ ነጥብ ስለሆነ በረሀቡ ሀተታ ውስጥ በግድ ቦታ ፈልገው ይደሉታል። የጋዜጠኛው ገሃድ ተልእኮ የረሀብ ዜና መሰብሰብ ቢሆንም የኢትዮጵያን «አሳፋሪና ፀያፍ ጉዳዮች» አጉልቶ ማሳየት ደግሞ ደራሲው የተላኩበት ሥውርና ዓቢይ ዓላማ መሆኑን የምዕራብ ብልህ አንባቢ በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል። በገጽ 29 እና 30 ላይ የሠፈሩት ሌሎች አርእስት ማለት ቁጥር ፪፣ ፫፣ ፭፣ ፮፣ ፯ እና ፱ ይዘት ሥፍራ ለመቆጠብ ስንል በንተነትናቸውም ርእሶቹ የጽሑፉን ማእከላዊ ዓላማ እንደሚጠቅሙ አንባቢያንን በማስገንዘብ እናልፋቸዋለን።

ለ) ለሥላሴ (ማህል ሠፋሪ ወይም ሊበራል) ጋዜጣዎች

እነዚህ ዓይነት ግዜጣዎች በጠቃላይ አቂማቸው የምዕራቡን ሁኔታ በሚተነትኑበት ጊዜ «ሊበራል» አቂም ይዘው ቢሆንም የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚመለከት ከወግ-አጥባቂዎቹ ጋዜጣችዎች እምብዛም የተለዩ አይደሉም። ለሥላሴ («ሊበራል») ጋዜጣዎች አንድ ጊዜ ከግራ ክንፍ ሌላ ጊዜ ከቀኝ ክንፍ በመዋዠቅ የሚጽፉ ሲሆን በአቀራረባቸው ደግሞ ማንኛውንም አንባቢ በማያስቀይም መልክ ይመስላል። «ለስላሴ» ብለን የሰየምናቸውም ለዚሁ ብለን ነው ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደሞከርነው ሊበራል ፀሐፊዎች ኢትዮጵያን በሚመለከት (በነሱ አስተያየት ኢትዮጵያ አፍሪካዊ ሶቪየት ሆናለችና) ሲጽፉ ባንድ በኩል ፀረ-ሶቪየት ኮሚዩኒስት ፕሮፖጋንዳቸውን ለመንዛትና የተደበቀ ፀረ-ጥቁር ሕዝብና ፀረ-አፍሪካ አቂማቸውን ያንፀባረቀበት ሁኔታ ታይቷል። በዚህ ረገድ በእኛ አመለካከት እንኳን ሊበራል ነጮች ቀርቶ «ኮሚዩኒስቶች ነን ለዓለም ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ አንድነት ነው የቆምነው» የሚሉት ሶቪየቶች እንኳ አዘውትረው ከዘረኝነት

ነፃ አለመሆቸውን የሚመሰክሩ አያሌ ድርጊቶች መጥቀስ ይቻላል። (8) የምዕራቡን ዓለም ሁኔታ እግሩ ምዕራብን የረገጠ የጥቁር ዘርና ኢትዮጵያዊ ሁሉ ስለሚያውቀው በዚህ ላይ ምሳሌ አንጠቅስም። በዚህ «ለ» ክፍል ለምናከናውነው ትንታኔ የተጠቀምንባቸው የጋዜጣ ጽሑፎች በሙሉ የተገኙት ከካናዳ ነው። ይህም የሆነው ባጋጣሚ ሳይሆን ሆን ብለን ነው። ለዚህ የመረጥነው ጋዜጣ በተለይ ቶሮንቶ ተብላ በምትታወቀው የካናዳ የኢኮኖሚና የባህል ዋነኛ መናኸሪያ ከተማ የሚታተመው The Toronto Starን ነው። የቶሮንቶ ስታር ሌሎች በአሜሪካ ከሚታተሙ ጋዜጣዎች ለየት ብሎ ያገኘንበት ምክንያት በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ፒር ኤልየት ትሩዶ ስር ለ16 ዓመታት ያህል በሥልጣን የቆየውንና አሁን ግን የዋና ተቃዋሚነት የፖለቲካ መድረክ ይዞ የሚገኘውን የሊበራል ፓርቲ ስለሚደግፍ ነው። ከዚህም በላይ ካናዳ በዚህ የፖለቲካ ፖርቲ የሥልጣን ዘመን «ዘረኝነት በኛ ዘንድ ፈጽሞ የለም፤ እኛ የብዙ ብሔሮችና ባህሎች (multi-ethnic & multicultural) አገር ነን» ብላ ድምጿን ጎላ አድርጋ የምትናገር አገር ስለነበረች የዚህን ፖርቲ አቋም የሚደግፍ ጋዜጣ ለኢትዮጵያ ከሌሎች የአሜሪካ ጋዜጦች የተሻለ የዜና አቀራረብ (coverage) ይሰጣል በማለት ነበር። ይሁንና ግምታችንና የጥናታችን ውጤት የሰማይና የመሬት ያህል መራራቃቸውን አንባቢዎች ሊገነዘቡት ይችላሉ። በቶሮንቶ ስታር ከወጡት በርካታ ርእሶች ውስጥ የሚከተሉትን ብቻ ለናሙና ያህል ወስደናል።

፩ «Marxist Atrocities Reported in Ethiopia « Relief Camps» The Toronto Star August 1, 1986, P.A13.

፪ «African Nations Cry poor But Lavish Money on Armies» The Toronto Star, March 24, 1988, p.A26.

፫ «5 Million Ethiopians Face Starvation,» The Toronto Star, Nov. 22, 1987, P.H2

፬ ) «Fight Famine, Not People Geldof Urges Governments,» The Toronto Star, Dec. 2, 1987.

፭ ) የካርቱን ሥዕል በገጽ 90ላይ የተመለከተ፤ The Toronto Star, Dec. 22, 1987.

ሀ

በመጀመሪያ በቁጥር አምስት እንፃር የተጠቀሰውን የካርቱን ሥዕል ልብ ብለን እናስተውል። እንደምስሉ አቀራረብ ነዋሪነቱ በሰሜን የምድር ዋልታ (pole) የሆነው የገና አባት (Santa Claus) በምቹ ወንበሩ ላይ ተጉዘጉዞ ተቀምጦ ዙሪያው ለህፃናት የሚናኛቸው ልዩ ልዩ አሻንጉሊቶችና መጫዎቻዎች ተከበ

Tuesday, December 22, 1987

# EDITORIAL



ይታያል። በጠኔ ምክንያት እጆቹና እግሮቹ የሰለሉበትና አለእድሜውም ፀጉሩ የተመለጠበት ህፃን የገናው አባት ጭን ላይ ተቀምጦ አፉን ከፍቶ እንደወሰፌ በሾለ ጣቱ ለገናው አባት ጉሮሮውን ያመለክተዋል። አጽሙ ብቻ ከቀረው ህፃን መቀመጫ በኩል የሚታየው አራፊ ጨርቅ ህፃኑ የሚወክለው ኢትዮጵያን ለመሆኑ የሚያሳየን በእንግሊዝኛ Ethiopia ተብሎ ተጽፎበታል። የዚህ ምስል ጭብጡ የተሞላበት አቀራረብ መሆኑን መረዳት የሚቻለው የምዕራብ ህፃናት ሁሉ በገና ወቅት የሚጠይቁት መጫወቻ እንጂ እህል እንዳይደለ ከቃላት የበለጠ ይነግረንና አጥንቱ የገጠጠው ህፃን (ኢትዮጵያ) ግን ከህፃናት መጫወቻ በስተቀር እህል ባጠገቡ የሌለውን «ሳንታ» ወደጉሮሮው የሚልከው ምግብ ሲጠይቀው መታየቱ ነው።

ይህ እንኳን በኢትዮጵያ ምድር ላለው አበሻ እኛም እዚህ ላለነው (ችግሩን ላልቀመስነው) የአገሪቱ ተወላጆች መጥፎ ምስል (image) በያለንበት ሕብረተሰብ አእምሮ እንደሚቀርጽ መረዳት አያዳግትም። ስለዚህም ነው ለአንዳንድ ፈረንጆች «ኢትዮጵያዊ ነኝ» ብለን ስንነግራቸው፣ «ታዲያ ወደዚያ ትመለሳለህ/ሽ?» ብለው በድንጋጤ የሚጠይቁን። እንደውም አንዳንዶቹ ኢትዮጵያዊነት ማለት ረሀብተኝነት የሚመስላቸው «አ አንተ/አንቺ እድለኛ ነህ/ነሽ በዚህ ጊዜ እዚህ መኖርህ/ሽ» የሚሉን። የዚህ ዓይነት ካርቱኖች በምዕራብ ዓለም ኢትዮጵያን አስመልክቶ ወጥተዋል። ይህ እጅግ አስቃቂ ሥዕል በልዩ ልዩ የምዕራብ ጋዜጣዎች ከሚወጡ መሰል የምዕራቡ የኃይልና የሀብት እብሪት መግለጫዎች እንደአንዱ በምሳሌነት ተወሰደ እንጂ ከሁሉም የከፋው ነው ማለት አደለም። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ግን ደጉና ሀብታሙ የገና አባት የምዕራቡን ዓለም ለጋሥነት የሚያሳይ (image) መሆኑን ነው። የዚህ ዓይነቱ ምስል ከምዕራብ (መጽዋቹ ዓለም) ተወላጆችና ከእኛ ከሐበሾች (የተመጽዋቾች ዓለም) ተወላጆች አእምሮ እንድያውን ከዚህ ዓለም በሞት ካልተለየን በስተቀር እንደምን ሊፋቅ ይችላል?! የዚህ ዓይነቱስ ምስል (image) ዛሬ በስደት ከየምንኖርበት የምዕራቡ ዓለም ሕብረተሰብ ፊት (በጥቁርነታችን ከሌላው ጥቁር ሕዝብ ጋር ከሚደርስብን ዘረኝነት በተጨማሪ) በምን መልክ እንድንታይ ያደርገናል?! «ምስኪን ረሀብተኛ ስደተኞች!» ይህ ሳይኮሎጂካዊ ውጊያ ቁስሉ ለአእምሮአችን ሥቃይ ለሆድ እቃችን ነቀርሳ ሆኖብን የሚያስቃየንን በባእድ ምድር የምንኖር እገር ወዳድ አበሾችን ቤታችን ይቁጠረን።

ይህ በምዕራቡ ዓለም ረሀብተኛ የሌለ የሚያስመስለው የገና አባት ምስልስ

የምዕራቡን ዓለም የማጀት ምስጢር ለመሸፈን የቀረበ አይደለም ወይ የሚለውን ብልህ ጥያቄ እልፎ እልፎ እንበቢዎች ያነሳሉ። በእንፃሩስ እንደ ኢትዮጵያ በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ አይገኙ እንጂ በምዕራቡ ዓለም በተለይ በአሜሪካ አገር ረሀብተኞች የሉም ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል እንዴ? አይቻልም። ይህንንስ ዓይን ያወጣ ነጭ ውሸት እኛ በአሜሪካ ትላልቅ ከተሞች የምንገኝ ኢትዮጵያውያን አንቀበለውም። በአሜሪካ በችግርና በረሀብ አለንጋ ከሚገረፉት ይበልጡኑ ከ400 ዓመታት በፊት ከአፍሪቃ በባርነት ተሸጠው የመጡ ጥቁር ወገኖቻችን ዝርያዎች አይደሉምን?! የነዚህ ወገኖች አሜሪካዊነት እጅግም የፈየደላቸው ነገር እንደሌለ አያሌ አዋቂዎች ይናገራሉ። (9) ከጥቂት ወራት በፊት ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት በዲሞክራቲክ የፖለቲክ ክልል በመወዳደር ላይ የሚገኙት ታዋቂው ጥቁር አሜሪካዊ አቶ ጄሲ ጃክሰን ዛሬ ብዙ የአሜሪካ ጥቁሮች የሚገኙበትን ሁኔታ «አሜሪካዊ አፓርታይድ» የሚሉት ለዚህ አይደል!

ከላይ በተራ ቁጥር ፪ የተጠቀሰው ርእስ የሚያመለክተው ምን ያህል የአፍሪካ ሕዝቦች እየተራቡ የአፍሪካ መንግሥታት የተራቀቀ የጦር መሣሪያ እንደሚያከማቹና ምን ያህል በርካታ ወታደሮች እንደሚያሰለጥኑ ነው። ነገሩ እውነትነት ቢኖረውም አንድ የተገደፈ ሀቅ አለ። ይኸውም በነዚሁ የአፍሪቃ አገሮች በጦርና በኤኮኖሚ እንዲሁም በፖለቲክና በንግድ አማካሪነት የሚመደቡት የምሥራቁም ሆነ የምዕራቡ አገር ወኪሎች የየሀገራቸውን የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ ውጤቶች ለነዚሁ ምስኪን የአፍሪቃ አገሮች ለመሸጥ ሲሉ በረጅም ጊዜ ብድር ሰምና በወታደራዊ እርዳታ እነዚህኑ «የረቀቁ» የሚሏቸውን ነገር ግን «ኋላ ቀር» መሣሪያዎቻቸውን እንደሚያራግፉባቸው ነው። ወደ ጽሑፉ ቁምነገር እንመለስና የጽሁፉን መጠን እንመልከት። ለዚህ ርእስ የአንድ ጋዜጣ ገጽ ከአምስቱ አራቱ እጅ የተለቀቀለት ሲሆን በሁለት ትላልቅ ፎቶግራፎች መረጃነት (illustration) የተደገፈ ነው። ደራሲው አቶ ጆን ኤድሊን (John Edlin) በዚምባቡዌ (ሐራሬ) የተመደቡ ሪፖርተር ናቸው። የጽሑፋቸውን ታማኝነት ለማጠንከር ጣልቃ ካስገቧቸው ምስሎች (pictures) አንዱ በሶቪየት ሕብረት የተሠሩ ሮኬት አመንጣቂና ሚሳኢል ተሸካሚ ከባድ የጦር ካሚዎኖችን የሚያሳይ ይገኝበታል። በሥዕሉ ስር የቀረበው ማብራሪያ እንዲህ ይላል። «ድህነት ያደሸቃቸው የአፍሪቃ ሀገሮች ይህንን የኢትዮጵያ ሮኬት ማምጠቂያ ከባድ መኪና የመሰለ አላቸው። ግን ረሀብተኞቻቸውን ለመመገብ ገንዘብ ይለምናሉ። ኢትዮጵያ ከዓመታዊ በጀቷ 9.3% (ጋዜጠኛው

የእሀዝ ስሀተት የፈፀሙ ይመስለናል) ለመከላከያ ስትመድብ ከሶቪየት ሕብረት ሁለት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ የጦር እርዳታ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ተቀብላለች።» እዚህ ላይ የጋዜጠኛው ጠብ የጦር መሣሪያው ለምን ከሶቪየት ሆነ ይመስላል እንጂ ለምን የምዕራብ አውሮፖ አገሮች የጦር መሣሪያ እንዲስትሪዎችስ ለብዙ የአፍሪካ አገሮች እንደሚሸጡ ጠቀመው ይህንን ድርጊት በጠቃላይ አያወግዙም ነበር?! ሌላው ሥዕል ደግሞ በንቃት ተሰልፈው በሙሉ ትጥቃቸው በረድፍ የሚያልፉ አፍሪቃዊ ወታደሮች ያሳያል። ከሥዕሉ ሥር የተፃፈው ማብራሪያም እንዲህ ይላል። «በአፍሪቃ ብዙሐኑ ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎታቸውን የሚያረኩበትን ሁኔታ እየተነፈጋቸው ወታደሮቹ ግን በሚገባ ደሞዝ ከመከፈላቸውም በላይ ሽክ ብለው የሚለብሱና በሚገባ የሚመገቡ ናቸው። ከዚህ በላይ የሚታዩት ወታደሮች ኢትዮጵያውያን ናቸው።» ለዚህ አቀራረብ ለምን ኢትዮጵያ ተመረጠች? እኛ እንደምንገምተው ለዚህኛው ምሥልና አገላለጥ መመረጥ የሚገባው የደቡብ አፍሪካ ወታደራዊ ተቋም ነበር። ደቡብ አፍሪቃ የኒውኩሊየር መሣሪያ ሳይቀር በምሥጢር እለት ይበላል። በጥቁር አገር ላይ ወታደሮቹ ነጮች ናቸው። ጥቁር ሕዝብ በቴክኖሎጂ በዳበረችና በበለፀገች ደቡብ አፍሪቃ ለዓይን በሚያሰቅቅ ሁኔታ ይኖራል። እኒህ ጋዜጠኛ እውነት ሚዛናዊ ከሆኑ ለምን ይህንንም ሁኔታ አላጋለጡም ነበር?! ደራሲው ግን ከደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ጋር የዘርም ሆነ የርእዮተዓለም ፀብ ስለሌላቸው ሁለቱንም ሥዕሎች ከሚጠሏትና ከሚያጥላሏት ከኢትዮጵያ ብቻ እንዲሆን ወስነው መላው አፍሪቃን እንደለመዱት እግራቸውን አንስተው ተሳድበዋል።

ይህ ከላይ የተመለከትነው አቀራረብ የሚያሳየን ኢትዮጵያ በጠቃላይ ለመላው ዓለም ጥቁር ሕዝብና በተለይም ለአፍሪካ ሕዝቦች መልካም ምሳሌ የምትሆንበትን ጉዳይ፣ ማለት የቀድሞ ሥልጣኔዎቿን ጋርዶ አፍሪቃውያንን ቀርቶ ኢትዮጵያውያን የሚያፍሩባት እስቀያሚና የባህል-የለሾች (Savages) አገር አድርጎ ለማቅረብ የተቀናበረ የምዕራብ ጋዜጦች የማደናቆሪያና ስም የማጥፊያ ዘመቻ ነው። የጆን ኤድሊን ጽሑፍ ይዘት ግን ከኢትዮጵያ ጠኔ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ሲሆን በጠቅላላ ጥቁሩ የአፍሪቃ ክፍል ምንኛ በወታደራዊ ወጪ የተወጠረ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ቀድሞውኑስ ቢሆን መች ይኸ ተከደና የጋዜጠኛው ሥራ መሆን የነበረበት የዚህን ምንጭ ማሳየት ነው።

ወደ ጋዜጠኛ ጆን ኤድሊን ዝርዝር አቀራረብ ስንገባ በኢትዮጵያ፣ በሞዛምቢክ፣ በአንጎላ ያሉት ፀረ-መንግሥት ኃይሎችና መንግሥታቱ

የሚያደረጉትን የጦር ግብ ግብ ነካክቶ ሦስቱም አገሮች በአፍሪቃ ጦርነት የፈሰበቻው፣ በዓለም የመጨረሻ መናጢ ድሆችና በማርክሲስት–ሌኒኒስት መንግሥታት የሚገዙ መሆናቸው ይገለጥልናል። በኛ አስተያየት ይህ ዓይነቱ የዜና አቀራረብ ሐሰተኛ ከመሆኑም በላይ በርእዮተ–ዓለማዊ (ideological) ጠለትነት የተመሠረተ ነው። ምክንያቱም አንጎላና ሞዛምቢክ በተፈጥሮ የተዋቡና ለም አገሮች ናቸው። እንደኢትዮጵያ እንኳ ድርቅ ደጋግሞ ነክቶአቸው አያውቅም። የሁለቱም ብርቱ ችግሮች ሶሻሊስታዊ አመራራቸውን የሚቃወምና በዘር መድልዎ የሚያምነው የደቡብ አፍሪቃ (አፓርታይድ) አገዛዝ ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ ፀረ–መንግሥት ኃይሎች ናቸው። ባደረሱባቸው ወረራና ጥቃት ሳቢያ ሳይወዱ በግድ ከብሔራዊ ገቢያቸው ይበልጡ ለመከላከያ ይመድባሉ። ከሁሉም በላይ አንጎላ የተፈጥሮ ነዳጅ ዘይት ከምችት ያላት ነዳጅ ዘይት አውጭና ላኪ አገር እንደመሆኗ ወደፊት ከአንዳንድ የአውሮፖ አገሮች የተሻለ ለመበልፀግ ችሎታ (potential) ያላት አገር ናት። አገራችን ኢትዮጵያም ብትሆን የዘመናት አስተዳደር ጉድለትና ቀውስ፣ የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት (natural disasters) የገጠማት አገር ብትሆንም በውጭና በሀገር ቤት ያለነው ተቆርቋሪ ልጆቿ ታጥቀን ስልማት ብንነሣ ምድሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ሀብትና ከሁሉም በላይ ችግር የማይበገረው ሕዝቧን በማቀናጀት የማደግና የመበልፀግ ዕድሏ ሰፊ ነው።

የጋዜጠኛ ጆን ኤድሊን ጽሑፍ ዓይነተኛ ዓላማ ምን እንደሆነ በቀጡ ለመረዳት የጽሑፋቸውን ጥቂት የመጨረሻ ዐረፍተ ነገሮች ማጤን ይበቃል። ጽሑፉ በጠቃለይ ይዘቱ የአፍሪካን ድክመትና ውድቀት ለማወጅ የታቀደ ሆኖ የሚከተሉት የማጠቃለያ ሐሳቦች ሠፍረውበታል። እንደሳቸው ድምዳሜ ኢትዮጵያ፣ ሞዛምቢክና፣ አንጎላ በአፍሪቃ እናት ላይ የሚያናጥረውን የ170 ቢሊዮን ዶላር የምዕራብ ዓለም ዕዳ ላለመክፈል እፉቸውን ከሚያሞጣሙጡት አገሮች ግንባር ቀደም ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ይላሉ ጋዜጠኛው፣ ከሶሻሊስት አገሮች ለታዳጊ (developing) አገሮች የሚለከውን የጦር መሣሪያ እርዳታ ከፍተኛውን ድርሻ ያገኛሉ። ለጥቀውም እንደሚሉት፣ ሦስቱ አገሮች በየወሩ የጦር መሣሪያ ክምር ከየወደባቸው እያራገፉ በየወሩ ደግሞ የምዕራብ የምግብ ደረጉት በዚያዋ መጠን እንዲመፀወታቸው እጃቸውን በማርገብገብ ይማጠናሉ። እንግዲህ በጋዜጠኛው አቀራረብ ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት በሦስተኛው ዓለም ውስጥ ጉልህ የሆነ የሥራ ክፍፍል አላቸው። ይኸውም፣ የምስራቁ (ሶሻሊስት)

ዓለም የድሀ አገሮች ሕዝቦች እርስ በርሳቸው መተራረጃ የሚሆናቸውን መሣሪያ ሲያቀርብ የምዕራቡ (ከፒታሊስት) ዓለም ደግሞ የሞት መድኀኒት የሆነውን የምግብ (ሰብአዊ) እርዳታ ብቻ ይለግሳል። በርግጥ ይህ ለምዕራብ የዋሃን አንባቢ ጆሮ ይጣፍጥ እንደሆነ እንጂ ነገሩን እውነት ነው ብሎ የሚያምን ከቶ አይገኝም። ምክንያቱም ምዕራቡን ዓለም (በአሜሪካ ፊታውራሪነት እየተመራ) በአንጎላ፣ በሞዛቢክና በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን ወንድማማቾች እርስ በርስ የሚጫረሱበት የጦር መሣሪያ ለአንጎላው የአቶ ዮናስ ሳቪምቪ ቀኝ አክራሪ ሽምቅ ተዋጊ ድርጅት፣ ለሞዛምቢኩ የደቡብ አፍሪቃ ቅጥረኛ ኤም ኢን አር (M.N.R.ወይም ሬናሞ) ድርጅት እንዲሁም በኢትዮጵያ ያለውን መንግሥት ለሚቀናቀኑ ሁሉ «በሰብአዊ እርዳታ» እሰበው እንዲያቀርቡ ራሳቸውን ፕሬዚዳንት ሬገን በየጊዜው በሚሰጡት የሬድዮ መግለጫ ያልደበቁት የአደባባይ ሚስጥር ነው። (10) ታዲያ ግዜጠኛው እውነት ሚዛናዊ (objective) ከሆኑ ይህንን እውነት ጨለፍ አድርገው ምነው በዘገባቸው አላከሉትም?።

እኚሁ ጋዜጠኛ ለአፍሪቃ አህጉር ጠቅለል ያላቸውን ንቀት በሚከተለው ዓይነት ያንፀባርቃሉ። «አፍሪቃ በዓለም የመጨረሻ መናጢ ድሀ፣ በልማትም ፍጹም ኋላቀር አህጉር ናት። የሕዝቧም ወሊድነት (fertility-rate) አህጉሪቱ ካላት የእህል ማምረት ችሎታ ጋር ሲነፃጸር ከፍተኛ ነው።» ትንታኔአቸውንም በመቀጠል፣ በ35 ጥቁር የአፍሪቃ አገሮች ውስጥ አንድ ሚሊዮን ወታደሮች መኖራቸውን ገልጠው በአንፃሩ ግን 30,000 ዶክተሮችና 1.75 ሚሊዮን አስተማሪዎች ብቻ እንዳሉ ያስረዳሉ። በአፍሪቃ የወታደሮችንም ሥርዓተ-አልበኘነት (indiscipline) ሲገልጹ መለዮ ለባሾች በናይጀሪያ ትጥቃዊ ዝርፊያ እንደሚያካሂዱ ገልጠዋል። ቀጥለውም በዛኢር የደሞዝ ወቅት ያለፈባቸው ወታደሮች ሰላማዊውን ሕዝብ ምግብና መጠጥ ሳይቀር እንደሚነጥቁ ያመለክታል። ጸሐፉ ግን እነዚህን ወታደሮች ከትኩተው ያሰደጉት የምዕራብ የጦር ድርጅቶች መሆናቸውን በፍጹም አይነግሩንም። ጋዜጠኛ ጆን ኢድሊን በ22 የአፍሪቃ አገሮች ውስጥ ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ የአስተዳደሩ ፈሊጥ መሆኑን ጠቁመው መሪዎቹ (ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም እንደተባለው) ከሥር ፍንቀላ (coup d'etat) ስለሚፈሩ ወታደሮቻቸውን ከመጠን ያለፈ እንደሚንከባከቡ ያብራራሉ። አሳዛኙ ነገር ግን ጋዜጠኛው እንደነሞቡቱ ሴሴሴኮና እንደነኢዲ አሚን ዓይነቶችን የአፍሪቃ መሰለቂያዎች ከእምሰ አለቃነት ከትኩቶ ወደመሪነት ደረጃ ያደረሰቻው የምዕራብ ጌቶቻቸው ድጋፍ መሆኑን አለመግለጣቸው ነው።

በዚህ ጉዳይ የአፍሪቃ ሰፊ ሕዝቦች ተጠያቂ አይሆኑም። እርግጥ ወደፊት የሶቪየት ሕብረት አፍሪቃዊ ቡችላዎችም ደህና የርዕዮተ ዓለም «ኩቲ» ለመሆን በመሠልጠን ላይ እንዳሉ አፍሪቃና ሐቀኛ ልጆቿ ያውቃሉ። ይህንን ያህል ሐተታ ስለ «ጥቁር አፍሪቃ» ያኈጎደጎዱት ጋዜጠኛ ጆን ኤድሊን ስለደቡብ አፍሪቃ የነጭ አገዛዝ (Apartheid) መንግሥት ምን ያህል ከባድ ወንጀል ሊነግሩን ይሆን እያልን በጉጉት ስናነብ ያንን እስከፊና ኢሰባዊ አገዛዝ በሚከተለው ልስላሴ የተሞላበት ገራ–ገር አስተያየት ያስናብቱታል። ለማስረጃም ያህል የሚከተለውን ጥቅስ እናስተውል፤

> ደቡብ አፍሪቃ እራሷን ለመከላከል በርካታ ገንዘብ ታጠፋለች። ባለፈው ረቡዕ (ይህ ጽሑፍ በቀረበበት ዋዜማ) የደቡብ አፍሪቃ ወታደራዊ በጀት ወደ 22.6% ከፍ በማለት ጠቅላላ ወጪው ወደ $4.1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲያሻቅብ አድርጎታል። ይህም እስካሁን ከተመደበው የወታደራዊ በጀት ከፍተኛው መሆኑ ነው። (11)

የታለ የደቡብ አፍሪቃ የዘር መድሎ ጉድና ጥቁሮች የቆዳቸው ቀለም ብቻ በገዛ ሀገራቸው ወንጀል ሆኖባቸው እንደአበደ ውሻ እየታደኑ የሚገደሉበት ሁኔታ እንደሞዛምቢክ፣ አንጎላና ኢትዮጵያ «ውድቀትና ጉድ» የተዘከዘከው?! እዬ የምዕራብ ጋዜጠኞች ሚዛናዊነትና ሐቀኛነት! እየነው ጉዱን! ቀደም ሲል እንደገለጥነው ሁሉ በተራ ቁጥር ፩፣ ፫፣ እና ፬ እንፃር የተጠቀሱትን የጋዜጣ እርእስት ሥፍራ ለመቆጠብ ስንል እንባቢያን እንዲመረምሩዋቸው እያበረታታን እናልፋቸዋለን።

(ሐ) ግራ ክንፍ (ሌፍቲስት ሶሻሊስት ባህሪይ ያላቸው) ጋዜጣዎች

ነገሩን በብርቱ ምርምር በመደገፍ ካላጤኑት በስተቀር ባጠቃላይ የምዕራቡ የግራ ክንፍ ጋዜጠኞች ኢትዮጵያን የሚያስተውሉበት ዓይን በጣም ግራ የጋባል። እነዚህ የግራ ክንፍ ጋዜጣዎች በራሳቸው ሦስት ቦታ ሊከፈሉ ይችላል። እነሱም የሶቪየት ሕብረትን አቋም የሚደግፉ የኮሙኒስት ፓርቲ ልሣኖች፤ የንኡስ ከበርቴ «ሶሻሊስት» ነን ባይ ጋዜጣዎችና እንዲሁም የሠራተኛ ማህበራት ጋዜጣዎች ናቸው። እነዚህም እንዲሁ እንደየ አቋማቸውና እንደየባህሪያቸው ሊከፈሉ ይችላሉ። ለዚህ ጽሑፋችን ግን ይህ ትንታኔ አስፈላጊ ስላልመሰለን በየክፍሉ የመመደቡን ነገር እዚህ ላይ አንገፋበትም። በአጭሩ ግን ለሞስኮ አቋም ድጋፍ የሚሰጡ የምዕራብ የኮሙኒስት ፓርቲ ጋዜጣዎች በሚጽፉአቸው ሐተታዎች የኢትዮጵያን «ትክክለኛ ገጽታ» ለማሳየት እንደሚሞክሩ ተገንዝበናል።

ይሁንና እነዚህም ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ልዩ አፍቅሮት ኑሮአቸው ሳይሆን ከሞስኮ ጋር ያላቸውን ርእዮተዓለማዊ አንድነት ለመግለጥ የሚያደርጉት

ይመስላል። የኢትዮጵያን መንግሥት በመቃወም ሳቢያ የኢትዮጵያን ማንነት እንደልነበረ ለማድረግ የሚጥሩ የየመንደሩ የምዕራብ ንዑስ ከበርቴ ሶሻሊስት ነን ባይ ጋዚጣዎች በርከታ ናቸው። የነሱም ጥላቻ የተመሰረተው ኢትዮጵያ ሶቪየት አቀፍ (pro Sovit) በመሆኗና ሶሻሊስታዊ መመሪያዋን ከነሱ ባለመቀበሏ ይመስላል። ሌላም ምን ማለት ይቻላል። በዚህ ጉዳይ ላይ ግን አረጋግጦ ለመፃፍ በቂ ምርምር ስላላደረግን ይህ የግላችን አስተያየት ብቻ መሆኑን ለአንባቢያን እንገልጣለን።

ከቀኝ ክንፍ ከማህል ሠፋሪ ጋዜጣዎችና ጋዜጠኞች የኢትዮጵያ ጉዳይ አቀራረብ ጋር ሲናወዳድረው አብዛኞች የምዕራብ ሶሻሊስት ጋዜጠኞችና ጋዜጣዎች በተሻለ ሚዛናዊነት ለማቅረብ ይሞክራሉ። ይሁን እንጂ ዞሮ ዞሮ ያው የምዕራብ የአተናተን ዘዴ ስለሚከተሉና ስለኢትዮጵያ ሁኔታ በቅርብ ስላላጠኑ በቁንጽል ወሬ ላይ የተመሠረተ አደገኛ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ የሚደርሱበት ጊዜ ብዙ ነው። ስለዚህም የነዚህ ጋዜጣዎች የዘወትር ኢትዮጵያን መመልከቻቸው መነጥር መልኩ ይህ ነው ብሎ ለመናገር ያዳግታል። ከምዕራቡ ዓለም የግራ ክንፍ ጋዜጣዎች ለናሙና የመረጥናቸው ኢትዮጵያ ነክ አርእስት የሚከተሉት ናቸው፤

፩ ) "Ethiopia: They Don't Have to Starve" Socialist Worker, February 1988 page 1.

፪ ) "Ethiopian Journey", The Canadian Tribune March 21, 1988., Page 6

፫ ) "Ethiopia: Famine Menace Returns, "The Guardian, April 6, 1988 Pages 10 11

እነዚህ ከላይ ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ፫ የተዘረዘሩትን አርእስት ከቀኝ ክንፍና ከማህል ሰፋሪ ጋዜጣዎች ኢትዮጵያ ነክ አርእስቶች ጋር በማስተያየት የምንመለከተው ዓይነተኛ ልዩነት አለ። ይኸውም ቀደም ሲል እንደመለከትነው የአንድ ጽሁፍ ርዕስ የሚጻፍበት ጉዳይ እምብርት ሐሳብና አልፎ አልፎም የጋዜጠኛውን አቋም መጠቆሚያ እንደመሆኑ መጠን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ሦሥት አርእስት ገና ስናነባቸው ይዘታቸው የጥላቻና የቂም መወጫ መልእክቶች አያስተላልፉም። ስለዚህም ነው እነዚህ ቢያንስ በጋዜጠኛነት ሙያ እንኳ ሚዛናዊነት (Objectivity ) እየተባለ የሚጠራውን ጉዳይ በኢትዮጵያ ሁኔታ የጠበቁ ይመስላሉ ብለን የገመትነው። ወደ ጽሁፎቹ ትንታኔ እንግባ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ሦሥት የግራ ክንፍ ጽሁፎች ውስጥ በተራ ቁጥር ፫ አንፃር የተመዘገበውን እንመልከት። ይህ ሰምንታዊ ግራ ክንፍ ጋዜጣ የሚታተመው በኒው ዮርክ ከተማ ነው። የዚህ ዘገባ ፀሐፊ ወ/ሮ ካተሪን ወትሰን (Catherne Watson) የተባሉ ጋዜጠኛ ናቸው። ጋዜጠኛዋ ጽሁፋን

ሲያዘጋጁ በኢትዮጵያ በተለይ በትግራይና በኤርትራ ሰፊ ጉብኝት አድርገዋል። ጋዜጣው ለዚህ ጽሁፍ ገጽ 10እና 11ን በሙሉ የለቀቀ ሲሆን አትኩሮቱም የድርቅን ችግር ለመቋቋም በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሴቶች ልዩ አስተዋጽኦ አጉልቶ (በስዕል ጭምር ) በማሳየት ላይ ነው። ጋዜጠኛዋ የአለም አቀፍ ቀይ መስቀልን አስተያየት በመጥቀስ በኤርትራ 100% እንዲሁም በትግራይ 75% የዘንድሮ ሰብል በድርቀት ምክንያት እንደጠፋ ጠቅሰው በጉብኝታቸው የታዘቡትን ሁሉ በአጭሩ ይዘረዝራሉ። አብሮአቸው የሚጓዘው አስጎብኝአቸው ኢትዮጵያዊ ጋር ሲወያዩ የጂረቶችን መድረቅ የተራሮቹን ደን አልባ መሆን እንደተመለከቱ ገልጠው በተለይም በሁለቱም ክፍለተ ሀገር ለረጂም ጊዜ የቆየው የፀጥታ መታወክም ጭምር ለችግሩ መባባስ አይነተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ከሐበሻው አስጎብኛቸው ቃል የሰሙትን ይጠቅሳሉ። በአበሻው አስጎብኛቸው አባባል የሰሜን ኢትዮጵያ ምድር ከ3,000 ዘመን ያላነሰ የታረሰ በመሆኑ ለሙ አፈር ተሸርሽሮና በንፋስ ተጠርጎ በሳለቀ ምድሩ አርሺ ታክቶታል።

ወ/ሮ ካተሪን በደቡብ ኤርትራ በመጓዝ ላይ ሳሉ በመንገድ አቶ ሠመረ አብርሃም የተባለውን ጎልማሳ ሐበሻ አግኝተው ያደረጉትን ጭውውት ይጠቅሳሉ። በጋዜጠኛዋ አቀራረብ አቶ ሠመረ የ40 ዓመት ጎበዝ ገበሬ ነው። በአጋጣሚም ከሱ ጋር የተገናኙት ያሉትን 8 በሬዎቹን ለመሸጥ ወደገበያ እየነዳ በመሄድ ላይ እንዳለ ነው። በዚህም ወቅት ጋዜጠኛዋ አቶ ሠመረን ለምን በሬዎቹን እንደሚሸጥ የምሬት ንግግሩን እንዳለ ያቀርቡልናል።«ምንም ምርጫ የለኝም። በዚህ ዓመት ከእርሻዬ ላይ አንድም የእህል ዘር አልበቀለበትም » ጋዜጠኛዋ በአቶ ሠመረ አነጋገር ምን ያህል ልባቸው እንደተነካ ከጽሑፋቸው ድምዳሜ መረዳት ይቻላል። እንደሳቸው አባባል አቶ ሠመረ በሮቹን ዘንድሮ በችግር ምክንያት ሸጧልና በሚቀጥለው ሰኔ ዝናብ ቢጥል እንኳ የሚያርስበት በሮች አይኖረውም።

ጋዜጠኛ ካተሪን የኢትዮጵያን ችግር በአቶ ሠመረ ተጨባጭ ሁኔታ አማካኝነት አጉልተው ካሳዩ በኃላ የምዕራብ ቀኝ ክንፍ (ኮንሰርቭቲቭና ሊበራሎቹንም ደምረው ) ጋዜጣዎች ለረሀቡ ያላቸውን የተዛባ አስተያየት ይነቅፋሉ። ወ/ሮ ካተሪን እንደሚሉት የምዕራብ ጋዜጣዎች የኢትዮጵያ ረሀብ እንዴት እንደዚህ በአጣዳፊ ይደከማል» ብለው ሕዝቡ ሆን ብሎ ቀጠሮ ሰጥቶ የጋበዘው ይመስል በብስጭት ይጽፋሉ ይላሉ «እንዳንዶቹ ደግሞ » ይላሉ ጋዜጠኛዋ «ቀድሞ የምግብ ተራድኦ ሲያደርጉ የቆዩ ለጋሶች ሁሉ የመሰላቸትና የመታከት (aid fatigue) ይታይባቸዋል ብለው ይተነብያሉ። ይህ ግን በፍጹም ያልተከሰተ ጉዳይ ነው» በማለት ጋዜጠኛዋ ጽፈዋል።(12) ቀጥለውም አንዳንድ የምዕራብ ጋዜጣዎች የኢትዮጵያን ችግር አስመልክተው የሰጡትን ስሜተቢስና ኢሰብአዊ አስተያየት በመንቀፍ ከዚህ የሚከተለውን አስተያየት ይሰነዝራሉ።

ሌሎች ብዙ (የምዕራብ) ጋዜጣዎች ይህንን አጋጣሚ (ማለት የረሀቡን ወቅት )ራሱን ሶሻሊስት ነኝ ብሎ የሚጠራውን የፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለማርያምን መንግስት የነቀፉ ውርጂብኝ ለማዥጎድጎድ ተጠቅመውበታል። በአድሀሪ አቋሙ የታወቀውና በብዙዎች ዘንድ ተነባቢነት ያለው የብሪታኒያ ታብሎይድ (Tabloid) ጋዜጣ ማለት ዘ ሰን (The Sun)(13) እየተባለ የሚታወቀው የዘንድሮውን የኢትዮጵያ ረሀብ በፕሬዚዳንት መንግስቱ እሳቦ በጣም ጉልሀና ደማቅ በሆነው ርዕሱ አማካኝነት ሰባት ሚሊዮን ለሚሆኑ እንባቢዎቹ ለኢትዮጵያ ረሀብተኞች እርዳታ እንዳይሰጡ እንዲህ ሲል ያዘቸዋል፤ «[ለኢትዮጵያ ረሀብተኞች ፍሬም] አትለግሱ»(14)

በጋዜጠኛ ከተራን አስተያየት የእነዚህ ሁሉ የምዕራብ ጋዜጣዎች ነቀፋዎች የኢትዮጵያን ከሶቪየት ሕብረት ከለመጠን መጠጋት እጥብቀው ለሚፈሩና ለሚጠሉ ምዕራባውያን ጆሮ የሚጥም ቢሆ ኑም አስተያየቶች ኢሰብአዊና ከመጠን በላይ ተገቢነት የሌላቸው ናቸው እኒሁ ጋዜጠኛ እንደሚሉት ኢትዮጵያ ከአፍሪቃ አገሮች እንኳ አሁን ባለት ሁኔታ ስትወዳደር የመነጠች ድሃ ሆና ሳለ ከምዕራቡ ዓለም ዓመታዊ የነብስ ወከፍ (per head) የልማት ድጋፍ ያገኘችው $9 የአሜሪካን ዶላር ብቻ ሲሆን ሌሎች ድሆች የአፍሪቃ አገሮች ግን በአንፃሩ የ$20 የአሜሪካን አማካኝ የነብስ ወከፍ ዓመታዊ የልማት ድጋፍ ተሰጥቶአቸዋል። ወ/ሮ ከተራን ሶሻሊስት ጋዜጠኛ ቢሆ ኑም «ሶሻሊስት ነኝ» የሚለውን የፕሬዚዳንት መንግሥቱን መንግሥት ጭ ዋነትና ሚዛናዊነት በተመለበት አግባብ ባለው መንገድ ነቅፈዋል። እንጥቀስ፤ «ከ47 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከመቶ ዘጠናው እጅ አርሶ አደር ነው። መንግስቱ ገበሬው ሰብሉን ለመንግስት ሰብል ግዥ ድርጂቶች በዝቅተኛ ተመን እንዲሸጥ በማድረግና በተለይም በገጠሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመሬት ይዞታ ለውጥ የመንደር ምስረታ ሰፈራ ማቢያ (resettlement) ወ ዘ ተ ጥንቃቄ በጎደለው ችኩልነት ተፈጽሟል። እነዚህ እርምጃዎች ተገቢነት ቢኖራቸውም አፈፃፀማቸው ግን አስጨናቂ (harsh) ነበር። »(15)

እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ ቁምነገር ጋዜጠኛዋ በሶሻሊስት እምነታቸው ላይ የተመሠረተ ድጋፍ ለፕሬዚዳንት መንግሥቱ ሳይሆን ለኢትዮጵያ አብዮት ቢሰጡም ይኸው ድጋፉቸው እንደቀኝ ክንፍ ጋዜኞች አስተያየት ፍጹም ጭፍን አይደለም። በኤርትራና በትግራይም ስለሚገኘው የወንድማማቾችና እህትማማቾች መተላለቅ ሲያብራሩ የሕዝብ እልቂትን፣ የንብረት መውደምንና ብሎም የረሀብን ችግር ማባባሱን ጭምር የሙያ ብስለትና ጨዋነት (professional ethics) በተመለበት እየየፍ አቅርበዋል። እዚህ ላይ በአጭሩ ለማለት የሞከርነው ወግ አጥባቂ ወይም ቀኝ መንገደኛ (conservative) ጋዜጦኞች የኢትዮጵያን ችግሮች በማስታከክ ለራሳቸው ስርዓት (ካፒታሊዝም)

የፕሮፖጋንዳ ትርፍ ለማስገኘት እንደሞከሩት ሁሉ ምዕራባዊ ሶሻሊስቷ ጋዜጠኛ ከተሬን ለሶሻሊዝም ድል ማንፀባረቂያ የፕሮፖጋንዳ ጥቅም ለመሸት አልፈለጉም ነው።

ከላይ ርእሱ በ (ሐ) ሥር በተራ ቁጥር ፩ አንፃር የሰፈረው ጋዜጣዊ ዘገባ ሱዛን ሸው (Susan Shaw) በተባሉ ጋዜጠኛ የተፃፍ ነው። ጋዜጣው ኃያላን መንግስታትን (ማለት ሞስኮንና ዋሽንግተንን) አዘውትሮ የሚነቅፍ የአለም አቀፍ ሶሻሊስቶች (international socialists) ልሳን ነኝ የሚል ወርሐዊ እትም ነው። ለዚህ ጥናታችን የተጠቀምንበት ዘገባ የጋዜጣውን የሽፋን ገጽ ይዞ በጉልህ ፊደሎች አማካይነት በችግር ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን በፍጹም መራብ እንደማይገባቸው በማመልከት የርሃቡን መጠን አጉልቶ ለማሳየት በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ የሚገኝ የህፃን ምስል ጨምሮ ያቀርባል።

ጋዜጠኛ ሱዛን ሸው እንደ ሌላዋ ሴት ጋዜጠኛ ከተሬን ሁሉ ጽሑፋቸው ለምዕራብ ሶሻሊስት አነባቢያቸው የኢትዮጵያን ችግር ስፋትና ጥልቀት ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት የታቀደ ነው። ጋዜጠኛዋ ሶሻሊስት ናቸውና የኢትዮጵያ ችግር ምን ያህል የዓለም ካፒታሊስት ኢኮኖሚ መዋቅርና የምራቡ የምግብ እህል ስርጭት ፖሊሲ ውጤትም ጭምር እንደሆነ በማመልከት የፖለቲካና የርእዮተዓለም ጠላቶቻቸው የሆኑትን የምዕራቡን ዓለም ቡርዧዎች መክርከማቸው አልቀረም። ፀሐፊዋ እደሚሉት በአለም ላይ ከቶ እንደ አሁን ጊዜ በምዕራቡ ዓለም የምግብ እህል የተትረፈረፈበት ጊዜ የለም። በዚህ ወቅት ግን ሰባት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በተለይ በትግራይና በኤርትራ የሚገኙ ህዝቦች በረሀብ አለንጋ መገረፍ እንደሌለባቸው መግታቸውን ለምዕራቡ ሶሻሊስት አንባቢዋቻቸው ያቀርባሉ። እኒህ ጋዜጠኛ ለዚህ አጭር ጽሑፋቸው በሰጡት ድምዳሜ አማካኝነት ለአንባቢያቻቸው ትምህርት ሲሰጡ እንዲህ ይላሉ። «ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የምዕራብ ፍርፋሪ ዳረጎት አይደለም። እነሱ (ኢትዮጵያውያን) የሚያስፈልጋቸው በቴክኖሎጂ የተራቀቁት የምዕራብ አገሮች የምግብ እህል ስርጭት ፖሊሲ ለውጥ ነው። ይሁን እንጂ ይህ በካፒታሊዝም ስር የሚሰካ ጉዳይ አይደለም፤ ምክንያቱም በዚህ ሥርዓት ገደብ የለሽ ትርፍ የማግበስበስ ፍላጎት ይህንን የፖሊሲ ለውጥ ጨርሶ አይቀበልምና ነው። ይህ ሊሰካ የሚችለው የማናቸውም ዓይነት ውጤቶች የማምረት ዓላማ የሕብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት በሆነበት በሶሻሊስታዊው ዓለም ብቻ ነው።»(16)

ለዚህ ጥናታችን ከተመለከትናቸው ግራ ክንፍ ጋዜጣዎች ውስጥ ከላይ በሐመሩ (ሐ) ሥር በተለይ በተራ ቁጥር ፪ አንፃር የሠፈረው በሰሜን አሜሪካ ከታወቁትና ነባር ከሆኑት የኮሚዩኒስት ፖርቲዎች ልሳን አንዱ የሆነው The Canadian Tribune ነው። ማንም አንባቢ እንደሚገምተው ሁሉ ይህ ፖርቲ ለሶቪየት ሕብረት የኮሚዩኒስት ፓርቲ ዓላማና አቋም ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጥ

ፓርቲ ነውና ልሳኑም ይህንኑ አቋም አዘውትሮ የሚያንፀባርቅ ይመስለል። ይኸው ጋዜጣ ከላይ በጠቀስነው እትሙ ለኢትዮጵያ አብዮት አጠቃላይ የሆነ «በዓለምአቀፋዊነት» ላይ የተመሠረተ የሚመስል ድጋፍ ኢትዮጵያ ውስጥ በተጧጧፎ በመካሄድ ላይ ባሉ የሕዝብ ትግል ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ ይሰጣል። የጋዜጣው አጠቃላይ ባህርይ ይህንኑ ይመስለል ብለን አፋችንን ሞልተን እንዳንናገር ለዚህ ጥናታችን ባጋጣሚ ካገኘነው በስተቀረ ሌሎች እትሞችን አልተመለከትንም ስለዚህም በዚህ አንድ እትም ላይ ብቻ በማትኮር አጠቃላይ የሆነ አስተያየት ከመስጠት እንቆጠባለን።

The Canadian Tribune በተለይ በMarch 21, 1988 በገጽ 6 ላይ በወጣው እትሙ በኢትዮጵያ የአንድ ዓመት የሥራ ጊዜ ያሳለፉ ባልና ሚስት፣ ዶክተር ቻርልስና ወይዘሮ ሳሊ ዴቪስ የተባሉ ግለሰቦችን በማነጋገር ሰፋ ያለ ቃለመጠይቅ አቅርቧል። በቃለ መጠይቁ በአጠቃላይ የተንፀባረቀው አስተያየት የትሪቡን ጋዜጣ ባልደረባ የምዕራብ ቀኝ ክንፍ ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን የማንቋሸሽ አቀራረብና ርእዮተዓለማዊ ፕሮፖጋንዳ ለማክሸፍ ባይቻል እንኳ ለማቻቻል (Counter balance) የታቀዱ ጥያቄዎቻቸውን በመመለስ ላይ ነው። የተጠያቂዎቹ አስተያየት በአጭሩ ከሌሎች ጋዜጦች አቀራረብ የተለየ ቀናነት( Positiveness) ያለውና ቀጥተኛከተናጋሪዎቹ አንደበት እንደፈለቀ የተፃፈ ነው። ሥፍራ ለመቆጠብ ስንል ቃለመጠየቁን እዚህ አንተረጉምም። ግለሰቦቹ የተናገሩት ሲጠቃለል የኢትዮጵያ ሕዝብ ለልማት ያለው፣ ጉጉትና ታታሪነት የሚያደንቅና አገሪቱ ግን በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት አበሳዋን በማየት ላይ የምትገኝ መሆንዋን የሚያመለክት ነው።(17)

ማጠቃለያ

የአውሮፖና የአሜሪካ (ባዕዳን) አፍሪቀኞች (Africanists) ስለአፍሪቃና ስለመላው ጥቁር ሕዝብ የሚጽፉት ታሪክ ውስጥ ብዙ የተዛቡ፣ የተጣመሙና አልፎ አልፎም በመሰሪ ጥበብ የተገደፉ ድርጊቶችና ክስተቶች መኖራቸውን በርከታ የአፍሪቃ ዘር የሆኑት (Negro) የታሪክ ሊቃውንት እየተገነዘቡት በመሄድ ላይ ናቸው። ጥቂቶችም «ፈረንጂ» ነጭ ቀለም የቀባውን የጥቁር ሕዝብ ታሪክ እውነተኛ ቀለሙንና ባህሪዩን ለመስጠት እየታገሉ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በጣም ልዩ ሥፍራ ሊሰጣቸው የሚገቡ አፍሪቃዊው የሴኔጋል ተወላጅ የታሪክ ሊቅ ሽክ አንታ ዲዮፕ (Cheik Anta Diop) ይገኙበታል። እሳቸው ከደረጉት ተጋድሎ ዋነኛው ላለፉት 180 ዓመታት ያህል የአውሮፖ የታሪክ ሊቃውንቶች የግብጽን ሥልጣኔ የነጮች ሥራ ውጤት አድርጎ ለማቅረብ የተደረገውን ረቂቅ ሴብነት በአኩሪና አንጀት አርስ ምርምሮቻቸው አማካኝነት ድል በመንሳታቸው ዛሬ የግብጽ ሥልጣኔ የጥቁር (Negroid) ሕዝብ የሥራ ውጤት ነው ብለን አፋችንን ሞልተን ወደ ምንናገርበት የታሪክ ዘመን ላይ ተሸጋግረናል። እኒህ የአፍሪቃ ሐቀኛ ልጅ ይህንን ባያደርጉ ኑሮ የእውነተኛውን የአፍሪቃ የታሪክ ቅርስ በፈጣሪነት አውሮፖውያን ሊሰለፉ

አልነበረንም? ለዚህም ነው የራሱ ታሪክ ፀሐፊ/ደራሲ የሌለው ሕዝብ ማንነቱን በትክክል የሚያቀርብበት ታሪክ የማይኖፍለት። ይህንን ለማለት የበቃነው ለዚህ ጥናት የመረመርናቸው የጋዜጣ ጽሑፎች ሁሉ በኢትዮጵያ ልጆች ቢቀርቡ ኖሮ ምንኛ በይዘታቸውና በአቀራረባቸው ከዚህ ለየት ያሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመገመት ነው። የምዕራብ ጋዜጠኞች ከቀኝ፣ ከመሐልና ከግራ ከንፍ እንፃር (Perspectives) ለየራሳቸው የርዮተዓለምና የፖለቲካ ትርፍ ለማግበስበስ ቢጥሩም በረሀብ የተጎዱ ኢትዮጵያውያን ፈጣንና ነብስ-አድን እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ በቃላት ሊገለጽ የማይችል እርዳታ የምዕራቡ ሕዝብ እንዲሰጥ ረድተዋል። ይህ የኛ ጥናት ግን ያተኮረው በዚያ ላይ ሳይሆን ኢትዮጵያ ከምዕራብ ሆነ ከምሥራቅ «የረሀብ ማስታገሽ እርዳታ» በተቀበለች ቁጥር ብሔራዊ ኩራቷንና በማጣት ረገድ የምታገባው «የውርደት» እዳ በአንድ ትውልድ ዘመን ከፍለ የማትዉርሰው መሆኑን ለመጠቆም ነው። ከሁሉም በላይ የዚህ ጥናታችንን መሠረታዊ ምክንያት የምዕራብ (ባዕዳን) ጋዜጠኞች የኢትዮጵን ረሀብ በማስታገስ ተግባር የተሸፈነ «ሰብአዊ ተልእኮ» አሳበው በዜና አቀራረባቸውና በልዩ ልዩ ዘገባቸው በእናት ሀገራችን ማህፀነ-ታሪክ ውስጥ ለዘለዓለም የማይሽር ነቀርሳ እየቀበሩና እንኳን የባዕዳንን እስተያየት ቀርቶ የእኛንም በውጭ አገር የምንገኝ አንዳንድ ልጆቿን አመለካከት እየጠመዘዙ ለአገራችንና ለማንነታችን የሚያስደነግጥ የግዴለሽነት ሁኔታ ላይ እስከምንገኝ ማድረሳቸው ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ጭምር ነው። ይህ ዓላማችን ባይሳካልንም እንኳ ይህንን ጽሁፍ ያነበቡ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ በነገሩ ለመወያየትና ለመነጋገር የሚያስችላቸው በቂ ምክንያት ከፈጠርን እንደምዕራቡ ዓለም ጋዜጠኞች የርእዮተዓለምና የፖለቲካ ሳሆን የተዳፈነ የሀገር ፍቅርን ስሜት በማካፈል ረገድ «ትርፍ አጋብሰናል» ብለን ልንኩራ እንችላለን።

ማንም ሰብአዊ ፍጡር ሊገምተው እንደሚችለው ሆዱን ሞልቶ የማያድር ሕዝብ ብሔራዊ ኩራት ሊኖረው ከቶ አይችልም። ይህንን ከቀድሞ ኩሩዎች ኢትዮጵያውያን የበለጠ የሚያውቀው ሕዝብ ያለ አይመስለንም። ባለፉት 15 ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ የረሀብ ምንጭ የፈለቀባትና የረሀብ ጎርፍ ያጥለቀለቃቸው ምውታን ምስኪኖች ከርሠመቃብር ምስል(image) ተሰጥቷት በመላው የምዕራቡ ዓለም የዜና ማሠራጫ ድርጅቶች ሲነገርላት ከርሟል። እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት 15 ዓመታት የተጎናፀፈችውን ይህንን የተመጽዋችነት ምስሏን ከመላው ዓለም ሕዝቦችና በተለይም ከራሷ ሕዝቦች እእምሮ ፍቆ ለመጪ ረስ የአንድ ትውልድ ዘመን (ከ60 እስከ 70 ዓመታት )አይበቃትም። ይህም ሊሳካ የሚችለው ተፈጥሮ (Mother nature) ፊቷን ብትመልስልንና ድርቅ በዝናብ፣ ጦርነት በሰላም መተካት የጀመረ እንደሆነ ነው።

በዛሬው የፈጣን ቴክኖሎጂ ዘመን የምዕራቡ ዓለም የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሁሉ ለገንዘብ፣ ለፖለቲካና፣ ለርእዮተዓለም ትርፍ የሚነግዱ

በመሆናቸው የቴሌቪዥን ጊዜም ሆነ የጋዜጣ ገጾች መከራያ ዋጋ በጣም ውድ ነው። በዚህም የተነሳ አንድ እውነትን አበጥሮና አንጠርጥሮ ለማቅረብ የሚፈልግ ምሁር የሥራውን ውጤት በነዚህ መገናኛ ዘዴዎች ለማቅረብ አይከጅልም። ከዚሁ ከኛ አስተያየት ጋር የተቀራረበ አስተያየት ያላቸው የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አዋቂ የሆኑት አቶ ፔሬግሪን ወርስቶን በምዕራብ ጋዜጣዎችና ቴሌቪዥኖች ሀቅን አንጥሮ ለማውጣት አይቻልም በማለት "What Journalism is" (18) በተባለው ጽሑፋቸው ያትታሉ። ከሥራቸው እንጠቅስለን፤

> «ማንኛውም እውነተኛ ጆርናሊስት በጋዜጦች ውስጥ የሚገኘው ሀቅ መጠን ምን ያህል ዝቅተኛ መሆኑን ሲገነዘብ በታላቅ ሀዘን ይመሰጣል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በተለይ ጆርናሊስቶች ሆን ብለው በመቅጠፍ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሆነው ሳይሆን ባጠቃላይ የዘመኑ (የምዕራብ) የጋዜጠኝነት ሙያ ባሀርይ እውነቱን አንጠርጥሮ ለማቅረብ የሚደረገን ጥረት ሁሉ የመግታ አዝማሚያ ስለአለው ነው። ይህ ዓይነቱ ችግር ግን እጅግ በከፋ ሁኔታ የሚታየው በቴሌቪዥን የዜና ማሰራጫ ዘገባና ትችት ፕሮግራሞች ነው።»(19)

ይህ ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ችግር በተለይ በአፍሪቃዊነታቸው ምክንያት ከተሰማቸው ግለሰቦች ውስጥ አንዱ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ዩኔስኮ) የበላይ ኃላፊ የነበሩት ሲኔጋላዊው አህማዱ መህታር እምባው ይገኙበታል። እሳቸውም የምዕራብ ዜና ማሰራጫ ድርጅቶች የአፍሪቃንና የሌሎችንም የሦስተኛው ዓለም ሁኔታ በትክክል አያንፀባርቁምና አዲስ የዓለም የዜናና የመገናኛ ሥርጭት ሥርዓት (New World Information and Communicaton Order) ተመሥርቶ የምዕራባውያን የዜና ማሠራጫዎች እንዳሻቸው የሦስተኛውን ዓለም ጉዳይ ማዳከራቸውን ማቆም አለባቸው በማለት ጥናት አቀረቡ። በጥናታቸውም ውስጥ የዚህ ዓይነት ድርጅት ካልተመሠረተ የሌሎች ድሀ አገሮች ትክክለኛ ስሜት፣ ፍላጎትና ምኞታቸው እንዲሁም እውነተኛ ማንነታቸው አይታወቅላቸውም በማለት ተከራከሩ። የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ አልዋጥላቸው ካላቸው አገሮች ውስጥ በተለይ አሜሪካና እንግሊዝ ከዩኔስኮ ድርጅት መውጣት ብቻ ሳይሆን የዩኔስኮን ድርጅት በእምብርኩ የሚያስኬደውን አሰፋሪ እርምጃ ወሰዱ። ይኸውም የድርጅቱ 30% ገቢ የነበረው መዋጮአቸውን ሲያቋርጡ እውነተኛ ለአፍሪቃና ለሌሎች የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች ተቆርቋሪ የነበሩት ግለሰብ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል አገሮች ዘንድ ታማኝነትና ተሰሚነት (Credibility) እንዳያገኙ አድርገው ስማቸውን አጠፉት። እንዲሁም በገንዘብ አባካኝነት፣ በአስተዳደር በዳይነትና፣ በሶሽሊስትነት ወነጇሏቸው። በዚህም ተጽዕኖ የተነሳ አህማዱ መህታር እምባው ለ14ዓመታት ያህል የገነቡትን ድርጅት የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ አቅርበው መሰናበት ግዴታቸው ሆነ።

እንደ አህማዱ ማህታር እምበው አፍሪቃ በምዕራብ ማሠራጫ ያች የሚሰጣት የዜና ሽፋን (Coverage) የአህጉሪቱን ትክክለኛ ሁኔታ የማያንፀባርቅ መሆኑ ያበሰጫቸው ሮበርት ፖልመር የተባሉ እንግሊዛዊው የአፍሪቃ ወዳጅ የጋዜጣኝነት ሙያ ምሁር የሚከተለውን ትዝብት የተሞላበት አስተያየታቸውን ይሰነዝራሉ።

በአውሮፖና በሰሜን አሜሪካ አህጉሮች ታላላቅ የፖለቲካ መሪዎች ከቤታቸው በወጡና በገቡ ቁጥር የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ደጃፋቸው ላይ ተኮልኩለው ይጠብቋቸዋል። እነዚህ ጋዜጠኞች ከዓመት ዓመት የፖለቲካ መሪዎቹ የተነፈሱትን ሳይቀር ይቀርፃሉ። ይህንን ሁኔታ ኬቪን ሀሚልተን የተባለው የተሌቪዥን ጋዜጠኛ ፍጹም ልዩ ከሆነው የአፍሪቃ ሁኔታ ጋር ያነፃጽረዋል። በሀሚልተን አባባል ከአፍሪቃ መሪዎች የምንሰማው አንዳች ነገር የለም። ስለአፍሪቃም ታሪክ (ሆነ የአሁኑ ይዞታ) የምንሰማው ዘገባ የውድቀት፣ የድሽቀት፣ የረሀብ ወይም የእንግሊዝ ነገስታት ጉብኝት ላይ ያተኮረ ነው። ምዕራባዊ የዜና ማሰራጫዎች የቀድሞዋ ሮዴሽያ የዛሬ ዚምባብዌነቷን ስትቀዳጅ (የነጭና ጥቁር ዘር) እልቂትና የደም መፋሰስ ተንብየው ነበር። (ይህንኑ እልቂት ለመቅረጽ ከጅለው) የጠበቁት ትንቢት አልይዝ ሲላቸው የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ከተታቸውን ቀረፃቅበው የዚምባብዌን ምድር ለቀው ወጡ። እነሆ ዛሬ አገሪቱ ነፃነቷን ከተቀዳጀች ጀምሮ ስላደረገችው የልማት እንቅስቃሴ ከምዕራባውያን ቴሌቪዥኖች የቀረበ አንዳች ነገር የለም።(20)

እኒሁ ታዋቂ የጆርናሊዝም ሙያ ምሁርና ደራሲ በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ የዜና ማሰራጫ ያች እንዴት አድርገው ሕዝባቸውን ከማደናቆር አልፎ ወደ ዓለም አቀፋዊ መሐይምነት ደረጃ እንዳወረዷቸው ሲያትቱ እንዲህ ይላሉ፤

«የምዕራብ ቴሌቪዥኖች አፍሪቃን በሚመለከት (ከደቡባዊት አፍሪቃ በስተቀር) የሚያደርጉት የዜና ሽፋን ከ1960ዓ'ም ወዲህ እጅግ በጣም እየቀነሰ ሄዷል። የምዕራቡ ዓለም የዜና ሪፖርተሮች ኢዲ አሚን የፈፀሙትን እልቂት፣እራሳቸውን ንጉሥ ብለው በሰየሙት በካሳ በዓለ-ንግስ፣ በሮዴሺያ የርስ በርስ ጦርነት፣ እንዲሁም በአፍሪቃ ቀንድ የረሀብን ሁኔታ ለመመልከት በብዛት ወደ አፍሪቃ ተልከው ነበር። ይሁን እንጂ በቴሌቪዥኖቻችን መስኮቶች የሚመጣልን የአፍሪቃ ትዕይንት ትንግርታዊው (Spectacular) ዐያፉ (Bizarre) እና ከምር አስደንጋጭ የሆነው ነው። ይህ አቀራረብ ደግሞ አፍሪቃንና አፍሪቃውያንን ዝቅ አድርጎ የመመልከት የምዕራብ ዓለም በሽታን(Stereotypes)ጭራሽ ያባብሰል። እኛ(እንግሊዛውያን) ተከታታይ የሆነ፣ የአፍሪቃን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚመለከት (Series) የአፍሪቃውያንን የእለት ከእለት ኑሮ የሚቃኝ የቴሌቪዥን

አቀራረብ አናገኝም። በዚህም የተነሳ የቢ ቢ ሲን አለም አቀፍ ከሚከታተሉት እንግሊዛዊ አድማጮች በስተቀር አልፎ አልፎ ስለአፍሪቃ በቴሌቪዥን የሚቀርቡ ለየት ያሉ (ልብ የሚነኩና አሳዛኝ) ዜናዎች ሲያዩ ሁኔታውን ከአህጉሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚያነፃጽሩበት አፍሪቃ ነክ እውቀት የላቸውም። ዛሬ በዜና ማሰራጫዎች ኃይል በጣም የተጠጋጋችው ዓለም አቀፋዊ መንደራችን (World) ውስጥ ዜናዎችን ከእንግሊዝ ቴሌቪዥን ብቻ የሚዘግነው የእንግሊዝ ሕዝብ ያለው ዓለም አቀፋዊ ጠቅላላ እውቀት በአፍሪቃ የመንደር ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚያስተምረውና የቢ ቢ ሲን አለም አቀፍ አገልግሎት ከሚያደምጠው የገጠር መምህር ያነሰ ነው። ይህ ደግሞ ታላቅ እንቆቅልሽ (irony) ነው።(21)»

እና ለመሆኑ ትላልቅ ዓለም አቀፍ የዜና ማሰራጫዎችን ልናምናቸው እንችላለን? ተብሎ ለሚጠየቅ-ጥያቄ መልሳችን «በጭራሽ አንችልም» ነው። በእርግጥ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ በዜና ማሰራጫዎች ታማኝነት ያለው ዜና ለማቅረብ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ጥበብ ውጤቶች እንደሰተለይት ግንኙነት ዓይነት ለዓይን ለማመን በሚያዳግት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ይሁንና በአቅራቢያዎቹና በዜና አዘጋጂዎቹ የግልና የቡድን እንዲሁም በዜና ማሠራጫዎች ባለቤቶችና በመንግስቶቻቸው የማይረካ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥም የተነሳ ፍጹም ከግል ጥቅም ፍላጎት ነፃ የሆነ ዜና በዛሬዋ ዓለም አገኛለሁ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው ትርፉ። ይህንን አስመልክተው በአሜሪካ የፔንሲልቫኒያ ስቴት ሴኔተር የሆኑት አቶ ሬቻርድ ኤ ስናይደር በፔንሲልቫንያ ስብሰባውን ላካሄደው የክርሺይ ሮታሪ ክበብ ባደረጉት ንግግር ቀኝ መንገደኛ (right wing) አሜሪካኖች አንኳ ከፍተኛ የዜና ማሰራጫዎችን እምነው እንዳይቀበሉ አሳስበዋል።(22) እኒሁ ግለሰብ የቴሌቪዥንን ኃይል (power) በሚመለከት በምሳሌ ደግፈው ለአድማጮቻቸው ያቀረቡት ታሪክ በጭሩ እንዲህ የሚል ነበር። ከጥቂት ዓመታት በፊት ታዋቂው አሜሪካዊ ሚሊዮኔር ኔልሰን ሮከፌለር ለኒው ዮርክ ስቴት ገዥነት ደግመው ለመመረጥ ይፈልጋሉ። ለዚሁ ጉዳይ ብለው በኒው ዮርክ አውራ ጎዳናዎች እየተዘዋወሩ ሕዝቡ እንዲመርጣቸው አላፊ አግዳሚውን እየጨበጡ በመማጠን ላይ እንዳሉ ሁኔታውን ለአሜሪካ ሕዝብ ለማቅረብ ታዋቂው ጋዜጠኛ ዴቪድ ብሪንክሊይ ፈልገው ኖሮ ከሳቸው በሸገር ቆመው ያስተውላሉ። በዚህን ጊዜ ተላላፊው ሕዝብ ለገዥነቱ በታ ምረጡኝ የሚሉትን የኒው ዮርክ ገዥውን ሮከፌለርን ትቶ ጋዜጠኛውን ዴቪድ ብሪንክሊይን እንደከበባቸው ይነገራል። ሴኔትር ሪቻርድ ስናይደር እንደሚሉት ዴቪድ ብሪንክሊይ እንዲያ ለአላፊ አግዳሚው ሕዝብ ብርቅ ሆነው የታዩበት ምክንያት ሲገልጡ እንዲህ ብለዋል። ጋዜጠኛው በየምሽቱ በቴሌቪዥኑ መስኮት እማካኝነት ወደእያንዳንዱ አሜሪካን ቤት ስለሚገቡና ታዋቂነትን ስላተረፉ ነው። ይህ የሴናተሩ ምሳሌ የሚያመለክተን

በቴሌቪዥን ተደጋግሞ የሚታይ ነገር በቀላሉ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ምን ያህል ሊያገኝ እንደሚችል ነው። እንግዲህ በዚህ መሰል ኃይለኛ መሳሪያ አማካኝነት በጠላትነት የተሞላ (hostile) አልፎ አልፎም ሐሰትና ስህተት የተደበለቀበት ዜና የሚነገርለት ኢትዮጵያ ምስል (image) በምዕራብ አንባቢ፣ ተመልካችና አድማጭ አእምሮ ውስጥ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም። የሴነተሩ ነቀፋ "ከኮንሰርቭቲቭ" አቋማቸው የመነጨ ቢሆንም የሚያሳየን አንድ እውነት አለ። ይኸውም ዘመናዊ የዜና ማሰራጫዎች አቀራረባቸው ወደፈለጉበት አቅጣጫ በመቶልመም የኃያላኑ መንግሥታት ጥቅም ማስከበሪያ ዋነኛ መሣሪያ መሆናቸውን ነው። እዚህ ልንገነዘበው የሚገባ አንድ ቁም ነገር አለ። ይኸውም የአሜሪካ ጋዜጠኞች ስለተወለዱበትና ስለአደጉበት ሕብረተሰብ በሚያቀርቡት የተሰሰተ ዜና አንዳንድ አሜሪካኖችን ስሜት ነክተው የሚያስቆጡ ከሆነ እኛማ አፍሪቃውያንን እለት በእለት በምእዕራብ ዜና ማሰራጫ ድርጅቶች ስለሚደርስብን ውርጂብኝ ምን እናውራ! በተለይም እናት አገራችን «ኮሚዩኒስት ነችና» በአፍ ጢሟ ትደፋ ብለው ከግልብ(Shallow) እውቀታቸው በመነጨ የጎሪጥ አስተያየት የሚገረምሟት ብቻ ሳይሆኑ ባልተወለደ አንጀታቸው በጭካኔ ብእር ሲያንገላቷት ምን ስሜት ይሰማን? በብእሩ ጦርነት እንዳንገጥማቸው ስለ ኢትዮጵያ ቀና የሚናገር ነገርን ሁሉ "ጃሮ ዳባ ልበስ" ብለው አያዳምጡም። እንደውነቱ ከሆነ ሰንቶቻችን በምዕራቡ ዓለም ከተሞች የምንገኝ ሐበሾች ነን አልፎ አልፎ በመኖሪያ ቤታችን ከሚኖረው የቴሌቪዥን ሳጥን ጋር (ሰው የሆነ ይመስል) «ኧረ ጉድ ነው ይኸ ልክ አደለም!» እያልን ስንሟገት የምናመሸው?!

ባጠቃላይ የምዕራብ ዓለም ጋዜጠኞች አፍሪቃን በተለይም ኢትዮጵያን በሚመለከት (ከግራም ከቀኝ እንፃር ቢጽፉ) «በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት» እንደተባለው ዓይነት የኢትዮጵያችንን እኩሪና ገናና ታሪክ ሁሉ በደርግ ላይ ባላቸው ቂም በቀል ብቻ ተነሳስተው የውብ አገራችንን መልክ በጭንቀትና በረሀብ፣ በሀዘንና በመከራ ቀለሞች በተነከረ እራፊ ሸፍነው « አስቀያሚነቷን » አጉልተው ለማሳየት ሲጥሩ በብስጭት እየበገንን «ተው ቻለው ሆዴ!» እያልን ወደየእለት «ሽቀላችን» እንሰማራለን። እንዲሁም በታሪክ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ በፍጹም የማንለያየውን ሐበሻ ሕዝቦች በገጠመን አሰዘኝ ጊዚያዊ የወንድማማቾች ፀብ ሳቢያ ጣልቃ እየገቡ ኃይለኛ የሆነውን የብዕር መሣሪያ በመጠቀም ይበልጥ እንድንለያይና በመከከላችን የዘወትር ጥላቻ እንዲሰፍን ሲያደርጉ እናየዋለን። ይሁን እንጂ ይህ ድርጊታቸው ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን አፍሪቃውያንና ድፍን ጥቁር ሕዝቦችን ለማጥቃት የተነሰነሰ መርዝ መሆኑን የምንገነዘብበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ አለን። እኒህ የምዕራብ ጋዜጦች የአፍሪቃን ሕዝብ ታሪክ በማጥ ጭቃ ውስጥ ደለው ቢረመርሙም ይህ ድርጊታቸው እንደእሳት የሚያንገበግባቸው ሀቀኛ ልጆቿ ታሪኳን መልሰው ንጹህ ለማድረግ እስከ ዛሬ ያጠፉትን ጊዜ ያህል

እንደማይወሰዱም እንጠራጠርም። በተለይም እናት ኢትዮጵያችንን በሚመለከት በአገር ቤትም ሆነ በስደት ላይ ያለነው ልጆቿ የሚሰማንን የስሜት አንድነት አበው ባወረሱን አፍአዊ (oral literature) እንጉርጉሮ እየታገዝን እንደምንተባበር ያለንን ምኞት በመግለጥ ሐተታችንን እዚህ ላይ እንደመድማለን።

«...አገራችን ታማ ተኝታ ባልጋ ላይ ፤
ወዴት እንሄዳለን ሞት ሸረቷን ሳናይ!?...»

# የግርጌ ማስታዎሻዎች

1. Encyclopedia Britannica, 1983, P . 1006
2. Rodney, Walter, How Europe Underdeveloped Africa, 1976, P. 265.
3. Gitlin, T. The Whole World's Watching, Berkeley; University of California Press, 1980.
4. Gans, H. Deciding What's New. New York: Vintage Books, 1980 ; Tuchman, G . Making News. New York; Free Press, 1978.

5. በርካታ የአሜሪካን አንባቢዎች ይህንን ጋዜጣ በሊበራልነት ይመድቡታል ። እኛ ግን የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚተነትነው መልኩና በፀረ-ኢትዮጵያ ባህርዩ በፀግ-አጥባቂነት ለዚህ ሐተታ መድበነዋል።
6. በዚህ ርእሰ ስር ግራ-ዘመም (left – leaning) የሆኑ የሠራተኛ ማህበር የሶሻሊስት ፖርቲዎች የኮሚኒስት ፖርቲዎችናእንዲሁም በግል የተቋቋሙ «ራዲካል» ቡድኖች ጋዜጣዎችና መጽሔቶች ሊካተቱ ይቻላል።
7. እዚህ ላይ የጋዜጠኝነትና የሥነጽሑፍ ሙያ እንግዳ ለሚሆንባቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን አንድ ነገር በቅድሚያ ማዝከር እንወዳለን። ይኸውም በጋዜጠኝነት ሙያ የአንድ ጽሑፍ ርዕሱ የሥነጽሑፍ አምብርት መባሉንና ቃላቱም ለማጥቃትም ሆነ ለመደገፍ ታቅደው በከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚመረጡ ነው። በተጨማሪም አንባቢዎች ሁሉ በጋዜጣ ላይ የተፃፈውን አንብበው ለመጨረስ ጊዜ ስለሚያጥራቸው የርእሱ አመራረጥ ጊዜ ለሌለው አንባቢ በቂ የሆነ ፍንጭ ስለነገሩ እንዲሰጥ ሆኖ ይታቀዳል። እዚህ ላይ አርእስቱ ደራሲው ሊጽፍበት የቃጣው ዋነኛ ሐሳብ መነሻ ነው ብሎ መደንገጉም ሳይጠቅም አይቀርም። አንዳንድ ጊዜ የአርእስቱ ይዘት የደራሲውን አቋምና የጽሑፍን አቅጣጫ ይጠቁመናል። ዜናው ሥዕል ሲጨመርበት ደግሞ ነገሩን ይበልጥ ያጠናክረዋል። ከ10 ሺህ ቃላት ድርሰት አንድ ሥዕል ማውጣት የአንባቢውንም ሆነ የደራሲውን ጊዜ ከመቆጠቡም በላይ ነገሩን 10 ሺህ ጊዜ ያጎላዋል።
8. ለትምህርት ወደ ሶቪየት ሕብረትም ሆነ ወደ ምዕራብ አውሮፖ የሚላኩ አፍሪቃውያን ወጣቶች ተመሳሳይ የሆነ የዘር መድልዎ እንደሚደርስባቸው The New African እየተባለ የሚጠራ መጽሔት አራት ገጽ ሐተታ በApril 1988 እትም አውጥቷል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በሶቪየት ሕብረት በመማር ላይ የሚገኙ አፍሪቃውያንን እስተያየት በመጥቀስ ደራሲው ለማመን የሚያዳግቱ ታሪኮች ሁሉ ይነግሩናል። ጽሑፉ እንደሚለው «የሶቪየት ሕብረት ሥርዓተ ትምህርት የአፍሪቃን ፍላጎት ለማሟላት ታቅዶ የተዋቀረ ባለመሆኑ ከባድ ውዥንብር ይፈጥራል።» በሶቪየት ሕብረት ስላለው (ከምዕራብ አውሮፖና ከአሜሪካ ያልተለየ ዘረኝነት ሲተነትኑ ቀጥሎ የተመለከትነውን የመሰለ መሪር አነጋገር ከወጣት አፍሪቃውያን ይጠቅሳሉ። « በመጀመሪያ [እኛን አፍሪቃውያንን] ዝንጀሮዎች እሉን' እለ እንዱ ተማሪ። ' አሁን ደግሞ ኤይድስ [ናችሁ] ይሉናል። በመጀመሪያ ወደ ሶቪየት ሕብረት እንደመጣሁ እንዲህ ያለው ዘለፋ ስሚቴን በኃይል ስለሚጎዳው በጣም እናደድ ነበር። አሁን ግን ነገሩን ለምጄው [ብዙም አልበሳጭም።] (ለዚህ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት The New African የApril 1988 እትም ከገጽ 24-27 ይመልከቱ)
9. አቶ ሌሪ ብራውን (Larry Brown) የተባሉ የሀርቫርድ ዮንቨርሲቲ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ፕሮፌሰር በፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን ዘመን የታየው የአሜሪካ ኢኮኖሚያዊ እድገት « 20 ሚሊዮን ለሚሆኑ አሜሪካውያን ረሀብተኞች» ምንም ፋይዳ እንዳልሰጠ በስጡት

መግለጫ ነው። በዚሁ መግለጫቸው ፕሮፌሰር ሴሪ አንዳንድ ቤተሰቦች «በቀን ከአንድ ምግብ የበለጠ እንደማይበሉና» አንዳንዶቹም « በአንድ ምግብ ብቻ ለጥቂት ቀናት እንደሚቆዩ አመልክተው የዚህም ጦስ ምንጭ እልፎ እልፎ «ሬገኖሚክስ» እየተባለ የሚጠራው ሳለው ይበልጥ የሚሰጠው የፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ነው ይላሉ። (ለዚህ "20 Million Americans Hungry Task Force Blames Reaganomics" The Toronto Star) October 27, 1987, P. A 3 ይመልከቱ)። ታዲያ «ዘረኝነትና ችግር የለብንም በሚሉ ካናዳውያን ዘንድም በቶሮንቶ ከተማ ብቻ ከ 60,000 ያላነሱ ረሀብተኞችና በርካታ በረንዳ አዳሪዎች መኖራቸው እልፎ እልፎ በዚያው ከተማ ከሚኖሩ ግለሰቦችና ከልዩ ልዩ ዘገባዎች መረዳት ይቻላል።

10. በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልግዎ ከሆነ የተስፋጽዮን መድኅኔን መጽሐፍ Eritrea: Dynamics of a National Question (1986) ይመልከቱ። የኢፒ ኤል ኤፍ ድርጅትም ዛሬ እንደቀድሞው ሶሻሊስት አለመሆኑንና በማርክሲዝም የማያምን መሆኑን በራሱ የህቡዕ ሬዲዮ ጣቢያ በሰጠው መግለጫ ያብራራል። በዚህ ሐተታ ውስጥም በቅርቡ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን የሶቪት ኅብረትን መሪ አቶ ሚኸኤል ጐርባቾቭን ሞስኮ ሲያናግሩ እንዲ አጀንዳቸው የኤርትራ ጉዳይ መሆኑ እንደታለቅ ድል ጠቅሶታል። በእኛ የግል አስተያየት ግን ኃያላን መንግሥታት የችግሩ አካል እንጂ የመፍትሔ መስጫው ወገን ባለመሆናቸው የነሱ በእኛ ጉዳይ ላይ መነጋገር እንደታለቅ ድል ሆኖ መታየት የለበትም። በታሪክም የምንረዳው የአውሮፖ ኃያላን መንግሥታትና ኰሎኒያሊስቶች የአፍሪቃን ችግር አመንጭዎች እንጂ ፈቺዎች ሆነው ያገኘንበት ምዕራፍ የለም። ለአፍሪቃ ችግር መፍትሔ ሰጪዎቹ እኛው አፍሪቃውያን በለሆንን ለሕዝቦቻችን ሰላማዊ ሕይወት የምንመሰርትበት ሁኔታ ላይ በማትኮር ፊታችንን ከጦርነት ወደ ሰላም ብንመልስ ይሻል ይመስለናል።

መረጃውን ለማግኘት «Rebel Radio Notes Superpower's Role in Eritrea» የቀሰኘው ጽሑፍ በ Daily News Report Sub- Saharan Africa(FBIS-AFR-88-092) በተለይ በገጽ 2 አንቀጽ 2 ከመስመር ስድስት ጀምሮ ይመልከቱ።

11. ይህንን ጥቅስ ከ The Toronto Star በMarch 24, 1988 በገጽ A 26 ላይ ወስደን የተረጎምነው ነው።

12. The Guardian April 6, 1988, p. 10.

13. ሌላው በሰሜን አሜሪካ ዘ ሰን (The Sun) ተብለው ከሚታወቁ ጋዜጦች ውስጥ አንዱ ቶሮንቶ በሚባለው የካናዳ ከፍተኛ ከተማ የሚታተመው ነው። ይህ (The Toronto Sun) ጋዜጣ በብዙ የካናዳ ነዋሪዎች ጥቁሮችና በሌሎችም ነጭ ያልሆኑ ማህበረሰቦች ሁሉ ከሦስተኛው ዓለም ወደ ካናዳ ለሚመጡ ጥቁሮችና ሌሎች ነጭ ያልሆኑ ወገኖች «እሚግራንቶች» ሁሉ በጎ አስተያየት የሌለው «ዘረኛ» ጋዜጣ ነው እየተባለ ይነገርለታል። ይህ ከእንግሊዝ አገሩ ታብሎይድ The Sun ጋር በአየናፍና በወግ-አጥባቂ አቋሙ የሚወዳደረው ጋዜጣ የረጅም ጊዜ አዘጋጅ የነበሩት ግለሰብ አቶ ፒተር ወርቲንግተን (Peter Worthington) ስደተኛ የሚታወቁ ወደ ካናዳ ነጭ ያልሆነ (በተለይ አፍሪካዊ ጥቁር) እሚግራንት እንዳይመጣ ከሚከላከሉ የቀኝ አክራሪ (ለምሳሌ በአሜሪካ እንደ አርያን ሬስ (Aryan race) ነን የሚሉ ዓይነቶች) ቡድኖች ጋር በመተባበር ለመሥራታቸው ሌሎች ፀሐፊዎችና ጋዜጣዎች የመሰከሩባቸው ግለሰብ ናቸው። እኒሁ ፒተር ወርቲንግተን የተባሉ ለጥቁር ዘር ሁሉ ንቀት ጥላቻና ፋሽስታዊ አመለካከት ያላቸው ግለሰብ ጋዜጠኛ ለመሆናቸው ዋነኛው ምስክሩ በመላው ዓለም የተጠላውን የደቡብ አፍሪቃ (Apartheid) አገዛዝ መንግሥት የበላይነት ለማስጠበቅ ከሚታገሉ የሰሜን አሜሪካ ዘረኛ ድርጅቶች ጋር አብሮ በመሥራት አስተዋጽዖ ማድረጋቸው ነው። የጥቂት

ነጮች አገዛዝ (Apartheid) በሃያ አራት ሚሊዮን ደቡብ አፍሪቃውያን ወንድሞቻችን ጫንቃ ላይ ለዘለዓለም እንደተጫነ እንዲኖር በሰሜን አሜሪካ የሚታገሉት አቶ ፒተር ወርቲንግተን የደቡብ አፍሪቃ ወንድሞቻችንን የነፃነት እንቅስቃሴ እንደ ተራ የሽብር እንቅስቃሴ ለማስመሰል ርእሱ "The A.N.C. Method: Violence" የተሰኘ የ25 ደቂቃ የፕሮፖጋንዳ ቪዲዮ የደቡብ አፍሪቃው ነጭ ፕሬዚዳንት የፒ ደብሊው ቦታ ቀኝ እጅ በመሆን ባለፈው ዓመት አውጥተው በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ። የፒተር ወርቲንግተን ፀረ የደቡብ አፍሪቃ ጥቁር ሕዝብ ትግል ቪዲዮ በሰሜን አሜሪካ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ በሚገኙ ፀረ አፖርታይድ ኮሚቴዎችና ግለሰቦች ታውቆላቸዋል። ለፒተር ወርቲንግተን የአፍሪቃና ለመሰለው የጥቁር ሕዝብ ጠላትነት ከዚህ የተሻለ ቀዋሚ ምስክር ሊገኝ አይችልም።

የፒተር ወርቲንግተን ፀረ ጥቁር ሕዝብ ቪድዮ ከ70 ዓመታት በላይ የነጮችን የበላይነትና ቅኝ ገዥነት አልቀበልም ብሎ የተነሳውን አፍሪካን ናሽናል ኮንግሬስ (A.N.C) ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄ እንደወንጀለኞች ቡድን አድርጎ ያቀርበዋል። በፒተር ወርቲንግተን የቪዲዮ አቀራረብ በደቡብ አፍሪቃ ዛሬ ያው ፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ወርቲንግተን የቪዲዮ ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ያሉት ጥቂት ነጮች ሳይሆኑ ኤ ኤን ሲ (A.N.C) የተባለው የነፃ አውጭ ድርጅት ነው። ፒተር ወርቲንግተን የነጭ ውሸት ቀልቀላ ነፈ ጋዜጠኛ ለመሆናቸው ከዚህ የተሻለ ማስረጃ ከቶ ከየት ይገኛል። አቀራረባቸው ውስጥ በንገባ እጅግ «አማተሪሽ» በሆነው የቪዲዮ ፊልም ጥበባቸው በመመራት ታዋቂውንና መላ እድሜአቸውን ለደቡብ አፍሪቃ ጥቁሮች ነፃ መውጣት መስዋዕት ያደረጉትን የአንጋፋውን መሪ የኔልሰን ማንዴላን ባልንጀራና የትግል ጓድ አቶ ኦሊቨር ታምቦን በምዕራብ ዓለም የዜና ማሠራጫዎች እንዲጠሉ ከተፈረደባቸው ከሊቢያው መሪ ምአመር ጋዳፊና ከፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅት መሪ ከያሲር አረፋት ጋር ያቀርቧቸዋል። በፒተር ወርቲንግተን ቤት የፕሬዚዳንት ኦሊቨር ታምቦ ምስል ከነዚህ ከምዕራቡ ዓለም «እጅግ ከተጠሉ » ሰዎች ጋር በረጋ ሥራሽ ጥበባቸው ተቀምሮ ቀረበና ኦሊቨር ታምቦ ሊጠሉ ነው። ለአንድ የምእራብ አገር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅነት የበቃ ሰው እHከዚህ ድረስ በዘር ጥላቻ የተጨማለቀ ተራ ድርጊት የሚሰራ ሆኖ ሲገኝ ስንቶች የምዕራብ ጋዜጠኞች ከዚህ ነፃ ናቸው ብሎ የመገረም ጥያቄ ማንሳት የብልህ አንባቢ የዘወትር ተግባሩ ነው።

ይህ የፒተር ወርቲንግተን አፓርታይድ ደጋፊና የደቡብ አፍሪቃንና የመሰለው ጥቁርን ሕዝብ የሚያናንቀው ቪዲዮ አሁንም በሰሜን አሜሪካ C-FAR (Citizens For Foerign Aid Reform) በሚባል በካናዳ በታወቀው ድርጅት አማካኝነት በመሰራጨት ላይ ይገኛል። ይህ ድርጅት እንደስሙ ለሦስተኛው ዓለም የተሻለ እርዳታ ለማስገኘት የሚታገል ይመስላል። ዓላማው ግን በሦስተኛው ዓለም እርዳታ መሰጠት ያለበት ቀኝ አክራሪ የፖለቲካ ፍልስፍና የሚከተሉ መንግሥታት በተቋቋመበት አከባቢ ብቻ እንዲሆንና እንዲሁም እንደኢትዮጵያ፣ አንጎላና ሞዛምቢክ ያሉ አገሮች ከምዕራቡ ዓለም ሰብዓዊ እርዳታ ጭምር እንዳያገኙ በምዕራብ መንግሥታት ዘንድ ቅስቀሳ (Lobby) ማድረግ ነው። የዚሁ የC-FAR ሌላው ዋነኛ ተግባር በካናዳም ሆነ በሰሜን አሜሪካ ነጭ ያልሆኑ (Non-white) የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች (ከአፍሪቃ፣ ከእስያ፣ ከላቲን አሜሪካ) የኢሚግራትነት (የስደተኝነት) እድል እንዳያገኙ መከላከልና ጨርሶ እንዲነፈጋቸው መታገል ነው። ይህ ድርጅት ታዲያ በመሰለው አሜሪካ ወአፀያፌ ዘረኛ ተግባራቸው ከታወቀት «ኩ ክለክስ ክላን» ጋር በተግባር የሚመሳሰል ካናዳዊ (ሰሜን አሜሪካዊ) ድርጅት አይደለምን? በዚህ የግርጌ ማስታወሻ ላይ ስለቀረበው ሐተታ ተጨማሪ መረጃ ከስፈለገዎ ቀጥሎ የምንጠቅሰውን ጽሑፍ ይመልከቱ። "Helping to wage propaganda war for south africa." The Toronto Star, May 18, 1988, P.A26.

እነሆ በጥቁር ሕዝብ ጥላቻቸውና በአፓርታይድ ሥርዓት ደጋፊነታቸው የታወቁት ፒተር ወርቲንግተን (Peter Worthington) እኛ አፍሪቃውያን ማንነታቸውን ደህና አድርገን የማናውቀው ይመስል ፤ እኒሁ በካናዳና በአሜሪካ የሚኖሩ ጥቁርና ጠይም ሕዝቦች እንደጥራቅ ለሚፈሩዋቸው ዘረኛ ድርጅቶች ተግባራዊ አገልግሎት ለሚሰጡ ጋዜጠኛ በአፍሪቃ ቀንድ በኩል ለሚገኘው ችግር የወንድማማቾችን አሰዘኝ መተሳሰቅ ለማስቆም ሳይሆን ለምዕራቡ ዓለም የርዕዮተ-ዓለምና የፖለቲካ መረገጫ መሬት የቀረቀሩ መስሏቸው የኢትዮጵያን ችግር እንዳሻቸው በማዳከር ጽፈዋል። ዘር ዘር ለመለው ጥቁር ሕዝብ ደንታ የሌላቸውና ጥላቻ ያላቸው መሆኑን ከካናዳው ድርጊታቸውና ደቡብ አፍሪቃን ከሚመለከተው ቪዲዮአቸው እንረዳለንና በኢትዮጵያ ጉዳይ ማልቃ ለመግባት የሞከሩት በዚያ ለሚኖሩት ጥቁር ሕዝቦች ልዩ የርህራሄ ልቦና በቀደ ጥገና ገብቶላቸው ሳይሆን በኤርትራ ችግር በረሀብ ሁኔታ አስታከው ያላቸውን የከረረ ፀረ-ቦሸሊስት ጥላቻ በኢትዮጵያ ላይ ለማውረድ ብለው ነው። በአፃፃፋቸው ይዘትም የፀረ ኮሙኒስት ውቃቢአቸው ነግሮአቸው የፃፉት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እውነትም ለአፍሪቃ ቀንድ ጥቁር ሕዝብ የሚያዝኑ ከሆነ ኤርትራን ብቻ ሳይሆን ለምን ሌላውን የኢትዮጵያን ክፍል እንዲሁም ሶማሊያን ጭምር ጎብኝተው አይጽፉም ነበር? የኤርትራ ጉብኝታቸው ለአቋማቸውና ለርዕዮተ ዓለም ትግላቸው የተቃጣ እንጅ ለእውነተኛ (objective) ጋዜጠኝነት አለመሆኑ በጽሑፋቸው አማካኝነት ደስታቸውን እንዲህ በማለት ያበስሩልናል። «ዛሬ ከበፊቱ ይበልጥ በኢ.ፒ. ኤል ኤፍ ዘንድ ማርክሳዊ ባህሪይ አላየሁም።» (ለዚህ ጽሑፍ ማረጋገጫ The Toronto Sun,April 25, 1988, p. 36 ይመልከቱ። በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ትንታኔ ለማግኘት በተሰፋጽዮን መድኅኔ Tesfatsion Medhanie ደራሲነት የተፃፈውን Eritea: Dynamics of a National Question የተሰኘውን መጽሐፍ ያገላብጡ።

ጋዜጠኛ ፒተር ወርቲንግተን በኢ.ፒ. ኤል ኤፍ ቁጥጥር ስር ያለውን የኤርትራን ክፍልና ሱዳንን ጎብኝተው በእየለቱ ከአንድ እስከ ሁለት ሙሉ የጋዜጣ ገጾች በመጠቀም በተከታታይ (series) ለአምስት ቀኖች ከአፕሪል 24 ቀን 1988 እስከ አፕሪል 28 ቀን, 1988 ጽፈዋል። የጽሑፋቸው የመጨረሻው ክፍል (ማለት April 28, 1988) በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም ላይ መፈንቅለ መንግሥት እንደሚካሄድ ብቻ ሳይሆን እንዲካሄድ ተማጽኖአል። በእኛ በጽሑፎች አስተያየት እንኳን አንድ ኮሎኔል አስር ኮሎኔል መንግሥቱን ቢፈነቅሉ ማን ቅር ይለዋል። ኢትዮጵያን ግን ልታፈርሷት አትችሉም ነው እኛ የምንለው።ለኤርትራ ችግር የኮሎኔል መንግሥቱ መፈንቀል መፍትሔ አይሆንም እንጂ ከሆነማ እሰየው ያርግላችሁ እንላለን። የእኛ ምኞት ኢትዮጵያ በዲሞክራሲያዊ አመራር የተገነባ መንግሥት ተፈጥሮ ልጆቿ በሰላምና በደስታ እንዲኖሩ ነው። ፒተር ወርቲንግተን ግን ለኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም መፈንቅለ አገዛዝ (ብሎም ሞት) በተመኙበት እንደበታቸው ለደቡብ አፍሪቃ የነጮች ጨቋኝ (አፓርታይድ) መሪ ለፒ ደብሊው ቦታ አገዛዝ ለዘላለም ዕድሜ የሚመኙበት ቪዲዮ መቅረፃቸው አስገራሚ ብቻ ሳይሆን ደካማ ዘረኛ ሰው መሆናቸውን አጋለጡ። ጥቁር ይጠላሉና ለኤርትራ ህዝብ አቀረቀራለሁ ቢሉ ማን ያምናቸዋል!!

14. "Ethiopia:Famine Menace Returns" The Guardian. April 6, 1988, ገጽ 10ና 11 ይመልከቱ
15. እንደላይኛው።
16. ይህ ጥቅስ የተወሰደውና የተተረጎመው ከ Socialist Worker No.133, February 1988, p. 1 ላይ ነው።
17. ለተጨማሪ ማብራሪያ «Ethiopian Journey» የተባለውን ጽሑፍ ከ The Canadian Tribune, March 21, 1988, Page 6. ይመልከቱ።

18. Peregrine Worsthorn, "What Journalism is ከ Time & Tide, Winter 1988, P. 60 ይመልከቱ።
19. እንደሳይኛው።
20. ለዚህ ማስረጃ Robin Palmer የፃፉትን "Africa in the Media" የተባለው ጽሑፍ ከAfrican Affairs ቅጽ 86 ቁጥር 343 የኤፕሪል 1987 እትም በገጽ 246 የመልከቱ።
21. እንደሳይኛው ገጽ 247
22. Richard A. Snyder, "Can We Trust the big media is our news free of bias?" in vital speeches of the day, vol. 58, No 6, January 1, 1985, p. 171
23. ከዚህ አነጋገር የምንማረው ጉዳይ ማንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚጽፍ ጋዜጠኛ ቢያንስ ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪቃ ሕዝቦች ባህል፣ አኗኗር፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና አፍሪቃን ዛሬ የፊጥኝ አሥር የያዛት ድህነት ዋነኛ ምንጩ ምን እንደሆነ ከነመፍትሔው ጥምር የሚያሳውቃቸው የታሪክ፣ የሰስዮሎጂ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ እውቀት እንደሚያስፈልጋቸው ነው። በምዕራብ ባህልና አመለካከት (Value) ያደገ ግለሰብ «ጋዜጠኛ» ስለተባለ ብቻ የአፍሪቃን ትክክለኛ ማንነትና ገጽታ ያቀርባል ብሎ መጠበቅ «ሰማይ በደር ሲታረስ ለማየት እንደመጠበቅ» ያለ ከንቱ ምኞት ነው። ለማያከብሩት ሕዝብየተከበረ ድርሰት ያቀረቡ ደራሲዎች እስካሁን አላጋጠመንምና!

# ሰላም በኤርትራ

ከዶክተር ያዕቆብ ሀይለማርያም

## (1) መግቢያ

በንኩል አስተዳደር ከተፈጥሮ ሁኔታዎች መበላሸት ጋር በመተባበር ዛሬ አገራችን የጦርነት ማሰ፣ የጠኔ ዋሻ አድርጎአት ከዓለም ሕብረተ ሰብ በብልጽግናና በኑሮ ደረጃ የመጨረሻውን ደረጃ ይዛ ትገኛለች። በራስዋ ተማምና በተራራዎችዋ ተከልላ፤ በጀግኖችዋ ተጠብቃ፤ መብቷንና ጥቅሟን አስጠብቃ ያልኖረችውን ያህል ዛሬ ኢትዮጵያ በምንና በምን የዓለም መድረኮችና ሸንጎዎች እንደምትገኝና፤ እንዲሁም በዓለም ሕብረተ ሰብ ዝናና አድናቆት ባተረፈችበት በኦሊምፒክ ውድድሮች ትሳተፍ አትሳተፍ ወሰኝዋ በአለፈው ሰሽየት ሕብረት ስትሆን ዛሬ ደግሞ ሰሜን ኮርያ ሆናለች። እንደዛሬ እያድርገውና ጣሊያኖች በማጭበርበር በ1889[1] ዓ.ም የተፈረመው የውጫሌን ውል ለውጠው «ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነትዋ በኢጣሊያ በኩል ታከናውናለች» የሚል አንቀጽ በመጨመራቸው የአገራቸው ልዕልናና ክብራቸውን ለማስጠበቅና ለማስከበር የትናንት በስቲያ ኢትዮጵያውያን በ1896 ዓ.ም ጦርነት አንስተው በዘመናዊ ትጥቅ የተሰለፈውን የጣልያ ጦር ድባቅ በመምታት ከአኒባል ወዲህ ለመላው የጥቁር ዘርና ለነፃነታቸው ታጋዮች ሁሉ መመኪያ የሆነ አንድ ትልቅ ገድል በታሪክ ማስመዝገባቸው ሰንገነዘብ ሰለዛሬዎቹ መሪዎች «የነብር ጭንጋፍ አነር» ያሉትን የአበቶችን ተረት ያስታውሰናል።

ገበናችንን ለባዕድ ሰንገልጥ፣ በወዳጆቻችን ተከብረን፣ በጠላቶቻችን ታፍረን፣ ድህነታችንን ችለን ያልኖርነውን ያህል ዛሬ አንጀታቸውን ከአጥንታቸው ጋር ተጣብቆ መለውን ዓለም ያስለቀሱ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ለረሃብ ቋሚ ምልክት ሆነው በቴሌቪዥንና በሬድዮ የበለጌ መሰለቂያ አድማጩን ማሰቂያ ሆነዋል።

አገራችን ለምትገኝበት ለእነዚህና ለሌሎችም ብዙ አሰቃቂ ሁኔታዎችና ብሔራዊ ውርደቶች ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም፤ የብሔሮች ውዝግቦችና የእርስ በርስ ጦርነቶች በተለይም በኤርትራ የሚካሄደው ከአንጋፋዎቹ ምክንያቶች አንዱ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ስለ ኤርትራ ችግር ያለኝን አስተያየትና ለችግሩ የሚመስለኝም መፍትሔ በጽሑፍ ሳቀርብ ያሰሰኝ በኤርትራውያን ሊቃውንትም ሆነ በሌሎችም ያልተዘከረ ልዩ ሃሳብ አቀርባለሁ በዬ ሰይሆን፣ የኤርትራ ጉዳይ በመፈራራት፤ በመከባበር፣ የአንዱን ወገን ስሜት እጎዳለሁ በማለት ሃሳባቸውን ያልሰነዘሩ ስለ ኤርትራ ችግር መፍትሔ ቅን ሃሳብ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ለግልጽ ውይይት፣ ለክርክር፣ ብሎም መፍትሔ መሰሎ

የሚታያቸውን ሃሳብ በግልጽና ባለማመንታት እንዲሰነዝሩ ለመጋበዝ ነው። ስለብሔሮች ጉዳይ፣ ስለ ኤርትራ፣ ወይንም በጠቅላላው ስለኢትዮጵያ የግዛት አንድነትም ሆነ መነጣጠል መጻፍ ወይንም መደገፍ ወይንም መንቀፍ «ጠባብ ብሔርተኛ፣ «ትምክህተኛ» ወይንም «ጎበና» የሚል ስም የሚያሰጥ ቢሆንም ይህንን ከንቱ ትችት በመፍራት ሃሳብን ማመቅ አይገባም። አንዳንድ እራሳቸው ምንም ሳያበረክቱ መንቀፍ ብቻ የሚቀናቸው አፍራሾች እንዲህ ዓይነቱ ውይይት የስደተኞች «ምን ልሥራ» ባይነት ነው ብለው ይቆጥሩት ይሆናል። ከአሜሪካ ሆኖ ስለ ኤርትራ ችግር መወያየት በመሠረቱ የተሟላ ሊሆን ባይቻልም አንድ ሃሳብ ከየትም ይመንጭ ከየትም ተፈጻሚነት የሚኖረው በብዙዎቹ ድጋፍ ሲኖረው እንደመሆኑ መጠን የኤርትራም ግምባሮች መሪዎች የኢትዮጵያውያን ስሜትና አስተያየት በየጊዜው እንደሚለኩትና እንደሚያዳምጡ ስለማያጠራጥር የሚቀርበው ሃሳብና ትችት ቀጥተኛና የተባ ውጤት ሊኖረው ይችላል።

እንዲሁም ዛሬ በፋርስና በኢራቅ፣ በምዕራብ ሰሐራና በሞሮኮ፣ በአን ጉላና በዘረኛዋ ደቡብ አፍሪቃ፣ በአፍጋኒስታን መንግሥትና ሙጃ ሽዲን፣ በሳንዲኒስታና በኮንትራዎች፣ በሰሜንና በደቡብ ኮርያ፣ በሱዳን መንግሥትና በሱዳን ነፃ አውጪ ድርጅት፣ ወዘተ የቆዩ ውዝግቦች በሰላም ለመፍታት የሰላም ጭላንጭል በታየበት በዛሬው ወቅት፤ እንዲሁም በአገራችን ቀጥተኛና የተባ ውጤትና ተጽእኖ በሚኖረው ሶቭየት ሕብረት «በግላሰኖስት» አማካኝነት ለመሠረታዊ ለውጥ እሰፍሰፋ በምትገኝበት በዛሬው ጊዜ የአገራችን ዋነኛ ጭንቀት አንስቶ መወያየት ወቅታዊ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ከ27 ዓመታት እልቂት በኋላ ጦርነቱ ምንም ውጤት አለማምጣቱ የተገነዘቡ ኢትዮጵያውያን፣ እንዲሁም ቀደም ሲል በመርሆ ደረጃ እንኳን የኤርትራን ነፃነት ይደግፉ የነበሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ ግምባሮች መሪዎች ጋር በነበራቸው የሸከረ ግንኙነት ምክንያት ዛሬ አቋማቸውን ቀይረው የኤርትራ ነፃነት በመርሆ ደረጃ እንኳን ስለሚቃወሙ የዚህ ውይይት አስፈላጊነቱ ጉልህ ያደርገዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ የበሰለና የሞቀ ክርክርና ትችት ማካሄዱ ለሁለቱም ወገኖች ጠቃሚነቱ ግልጽ ነው።

ከዛሬ 18 ዓመታት በፊት ጀምሮ እስከዛሬ የቀኙ አክራሪዎች «አንድነት ወይንም ሞት» [2] ወይንም የግራ ተስፈንጣሪዎች «ማንኛውም የብሔር ውዝግብ በመገንጠል ይፈታል» በማለት ለ18 ዓመታት የተመላለስንባቸው አሮጌ ጎዳናዎችን ትተን በ27 ዓመታት ጦርነት ተመክሮ ላይ የተመረኮዘ ውይይት ብናካሄድ የበለጠ ጠቃሚ እንደሚሆን ግልጽ ነው። የብሔሮች ጥያቄ ውይይት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲነሳ [3] የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ያልተመረኮዘ፤ በአንድ ፎርሙላ ላይ ብቻ የተወሰነ ስለነበረ ውጤት አላመጣም፣ ውይይቱም አልተስፋፋም። እንዲሁም የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕብረትና አንድነት ለሁለቱም ብልጽግናና እድገት የሚበጅ፤ የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር

መቆየት የሁለቱም ሕልውና ጥያቄ መሆኑን፤ የኤርትራ መገንጠል የኢትዮጵያን አንገት እንደመቁረጥ ይሆናል የሚሉ ክርክሮች በሌላ ወቅቶች በሌሎች ስለተብራሩ እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊ አይደለም።

በአገሪቱ ያለው የብሔሮች ችግር በኤርትራ ብቻ ነው፤ ሌሎች ብሔች የሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች ፍሬ ቢስ ናቸው ለማለት ሳይሆን ይህ ጽሑፍ በኤርትራ ላይ ብቻ ያተኮረው የሌሎቹን ጥያቄዎች ሌላ ጊዜ እንመለስበቸዋለን በማለት ነው።

## 2. የኢትዮጵያና የኤርትራ ታሪካዊ ግንኙነት

ኤርትራ የኢትዮጵያ አንድ አካልና አይነተኛዋ ክፍል ነበረች አልነበረችም በሚለው ላይ ብዙ ክርክር ተደርጎበታል። በረኸት ሃብተ ሥላሴ (1980 49) ከ300 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ አብዛኛው የኤርትራ ክፍል ምዕራብ ኤርትራም ጭምር እንዲሁም መላው ትግራይ የአክሱም መንግሥት ግዛት እምብርት እንደነበሩና፤ ይህም ግዛት በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ተዳክሞ እንደተንኮታኮተ ጽፈዋል። በዶክተር በረኸት አባባል ግን የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከጥንታዊት አክሱም ተከታትላ የወረደች ሳትሆን በ19ኛው መቶ ዓመት የተገነባች በውስጥዋ ብዙ ቅኝ ግዛቶችን አምቃ የያዘች አገር ናት። [4] ሆኖም ግን በጉዳዩ ገለልተኝነት ያላቸው የታሪክ ሊቃውንት ዛሬ ሐማሴን፣ አከለ ጉዛይ፣ ሠራዬ፣ ወዘተ በመባል የታወቁት የኤርትራ ክፍሎች የአክሱም ግዛት አካሎች መሆናቸውን ገልጸው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በተለይ የሰሜኑ ክፍል ደግሞ ቀጥተኛ የጥንቷ የአክሱም ተዋራጅ እንደሆነች ያረጋግጣሉ።

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-1468) የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በነበሩበት ወቅት ዳህላክ፣ ምጽዋና የጠረፍ ግዛቶቻቸው «ምድረ ባህሪ» ወይንም «ባህረ ነጋሽ» ብለው ይጠሩ እንደነበረ ታሪክ ጸሐፊዎች ያረጋግጣሉ። እንደዚሁም የኢጣልያ አገር ጎብኛች በ1482 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ጊዜ ዳህላክ ደሴትና ምጽዋ የኢትዮጵያ አካላት እንደነበሩ ጽፈዋል። ዝነኛው የፖርቱጋል አገር ጎብኝና ጸሐፊ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ በ1520 ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ምጽዋ ደሴትና አካባቢዋ «ምድር ባህሪ» በመባል ይታወቅ የነበረ የኢትዮጵያ አንዱ ክፍል እንደነበረ በማረጋገጥ ጽፎአል። (Alvarez 1881:3), (Crawford 1958:43)

በ1557 ዓ.ም ቱርኮች ምጽዋን ይዘው ለተወሰኑ ጊዜያት ከአስተዳደሩ በኋላ የማዕከላዊው መንግሥት ሥልጣን ተዳክሞ አገሪቱ በመሳፍንት አስተዳደር በተከፋፈለችበት በዘመነ መሳፍንት ኤርትራና ትግራይ ራሳቸውን የቻሉ አስተዳደር ሆነው ቆይተዋል። የአውሮፖ ኢምፔርያሊዝም የአፍሪካን አገሮች በኮሎኒነት ለመቀራመት በወሰነው መሠረት «ምድረ ባህሪም» በጣልያኖች እጅ ወድቃ በጣልያ ንጉሣዊ ድንጋጌ መሠረት በ1890 ዓ.ም ስሟ ወደ «ኤርትራ»

ተለወጠ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ታሪካዊ እውነታዎች ታመኑም አልታመኑም፣ እውነትም ይሁኑ ውሸት፣ ታሪካዊ ሐቆችም ይሁኑ ፕሮፖጋንዳ አንድ የማያጠራጥር ሁሉም የሚያውቀው ሐቅ አለ። ይኸውም ፖለቲካው ወደ ጎን የተተወ እንደሆነ፤ በተለያዩ ወቅትም ይሁን ያለ ማቋረጥ፣ በከፊልም ይሁን በሙሉ፣ ኤርትራ የጥንታዊት ኢትዮጵያ አካል ከመሆንዋም አልፎ የስሜኑ ኢትዮጵያ እምብርትና የሥልጣኔዋ ምንጭ የታሪክዋ ግንድና መሠረት እንደነበረች አሌ ማለት አይቻልም። በምንም ጎሣ ስም እንታወቅ በምንም፤ ከሰማችን ስር ብዙዎቻችን ኤርትራውያን ነን ብንል ሐቅ ነው።

## 3 ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ነች?

ኢትዮጵያ በውስጧ ቅኝ ግዛቶችን አምቃ ይዛ እነዚህ ቅኝ ግዛቶችን ትበዘብዛለች በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ክስ የሰነዘረች ሶማሊያ ነች። (Major Asseged 1984:4)። የኤርትራ ጥያቄ ግን ለብዙ ዘመን የብሔር ጥያቄ ሆኖ ከቆየ በኋላ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች የሚለው ክርክር ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ የተነሳ እንጂ ትግሉ ከተጀመረበት ጊዜ እንስቶ ተዋጊዎቹ የተሰለፉበት ዓላማ አይደለም። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችና ተራማጅ ግለሰቦች ኤርትራ የራስዋን እድል በራስዋ እንድትወስን ሲደግፉ ለዚህም ዓላማ መስዋትነትን ከፍለዋል። በ1976 ዓ.ም የኤርትራ ሕዝባዊ ነፃ አውጪ ግምባር ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ያሰንዳች ውይይትና ምርምር የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው፤ ኤርትራም እንደማንኛውም ቅኝ ግዛት ነፃ መውጣት አለበት በማለት መፈክሩን በቀየረበት ጊዜ በኢትዮጵያ የኤርትራ የራስን እድል በራስ መወሰን ደጋፊዎች የሚዉብጡትን አጥተው በኤርትራ ግንባሮችና በኢትዮጵያውያን ደጋፊዎቻቸው መሃከል ከፍተኛ ውዥንብር ተፈጠረ። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት (ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ) የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲን (ኢሕአፖ) ከትግራይ ክፍለ ሐገር ለማስወጣት በአሲምባ በከፈተው ጦርነት ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍን ረድቶአል የሚለው ጥርጣሬ ምንጩ ኢ.ሕ.አ.ፖ የኤርትራ ቅኝ ግዛትነት አልቀበልም በማለቱ ነው የሚል ክስ ኢሕአፖ ደጋግሞ አቅርቦአል። ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ግን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት መሆንዋን ማመኑ ከኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ ጋር በ16/8/80 ዓ.ም በተፈራረመው የጋራ መግለጫ አረጋግጦአል። በዚህም መሠረት ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ «ኤርትራ ሕዝብ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል» የሚደግፍ መሆኑን ሲያረጋግጥ የቲዎሪም ሆነ የገቢር ችግር የገጠመው አይመስልም። (የህ.ግ.ሐ.ኤና. የሕ.ወ.ሐ.ት የጋራ መግለጫ 1980: 2)። ኤርትራ በውን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ከሆነች በቋንቋ፣ በባህል፣ በኑሮ ዘይቤና በጠቅላለው በአሰተሳሰብ ከኤርትራ ጋር የምትመሳሰለው የትግራይ ክፍለ ሐገር እንዴት የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት

እንዳልነበረች ግልጽ አይደለም።

ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ አገር ናት ኤርትራንም በቅኝ ገዢነት ይዛለች ሲባል፣ ደንበሩዋን አቋርጣ የሌሎችን ባዕዳን ሕዝቦች ሃብት ለመበዝበዝ ስትል እነዚህኑ ባዕዳን ሕዝቦች በቁጥጥሩዋ ስል አውላ ከመሃከል አገሩ ሕዝብ በተለየ የጭቆናና የብዝበዛ ሕግ ታስተዳድራለች ማለት ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ሲባል በኬንያ፣ በኡጋንዳ፣ በታንዛንያ፣ ወዘተ እንደነበረው በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በኑሮ ዘይቤና በአስተሳሰብ ፍጹም የማይመሳሰሉ ባህር አቋርጠው ከመጡ እንግሊዞች አስተዳደር ጋር ይመሳሰላል ማለት ነው። እንግሊዞችም ሆነ ፈረንሰዮች በቅኝ ግዛቶቻቸው እንዳደረጉት ኢትዮጵያ የኤርትራን ሃብት ለመበዝበዝ ኤርትራውያንን ከለሙ መሬታቸው ነቅለው ኢትዮጵያውያን ሰፍረውበት ሕዝቡን በበታችነት በመቆጠር ይገዛሉ ማለት ነው። ፊውዳል ኢትዮጵያ በመጠኑም ቢሆን የካፒታሊዝም ጭላንጭል ያቆጠቆጠች የነበረችውን ኤርትራን በቅኝ ግዛትነት ይዛለች ሲባል፣ ቅኝ ገዢዎችና ተገዢዎች ከሚገኙበት የኢኮኖሚና የሰሻል ደረጃ ጋር አይጣጣምም። ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ የኢጣሊያ፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ቅኝ ገዢዎች ካፒታሊስቶች መሆናቸውን ገልጾ የቅኝ ገዢዎቹ መሠረታዊ ዓላማ በአገራቸው የሚገኘው ካፒታል መውጪያና መስፋፊያ መፈለግ ስለነበረበት ኋላ ቀርና ከፊል ፊውዳል የሆኑትን አገሮች በመግዛት መበዝበዛቸውን ገልጿአል (EPLF Memorandum August 1978) ኢትዮጵያ እራስዋ ትናንት በአሜሪካን ኢምፔርያሊዝም ዛሬ ደግሞ በሶሻል ኢምፔርያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እግር ተወርች የተጠፈረች አገር ስትሆን፣ እንዴት ቅኝ ገዢ እንደምትሆን ግር ይላል። በኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ መሪዎች አበባል ግን ኢትዮጵያ የካፒታሊስትነት ሥርዓት ማህበር የሚጠይቃቸው ሁኔታዎችን ስለምታሟላና በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ነባራዊ ሁኔታዎች የተገላቢጦሽ ስለሆነባቸው ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢነትዋ በአሜሪካን እርዳታ መሆኑንና በአሜሪካ ወኪልነት መሆኑን ገልጸዋል። ዛሬ በአሜሪካን እግር ሶቭየት ሕብረት የተተካች ቢሆንም ኢትዮጵያ ኤርትራን በቅኝ ግዛትነት የያዘችው በሶቭየት ሕብረት ተጠሪነት ነው የሚል በአሜሪካ ላይ የሰነዘሩት ክስ ግን በሶቭየት ሕብረት ላይ አልሰነዘሩም። (Ogbagzi 1988:645) ሶቭየት ሕብረት ወታደራዊውን መንግስት በመደገፍ የምትጫወተውን ሚና ከቅን ስህተት የመነጨ መሆኑን ኢ.ፒ.ኤል.ኤፍ፣ ደጋግሞ አሰስቦአል።

እንግዲህ ባጭሩ የኤርትራ ግምባሮች ዋናው ክርክር ኤርትራ በታሪክም ይሁን በባህል፣ በቋንቋ፣ በኑሮ ዘይቤ፣ ወዘተ ከኢትዮጵያ ፍጹም የሚያገናኛት ነገር ስለሌለና ሌላም አገር ስለሆነች ከኢትዮጵያ ነፃ ወጥታ የራስዋን መንግሥት መሥርታ በፈለገችው ሥርዓት መተዳደር መቻል አለባት የሚል ነው።

ኤርትራና ኢትዮጵያ ከላይ ከአጭሩ እንደተጠቀሰው የታሪክ ግንኙነት የማያጠራጥር ሲሆን በባህልና በኑሮ ዘይቤ በአስተሳሰብ ወዘተ የተመሳሰሉ

ሁኔታም ስለማያከራክር እነዚህን ግልጽ ሁኔታዎችን ወደ ጎን ትተን በአሁኑ ወቅት የዓለም ሕብረተሰብም ሆነ የዓለም ሕግ ኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አድርጎ ይመለከት እንደሆነ ማየቱ ለውይይቱ ተጨማሪ ነጥብ ይሆናል። የዓለም ሕግ ከብዙ ልውውጦች በኋላ ስለአገሮች ልዕልና (ሶቭሬንቲ) ዛሬ የደረሰበት ነጥብ አንድ ሕብረተሰብ ልዕልናውም አገርነቱ የሚወሰነው በሌሎች የዓለም መንግሥታትና ሕብረተሰብ ልዕለዊነቱ ወይንም አገርነቱ ሲታወቅ እንጂ በውስጡ ያለውን ሕዝብ በቋንቋ በባህል በጎሣ መመሰሉ አይደለም የሚል ነው።

በዚህም መሠረት በአንድ ነፃ አገር ውስጥ በጎሣና በቋንቋ በባህል ወዘተ መለያየት ምክንያት በብሔሮች የሚነሱ ውዝግቦች የቅኝ ግዛት ጥያቄ አድርጎ ካለማየቱም ሌላ እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ መደገፍ በአንድ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንደመግባት በመቁጠር ያወግዛል። ስለዚህ ነው የኤርትራ ጥያቄ በተባበሩት የዓለም መንግስታትም ሆነ በገለልተኛ አገሮች ጉባዔ በሌሎችም ዓለም አቀፍ መድረኮች ይሁን (ከአረብ ሊግ ሌላ) በግል ሃገሮች (ከጥቂቶች በስተቀር) ቀጥተኛና ግልጽ ድጋፍ ሊያገኝ ያልቻለው። በተጨማሪም ከእነዚህም የዓለም ሕግ ውስጥ በካይሮ በ1964 ዓ.ም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ በአባላት መሃከል በጊዜው የነበረው የግዛት ክልልና በቅኝ ገዢዎች የተከለሉ ወሰኖች የማይጣሱና የማይለወጡ መሆኑን ደነገገ። ስለዚህ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ማለት በቲዎሪ፣ በታሪክ እንዲሁም በዓለም ሕብረተሰብ ፊት ሐቀኛና በገቢር ሊተረጎም የሚችል መፈክር አይደለም።

4) የኤርትራ መለየት።

ኤርትራ እጅግ ቢያንስ ለ60 ዓመታት ከኢትዮጵያ ተለይታ በልዩ ልዩ በዕዳን እጅ ገብታ መኖርዋ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ልዩ ጠባይ ስለሰጣት የኤርትራ ጥያቄም ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች ጥያቄ ተለይቶ መታየትና ለችግሩም የተለየ መፍትሔ መሻት ያስፈልጋል። በዚህ አረገድ መዘንጋት የሌለበት ኤርትራ በ1952 ዓ.ም በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር በተቀላቀለችበት ጊዜ የራስዋ ሰንደቅ ዓለማ፣ የራስዋ ሕግ አውጪ ክፍል፣ የራስዋ ሕግ አስፈጻሚ የመንግሥት ዘርፎች፣ እንዲያውም ከመሃሉ አገር ከነበረው የሰቀና የደረጀ በዴሞክራቲክ ሕገ መንግሥት ላይ የተመሠረተ አስተዳደር ነበራት። በኤርትራ ውስጥ ለተካሄደውና ለሚካሄደው እልቂትና ፍጅት ከመንስኤው ጀምሮ እስከ ዛሬ ላለበት አስከፊ ሁኔታ ተጠያቂዎቹ፣ ለምን ዓለም በዋስትና የደነገገልን ፌዴሬሽን ያለፈቃዳችን ፈረሰ፣ ለምን ዳብሮ የነበረው ዴሞክራቲክ አስተዳደራችን ተደመሰሰ፣ ለምን ቋንቋችንና ባህላችን ተናቀ በማለት ለዚህ ሃቀኛ መብታቸው የሚታገሉትን የኤርትራ ተዋጊዎችን አይደለም። ለ27 ዓመታት በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ መኖር፣ መራብ፣ መጠማት፣ መታረዝ ዘወትር በሞት ጥላ ስር መኖር ቅንጦት ነው የሚል የለም። ከኤርትራ ተዋጊዎች

አንዳንዶቹ በትምህርት ቤት አብሮ አደጎቻችንና ወዳጆቻችን የነበሩና እንደማናችንም በመኪና መንፈላሰስ፣ በለሰለሰ አልጋ ላይ መተኛትና በቅንጦት መኖር ባልገደዳቸውም ነበር። ሆኖም ግን የግል ቅንጦትና ድሎት ለመብታቸው በመሰዋት ለእመኑበት ጉዳይና ዓላማ እንዲህ በቁርጠኝነት በመታገላቸው ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የኩራት ምንጭ ሉሆኑ ይገባል። ለዚህ ሁሉ እልቂት ጥፋተኞችስ ይልቅ በፈውዳል ኩራትና ትምክህተኛነት የተወጠሩ እነራስ እንዳርጋቸው መሣይን እነጄኔራል አብይን በሹመት ቂጥጥ አድርጎ የኤርትራ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርና ባህል የገዘገዘው ፈውዳሉ መንግሥትና ከሰላም ድርድር ይልቅ ጣቶቹን ወደ ብረት ቃታ የሚያስቀድመው የዛሬው ወታደራዊው መንግሥት ናቸው። እንደውነቱማ ከሆነ ትናትናም ሆነ ዛሬ ከኤርትራውያን በጎ ፈቃድ አልጠፋም ነበር። ኢትዮጵያ በተለያዩ ጠላቶች በግብጾች፣ በቱርኮች፣ በጣልያኖች ወዘተ በተወረረችበት ወቅት አብዛኛው በሰሜኑ በኩል ስለሆነ የጦርነቶቹን ገፈት በመጀመሪያ ቀማሾች ሆነው ኖረዋል። በ1952 ዓ.ም የቀድሞው የጣሊያ ቅኝ ግዛቶች የወደፊት እድል በተባበሩት መንግሥታት በሚወስንበት ጊዜ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ (Medhane 1988:2) ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለመቀላቀል ፈቃደኝነቱን ገልጾአል።[5] በታሪክ የተመዘገቡት የነአብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ገድል፣ የእነጸሐፊ ትዕዛዝ ሎሬንዞ ውልታዎችን ትተን በዛሬው ትውልድ የኤርትራ ችግር በሰላም እንዲፈታ የታገሉት እነጄኔራል አማን አንዶም፣ ተማሪውንና ሠራተኛውን ከኃይለሥላሴ ፊውዶ ቢሮክራሲ መንግሥት ጋር የረጅም ጊዜ ትንቅንቅ በተያያዘበት ወቅት ከተማሪ ጎን በመሰለፍ መሪነቱን በማበርከት ለአብዮቱ መጠንሰስ መፈንዳትና መቀጣጠል አስተዋጽኦ ያደረጉት እነገሩይ ተድላን፣ እነአማኑኤልን፣ እነኢሳያስ አፈወርቂን፣ እነበረኸት ሃብተሥላሴን ለናሙና ያህል መጥቀስ ይቻላል።[6]

እንዲሁም ኤርትራውያን መብታቸውን ለማስከበር ያላቸው ቁርጠኝነት የሚደነቅና የሚከበር ቢሆንም፣ ከ27 ዓመታት ጦርነት በኋላ ግን ሐቀኛና በሥራ ላይ ሊውል የሚችል የሕዝቦችንም ጥቅም የሚያስጠብቅ መፍትሔ መሻትና መቀበል ይኖርባቸውል።

## 5) ለሰላም ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች።

ዛሬ የኤርትራ ጥያቄ በቅኝ ግዛትነት ስም ይታወቅ በብሔር በመሠረቱ የፖለቲካ መሆኑንና ችግሩም በዘላቂነት ሊፈታ የሚቻለው በፖለቲካ ድርድር እንጂ በጦር ኃይል እንዳልሆነ በአሁኑ ወቅት በእድላዊነት ሳይሆን ሁኔታውን በቅን በገለልተኝነት ለተመራመረ ሁሉ ግልጽ እየሆነ መጥቶአል። 27 ዓመታት በእሳት የተፈተኑ በሙሉ ቁርጠኝነት የሚዋጉና ለምን እንደሚዋጉም አጣርተው የሚያውቁ የኤርትራ ግንባሮች በጦር ሜዳ ተሸንፈው ይበተናሉ ማለት ዘበት

ነው። በአንጻሩም ከ40 ሚልዮን ሕዝብ በላይ የሚያስተዳድር መንግሥት፣ ራሱ መንግሥቱ ተወዳጅ ባይሆንም በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ዓላማ ይዞ፣ በአንድ ኃያል መንግሥትና በተከታዮቹ ያልተወሰነ የጦርና የዲፕሎማቲክ ድጋፍ እያገኘ የሚዋጋ መንግሥት አንዳንዶች እንደሚሉት (Berhe June 1988:7) ይሸነፋል ማለትም ዘበት ነው። ውዝግቡ በሰላም እስከአላለቀ ድረስ ኮሎኔል መንግሥቱ በአንድ ሕዝበ ትርዕይት ላይ እንዳሉት ጦርነቱ ለብዙ ትውልድ ይቀጥላል። ስለዚህ ውዝግቡ በሰላምና በድርድር መጨረስ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። ለ13 ዓመታት ግራ እጅ እያነሱ እናሸንፋለን ማለት ድልን አያጎናጽፍም። እንድሁም በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲ ተመሥርቶአል፣ ሥልጣን ለባለቤቱ ለሰፊው ሕዝብ ተመለሰ ብሎ እራስን መደለል (ሕዝብ አልተደለለም) ለችግሮቹ መፍትሔ አይሰጥም [7]። በአንጻሩም ደግሞ አሜሪካ ሆኖ «የኤርትራ ተዋጊዎችም አይዘአችሁ ታሸንፋላችሁ ጦርነቱን ቀጥሉ» እያሉ እሳቱን ማራገብ የአገሪቱን ችግር አይፈታም። የኤርትራን ወጣትም የእሳት እራት ከመሆን አያድነውም። እንዲሁም በኤርትራዎች በኩል ከመኢሰን ጋር ትርጉም የለሽ የወዳጅነት ውል መፈራረም ወይንም ከቲ ፒ ኤል ኤፍ ጋር የጋራ መግለጫ መፈረም የሕዝቡን ችግር ያባብሰዋል እንጂ ዛሬ አገሪቱ ላለችበት ከፍተኛ ችግር መፍትሄ አይሆንም፤ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ችግር አቅልሎ ማየትም ያስመስላል።

ይልቁንስ የአዲስ አበባ መንግሥት መሪዎች አገሪቱ ያለችበትን ከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግር በጥሞና በሃቅ መርምረው ትክክለኛውን መፍትሔ መሻት ይኖርባቸውል። ዛሬ በሥልጣን ያሉ ግለሰቦች እጅግ ቢበዛ ከ50 ዓመታት በኋላ እንደሌሉ ተገንዝበው፣ አገር ግን ዘላለማዊ፤ ዕድሜዋ በዓመታት የማይለካ መሆኑን ተረድተው፣ የእርስ በርስ ጦርነቶች እንዲቆሙ፣ በሕዝቦች መሃከል እርቅ እንዲወርድ፣ ሕዝቡ ከሃገሩ ከመሸሽ ይልቅ እናት አገሩን አቅፎና ደግፎ እንዲኖር፣ የላሸቀው ኤኮኖሚ እንዲያንሰራራ፣ ሕዝቡ ወደ ተመረጠበት ተግባር እንዲመለስ አማራጭ የሌለው መፍትሔ በኮሎኔል መንግሥቱ የሚመራው መንግሥት ከስልጣን ገለል ብሎ ሥልጣን ለባለቤቱ ለሰፊው ሕዝብ በውን ማስረከብ ነው። ቅን አገር ወዳድ ወታደሮች በተለያዩ ወቅት በናጄርያ፣ በጋና በላቲን አሜሪከና በእስያ ሥልጣን በበጎ ፈቃደኝነት ለባለቤቱ ለሰፊው ሕዝብ ያስረከቡ ሲሆን የሃገር ፍቅር በልቦናቸው ካለ ለኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግሥት ባለሥልጣኖችም በተለይ የሚከብድበት ምክንያት የለም።

ይህ መሆን ያለበት የኤርትራም ሆነ የሌሎች ብሔሮች ችግር መፍቻው ቁልፍ በኢትዮጵያ በሕዝብ ነፃ ምርጫ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ስለሆነ ነው። የኤርትራ ግምባሮችም ሆነ ሌሎች ከአዲስ አበባው ወታደራዊው መንግሥት ጋር ድርድር ለመጋባት ምን ጊዜም ፈቃደኛ መሆናቸው የሚያጠራጥር ነው። ወታደራዊው መንግሥት ከኤርትራ ሕዝብም ሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ደም ከመቃባቱም ሌላ ፊዙን ወዲያ ትቶ በሕዝብ ምርጫ የተመሠረተ ባለመሆኑ ኤርትራውያንም ሆነ ሌሎች ከማን ጋር ድርድር

ይግቡ የሚለው ጥያቄ ያነሳል። ነገ ሌላ መንግሥት መጥቶ ድርድሩን ቢሽርስ? ወይንም ይህንኑ መንግሥቱ ተጠሪነቱ ለሕዝብ ስላልሆነና፣ ድርጊቱን የሚነቅፉና የሚያጋልጡ ፓርቲዎች ስለሌሉ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ ተነስቶ ስምምነቱን ቢያፈርስስ? እኔ ኃይለ ሥላሴ የዓለም መንግሥታት ውስጤ 390 በመጣስ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ተመሥርቶ የነበረው ፌደሬሽን 1962 ዓ.ም ሲያፈርሱ ተጠሪነታቸው ለሕዝብ ባለመሆኑ እንዲሁም በኢትዮጵያ ቅንጣት የዲሞክራሲ ጭላንጭል ባለመኖሩ ይህንን ሕገ ወጥ ድርጊት የሚቃወም አልተገኘም። ከአገራችንም አልፎ እንዲሁም በደቡብ ሱዳን አኖንያ የነፃነት ታጋዮችና በእምበገነኑ በሱዳኑ ወታደራዊ ገዥ ጃፋር ኤል ኒሜሪ መሃከል ከ17 ዓመታት ጦርነት በኋላ በ1972 ዓ.ም ተደርጎ የነበረው ድርድር ኑሜሪ አፍርሶት አገሪቱን እንደገና የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ዘፈቃት። የኤርትራ ግንባሮች ከአዲስ አበባው መንግሥት ጋር ቢደራደሩ ሁስቱም በውሏቸው ጸንተው እንዲኖሩ ለሌሎች መንግሥታት በተለይም ለሃያላኑ መንግሥታት ዋስትና ሊሰጡ ይችላሉ የሚል ክርክር ሊኖር ይችል ይሆናል። ዛሬ ዓለም ሁለት ኃያላን መንግሥታት በተቀራመቷት ጊዜ ከተዋዋዮቹ አንዱ ቢከፋው ከአንደኛው ኃያል መንግሥት ጉያ ሊገባ ስለሚችል የውጭ መንግሥታት የሚሰጡት ዋስትና ዋጋ ቢስ ነው። ውል ጣሹ መንግሥት እጅግ ቢበዛ ሊደርስበት የሚችለው ከኢኮኖሚ ማቀብ ሊያልፍ አይችልም። ስለዚህ «አድበስብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» ነውና በአንተም ተው፣ በአንተም ተው ግልግል የኤርትራ ግንባሮች ከአዲስ አበባው መንግሥት ጋር ድርድር ገብተው ፍጥጫው ረግቦ ጦርነቱ ለግዜውም ቢቆም ዘላለማዊ ሰላም ተመሠረተ ማለት አይደለም። ስለዚህ የማይጣስና ዘላለማዊ ውል ተደራድሮ ሊገባ የሚችለው ከላይ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ የሚቋቋም ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ብቻ ነው።

የኤርትራ ግምባሮችም ሆኑ ሌሎች ግንንም ከማይወክለው ከአዲስ አበባው ወታደራዊ መንግሥት ጋር ድርድር ለመግባት ፈቃደኛ ባይሆኑ ሰላም ፈላጊዎች አይደሉም ብሎ መውቀስና ማውገዝ አይችልም። «በሬ ከራጁ ጋር ይውላል» እንዲሉ ኢሳያስ አፈወርቂና አህመድ ናስር ከደርግ አባሎች ጋር ዝግ ስብሰባ ለምን አልተቀመጡም የሚል ወቃሽ ካለ እነተፈሪ ባንቲ በተገደሉ ማግስት ኮሎኔል መንግሥቱ በገዛ ወንድሞቻቸውና ወገኖቻቸው ላይ ቀይ ሽብር ካተት በአወጁበት ወቅት በአደባባይ ለመለው የኢትዮጵያ ሕዝብ «ለቁርስ ሲያስቡን ለምሳ አደረስናቸው» ያሉትን ማስታወስ ያሻዋል። ስለዚህ ለብሔሮች ችግር በተለይም በኤርትራ ያለው እልቂት ቆሞ ዘላቂ መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው የአዲስ አበባው ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን ለቆቶ በምትኩ እጁ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በኤርትራውያን ደም ያልነከረ በኤርትራኖች ሊታመን የሚችል ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ተቋቁሞ ሲገኝ ብቻ ነው።

ለዚህም የመጀመርያው እርምጃ በኢትዮጵያ ፖርቲዎች እንዲቋቋሙ መፍቀድ፣ ማበረታታትና መርዳት እንዲሁም በአሁኑም ወቅት ተቋቁመው

ያሉት ከሕቡዕነት ገሃድ ወጥተው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ሕጋዊ ማድረግ ነው። እነዚህ ፖርቲዎች ከተቋቋሙ በኋላ ከእነዚህ ፖርቲዎች ወይንም አብዛኛው የሕዝብ ድጋፍ ያለው ፖርቲ የተውጣጣ መንግሥት መቋቋም ይኖርበታል ማለት ነው። በአሁኑ ወቀት ሥልጣን በሞኖፖል የያዘው ብቸኛው ፖርቲ ኢሠፖም በአበላቱ ፈቃድና ፍላጎት የተቋቋመ እውነትም ተከታዮች ያሉት ፖርቲ ከሆነ ከሌሎች ለወደፊት ከሚቋቋሙት ወይንም ዛሬም ተቋቁመው ከሚገኙት ፖርቲዎች ጋር በመወዳደር ለሥልጣን ዴሞክራሲያዊ ሽግግ ከማድረግ የሚያግደው ነገር መኖር የለበትም። ዛሬ በሥልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦችም በዚሁ ፖርቲያቸው አማካይነት በሥልጣን ሊጋሩ ይችላሉ።

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ማንንም የማይወክል መንግሥት የኤርትራ ችግር መፍታት አለመቻሉ ግልጽ ሆኖአል። በተጨማሪም በጠቅላላው ለአገሪቱ የወጠነው ፕሮግራም ከሥራ ላይ ማዋል አቅቶት ይኸ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ወዲህ በብዙ እረገድ አገሪቱ ወደ ኋላ ሄደች እንጂ ወደ ፊት አልገፋችም። እዚህ ላይ እንግዲህ ትልቁ መሰናክል ይኸ መንግሥት እነዚህን ተረድቶ በፈቃደኝነት ከሥልጣን ገለል ያላለ እንደሆነ ነው። ሆኖም ግን የኤርትራ ግንባሮችም ይሁኑ ሌሎች ለሰላም ድርድር ተቀዳሚ ሁኔታ ያሁኑ መንግሥት ከሥልጣን ገለል ብሎ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ማቋቋም መሆኑንና ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ለመኖር ፈቃደኛነታቸው ቢገልጹ በአሁኑ መንግሥት ላይ ወታደራዊ ግፊት ሊደርስበት ይችላል። በፌዴሬሽን ለመኖር ሁለቱም ወገኖች በዴሞክራሲ አስተዳደር የተመሠረቱ መሆን አለባቸው። ያለ ዲሞክራሲ የፌዴሬሽን አስተዳደር ሊኖር አይችልም። ፌዴሬሽን በፌደራል አስተዳደር የሚተዳደሩት ክፍሎችን እኩልነትና ነፃነትን ያመለክታል። ብዙ ጊዜ የሚዘነጋና መረሳት የሌለበት አንድ ጉዳይ በዚህ የውጭ ወይንም ባዕድ ጠላት በማይታይበት የወንድማማች ጦርነት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ማለቃቸውና ወታደሩም ከቤቱና ከንብረቱ ተፈንቅሎ በቀበሮ ጉድጓድ መኖር መሰልቸቱና መውጪያ መንገድ መፈለጉ ነው።

በአንጻሩ ደግሞ የኤርትራ ግንባሮች የኤርትራ ሕዝብ ሕጋዊ ተወካዮች መሆናቸውን በረጅም ትግል ያረጋገጡ ቢሆንም ከሁለቱ ድርጅቶች ተለይቶ መደራጀትና ፖርቲ ማቋቋም የሚፈልጉ ቢኖሩ መብታቸው መጠበቅ ይኖርበታል። በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ የፖርቲዎች መፈቀድ አስፈላጊነቱ በድርድሩ ወቅት እውነተኛዎቹ የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ተወካዮች ተገኝተው በሕዝቡ ፍላጎት የተመሠረተ ማንም በእሸው ጊዜ የማይሽረው ዘላቂነትና ተቀባይነት ያለው ስምምነት እንዲደርሱ ነው።

በቅድሚያ ግን ሁለቱም ወገኖች በእርግጥም ለዚህ እልቂት ገደብ አበጅተውለት ወዝግቡን በሰላም ሊጨርሱ በውን የሚፈልጉ ከሆነ ያለ

ማመንታትና በድፍረት ሊቀበሉአቸው የሚገቡ ምንአልባትም የሚያስደስቱ ሐቆች አሉ።

ኢትዮጵያውያን ኤርትራ፣ ጎጃም፣ አርሲ፣ ከፋ፣ ወይንም ትግራይ እንዳልሆነችና ቀደም ሲል እንደተገለጸው የራስዋ ሰንደቅ ዓላማ፣ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንደነበራት አውቀውና ተቀብለው ለድርድር መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም የኤርትራ ችግር በሃቅና በፍትሕ እንዲፈታ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ያዋሃደትን የ1952 ዓ.ም የዓለም መንግሥታት ውሳኔ 390 በአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት በ1962 ዓ.ም መሻር ሕገ ወጥ ድርጊት መሆኑን ይቀበላሉ። ምናልባትም ይኸ ፌደሬሽን ኢምፔርያሊስቶች በአፍሪካ ቀንድ እግራቸውን ለማስገባት አስበው የኤርትራ ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ከሚዛን ሳያገቡ፣ ያደረጉትም ሊሆን ይችላል። የሆነው ሆነ፣ ታሪክን ወደ ኋላ መመለስ አስቸጋሪ ነው። በእውን ብንነጋገር በኢትዮጵያ የቅኝ አከራሪዎችም ሆኑ የግራ ተሰፈንጣሪዎች ከትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት መሪዎች ሌላ፣ የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል የሚደግፍ መኖሩ ያጠራጥራል። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅትም መሪዎች ለጊዚያዊ ጥቅምም ይሁን በውን እምነውበት መሆኑ ማወቅ አይቻልም። ይኸንን ሁሉ መስዋዕትነት ለከፈሉ ለኤርትራውያን ይህንን መስማት ከባድ ሊሆን ይችላል። ግን ሐቁ ይኸው ነው። ሆኖም ከየአቅጣጫው በሚደረጉ የግልም ሆነ የአደባባው ውይይቶች መደምደም እንደሚቻለው ለኤርትራ በጎ ፈቃድ ያላቸው ቅን አሳቢ ኢትዮጵያውያን ኤርትራ ከኢትዮጵያ በአንድ የፖለቲካ ሐረግ (የሰለለም ቢሆን) ማለት በፌዴሬሽን፣ በኮንፌዴሬሽን ወይንም በሌላ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ጋር እስከተያያዘች ድረስ የኤርትራውያን ልዩነትና ሊኖራቸው የሚገባ መብቶችን ይደግፋሉ። ፌዴሬሽን ወይንም ኮንፌዴሬሽን ብዙ ደረጃዎች የያዙ ቃላት እንደመሆናቸው መጠን፣ የውጭ ጉዳይ በፌደራል መንግሥት ስር ይሁን አይሁን፣ ገንዘብና ፋይናንስ ነክ ጉዳዮች በየግላቸው ያስተዳድሩ፣ እያንዳንዳቸው የፖሊስ ኃይል ይኑራቸው አይኑራቸው የመሳሰሉ መለስተኛ ጉዳዮች በድርድሩ ወቅት የሚፈቱ ጉዳዮች ናቸው።

## 6) ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ በዝርዝር የሰፈሩ ሃሳቦችና አስተያየቶች በሚከተሉት አጫጭር ጭብጦች ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

ሀ) የኤርትራ ግምባሮች ከዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ለመኖር ፈቃደኝነታቸው በግልጽ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስታወቅ።

ለ) በቅድሚያ ግን የአሁኑ ማንንም የማይወክለው የአዲስ አበባው መንግሥት ከሥልጣን ወርዶ፤ በምትኩ ለወደፊት የሚቋቋሙ፣ ተቋቁመው በሕቡዕነት የሚገኙ ፖርቲዎችና ኢሠፖም ጭምር ሕዝቡን የሚወክል መንግሥት

ለማቋቋም ዲሞክራሲያዊ ሽሚያ አድርገው ከሚቋቋመው የሕዝብ ተወካይ
መንግሥት ጋር ብቻ ለመደራደር ፈቃደኝነታቸው መግለጽ።

ሐ) ኤርትራ በረጅም ትግል የተፈተኑ ግምባሮች የምትወከል መሆኑ የማያጠራጥር ቢሆንም ከግምባሮቹ ውጭ ለመደራጀት የሚፈልጉ ኤርትራውያን ካሉ በሚያቋቁሟቸው ቡድኖች ወይንም ፖርቲዎች እማካይነት እንዲወከሉ መፍቀድና መርዳት።

መ) የኤርትራ ተወካዮች ቡድን ከታወቀ በኋላ ከኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ጋር ድርድር ገብተው የፌዴሬሽኑ ዝርዝር ሁኔታዎችን መወሰን
።

ሁለቱም ወገኖች የያዝዋቸው አቋሞች በጣም የከረረ እምነቶችን ያዘለ ነው። ኢትዮጵያውያን ነፃነታቸውን ለማስከበርና ሕልውናቸውን ለመጠበቅ እንዲሚታገሉ አድርገው እንደሚቆጥሩት ያህል ኤርትራውያንም ደግሞ ለነፃነታቸውና ለመብታቸው እንደሚታገሉ ያምናሉ። ስለዚህ ሁለቱም ወገኖች ከአቋማቸው ፈቀቅ ማለት ከበድ መሆኑ የሚከድ አይደለም። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ መሪነትና ዝም ብሎ በስሜት መነዳት ሐቁንና ምኞትን መለየት ከትግል መማርና፣ እንዲሁ ዝም ብሎ በትግል ማለፍ የሚለየው። እነዚህን እውነታዎች ከለመቀበልና ከለመረዳት ኢትዮጵያውያን ኤርትራ እንደሌሎቹ ክፍለተ ሐገራት የኢትዮጵያ አንዷ ክፍል ሐገር ነች፣ በዚሁ መሠረት ትተዳደራለች እስከእሉ ድረስ የኤርትራ ግምባሮችም ከነፃነት ወይንም ከመገነጠል ሌላ ግንኙነት ለመቀበል እስካልፈቀዱ ድረስ፣ ይኸ እሽናፊና ተሸናፊ የሌለበት ግዳይ የማይጣልበት፣ ጀግናና ፈሪ የማይለይበት የወንድማማች እልቂት ይቀጥላል። ኤርትራም የጦርነት ማሳ ሆና አገሪቱም በድህነት እየማቀቀች የዓለም ተመጽዋች ሆና የዘሬው ትውልድ በታሪክ ተወቃሽ ሆኖ ዘመን ያልፋል ዘመን ይተካል።

# የግርጌ ማስታወሻዎች

[1] በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙት ዓመተ ምህረታት በሙሉ በአውሮፓውያን አቆጣጠር መሠረት ነው።

[2] ማህተማ ጋንዲ ይህንን መፈክር ሲያሰሙ የራሳቸውን ሞት ጠቅሰው እንጂ የሌሎችን አልነበረም የኢትዮጵያዎቹ «አንድነት ወይንም ሞት» ሲሉ ግን ከሞቱ አካባቢ ከአንድ ሺህ ኪሎሜትር በላይ እርቀው ስለሌላው ሞት ነው የሚፎክሩ።

[3] በ1969 ዓ.ም ዋለልኝ መኮንን ይህንን እስመልክቶ በተማሪዎች ጋዜጣ አንድ አንቀጽ ጽፎ ብዙ አዲስ አሳቦች ስለተነሱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መኮንን አዳራሽ ውስጥ አሰፋ ምህረቱ፣ ንጉሤ አየለ፣ ፋሲካ ሲደልልና ይኸው ጸሐፊ የተሳተፉበት የመጀመሪያው የብሔሮች ጥያቄ ውይይት ተካሂዶ ነበር።

[4] በ1935 ዓ.ም ኢትዮጵያ በጣልያን እጅ በወደቀችበት ጊዜ የኬንያው ጆሞ ኬንያታ ኢትዮጵያ የመላው የአፍሪካና የጥቁር ዘር መመኪያ እንደነበረች ሲገልጹ የናይጄርያው ናምዲ አዚኪዌ ደግሞ የመጨረሻዋ የተቀደሰች የአፍሪቃ የነፃነት ሙራ፣ የማትገረሰስ የነጮች ወራሪ መከቻ ቋጥኝ የአፍሪካ የነፃነት ሰንደቅ ነች በማለት አሞጋግሰዋታል።
የኢትዮጵያ ነፃነት ለመዋጀትም ጥቁር አሜሪካኖች «ብራውን ኮንዶር» «ብላክ ኢግል እሽ ሃርለም» በሚሉ ስሞች ተደራጅተው ከኢትዮጵያውያን ጎን ተዋድቀዋል። እንዲሁም ብዙ አፍሪካውያን ለኢትዮጵያ ነፃነት ብዙ ተጋድሎ አድርገዋል። ታድያ ዛሬ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ናት ሲባል እነዚህ አፍሪካውያን፤ ጥቁር አሜሪካውያንና የካሬብያን ሰዎች በሙሉ ተሳስተው ነበር ከማለት ሌላ ምርጫ የለም። ኢትዮጵያ መቼም ቅኝ እንዳልነበረችና እንዳልሆነችም Teshale Tibebu «Process of state Formatinon in modern Ethiopia 1850–1974» Proceedings 2nd International Conference on the Horn of Africa p. 13–40 አጥጋቢ በሆነ መንገድ ተንትነውታል።

[5] የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር በመቀላለል ፈቃደኛ አልነበረም፣ አብዛኛው የኢርትራ ሕዝብ ተቃውሞአል የሚልም ወገን ክርክር አለ።

[6] ሕሩይ ተድላ በአ.አ ዩኒቨርሲቲ ክሎጅ ተማሪዎች መሪነት ተማሪውን ያነሳሱ ሲሆኑ፣ ኢሣያስ አፈወርቂ ደግሞ አ.አ ኢንጂኒሪንግ ኮሌጅ ለሁለት ዓመታት መተማሩበት ወቅት በተማሪዎች ንቅናቄ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ መሆኑ አይዘነጋም። እንዲሁም በረኸት ሃብተሥላሴ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣን በነበሩበት ጊዜ በስውር የተማሪዎች መሪዎችን በሃሳብ ይረዱ ነበር። አብዮቱም እንደፈነዳ በዓለም ባንክ የነበራቸው ከፍተኛ ደረጃ ለቅቀው በፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአደረገላቸውን ጥሪ አክብረው ኢትዮጵያ በመመለስ በምርመራ ኮሚሽን በማገልገል ለአብዮቱ እድገት አስተዋጽኦ አድርገዋል።

[7] መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በሜይ 28 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ ለውጭ አገር ጋዜጠኞች በሰጡት መልስ መንግሥታቸው በሕዝብ ሙሉ ፈቃድና ምርጫ የተቋቋመ መሆኑን

ገልጸው፣ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ስለመስፈን ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል። " Could there be any other country in the world that has gone to this extent of guaranteeing the freedom of its people?" (Mengistu Hailemariam 1988: 21)

## የጽሑፎች ዝርዝር


Alvrarez F. Narrative of the Portuguese Embassy to Abyssinia during the years 1520-1527 tr. and ed. by Lord stanley (London Hakluyt Society 1881)

Berket Habte Selassie, Conflict and Intervetion in the Horn of Africa, Monthly review Press, (London 1980)

Berhe Habte Ghiorgis, "Prospects for Peaceful Settlement of the war in Eritrea" Journal of Eritrean Studies, Summer 1988.

Crawford, O.G.S ed. Ethiopian itineraries ( Circa 1400-1524) London hakluyt society 1957)

E. P . L. F Memorandum August 1978

የሀ.ገ.ሐ.ኢና የሕ.ወ.ሐ.ት የጋራ መግለጫ 1980

Major Asseged, Ethiopia. Revolution and War, Ph.D Dissertation, University of Denver, Colorado, 1982.

Medhane, Tesfatsion, Eritrea: Dyanamics of a National Question, B.R. Gruner, Amsterdam 1986

Ogbazgi, Yohannes, "Behind the Etho-Eritrean Federation. The Conspiracy Thesis" Journal of Eritrean Studies, Summer 1988.

Teshale Tibebu, "Process of State Formation in modern Ethiopia 1850-1974" Proceedings 2nd international conference on the Horn of Africa, New York School of Social Reasearch, New York May 29-30, 1987.

## አስተዋጽኦ ላደረጉ ምሥጋና

ለዚህ ቀጥር ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰማቸው ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩ ግለሰቦች የመጽሄቱ አዘጋጅ ክፍል ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል።

አቶ አበበ ደምሴ ፣
የህብረት መጽሄት አዘጋጅ፣ የዚህን ቁጥር ግማሹን በኮምፒዉተር በማዘጋጀት ስለረዱን፣

አቶ ብንያም ጥላሁን ፣
የዚህን ቁጥር ግማሹን ጥራት ባለዉ ሁኔታ በኮምፒዉተር አዘጋጅተዉ ሌላም ብዙ የሃሳብና የቁሳቁስ ድጋፍ በመስገሳቸዉ፣

ዳሽን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ፣
መጽሄት አሁን ይዞ የሚገኘዉን አቅድ ለማግኘት ኩባንያዉ ያልተቆጠበ ጥረት በማድረጉና ሌላም ቴክኒካዊ ምክር በመስገስ በኩል ስለተባበሩን፣

አቶ ፈለቀ 'አርምዴ
በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ስእል ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ናቸዉ። ለዚህ ቁጥር ተስማሚ የሆነ ስእል በፈለግንበት ጊዜ ከስራዎቻቸዉ አንዱን በመስገስ ስለረዱን ከልብ እናመሰግናቸዋለን።

ፕሮፌሰር ሃይሌ ገሪማ፣
ፕሮፌሰር ሃይሌ በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ የፊልም ጥና ክፍል ፕሮፌሰር ናቸዉ። በዚህ መጽሄት ሽፋን ላይ የሚታየዉን ፎቶግራፍ ከስብስቦቻቸዉ መካከል አዉጥተዉ በመስገሳቸዉ በጣም እናመሰግናቸዋለን።

ዶክተር አበራ ሞላ፣
በእንስሳት በተለይም በከብት ህክምና በዶክትሪት ደረጃ የተመረቁ ቢሆን የዚህን ቁጥር ርእስ አንቀጽ እዲስ በፈጠሩት የግእዝ ፊደል በማዘጋጀት ስለረዱን ከአድናቆት ጋር እናመሰግናቸዋለን።

ወይዘሮ አሥራቅ ወ ሥላሴ ለስገሱልን ስጦታና

ላደረጉልን እርዳታ ከልብ እናመሰግናቸዋለን።

* * *

በመጽሔቱ ውስጥ ማስታወቂያዎችን
ማስገባት ስለወሰንን ማስታወቂያዎች
ያሏችሁ ሁሉ በቅድሚያ
እንድትልኩልን።

| | |
|---|---|
| ሙሉ ገፅ | $ 160 |
| ግማሽ ገፅ | $ 80 |
| ሩብ ገፅ | $ 40 |

# ደብዳቤዎች

## ይድረስ ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች

በመጀመሪያ ጥንታዊ አበቶች ባወረሱን ወግ መሠረት ከራሳችን ዝቅ በማለት አክብሮት የተመላበት ሰላምታችንን ለናንተ ለአዘጋጅዎችና ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለሆኑት አንባቢዎቻችሁ ሁሉ በጋለ ስሜት እናቀርባለን።

ለጥቀንም በመላው ዓለም ከምድር እድማስ እስከ እድማስ ባሸገሮች ተበታትነን የአገርና የወገን ፍቅር፤ ናፍቆት፤ የወገኖቻችን ችግርና ቸነፈር፤ የምዕራብ ዜና ማሰራጫዎች ፀረ-ኢትዮጵያ ውርጅብኝ እያሰጨነቀን የሆዳችንን ብሶት ሁሉ የምናወጋው ወገን ከጉናችን በምንፈልግበት እንገብጋቢ ወቅት ሰምና ወርቅን ይዛችሁ ብቅ በማለታችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ እያልን የኛንም መሥፈሪያ የማይገኝለት ፈንጠዝያ ጭምር እንገልጥላችኋለን። ማናቸውም በስደት በባዕዳን አገር የምንገኝ «አበሾች» ሁሉ እንደምናውቀው መተንፈሻ አጥቶ በ«ፈረንጅ አገር» የተዳፈነ ብሶታችንን፤ ከእሳት የጋለ የሀገር ፍቅር ስሜታችንንና አገራችን ከገባችበት ማጥ መንጥቶ ለማውጣት ሁላችንም የኢትዮጵያ ልጆች ለምናደርገው ውይይት እስከ ሁን ከጠባብ ፖለቲከና ርእዮተዓለም ነፃ የሆነ አገር-አቀፍ መድረክ ሳጣነው ሁሉ ሰምና ወርቅን ታላቅ የእፎይታና የእለኝታ መሠረተ ድንጋይ እኑራችኋልና ጥረታችሁ ይሰካላችሁ እያልን መልካም ምኞታችንን ስንገልጥላችሁ በናንተ ያለንንም ከፍተኛ ኩራት በመግለጥ ጭምር ነው። እኛም ብንሆን በአውሮፖ፤ በአፍሪቃ (ከኢትዮጵያ ውጭ) እንዲሁም በሰሜን አሜሪካ የተበታተንን ኗደኞሞች ብንሆንም እቅማችን በፈቀደው ሁሉ መጽሔቷን እንድትቀጥል ለማድረግ በምታደርጉት ጥረት ሁሉ የምንተባበራችሁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ቃል እንገባላችኋለን።

የናንተ የጥናት መጽሔት ከመጀመሩዋ በፊት በየእለንባቸው የአውሮፖና የሰሜን አሜሪካ ከተሞች የሚወጡ ጋዚጣዎች ፀረ-ኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ ሳይሆኑ ፀረ-ብሔረ ኢትዮጵያ ሆነው ስላገኘናቸው በሁኔታቸው ላይ በመወያየት ብሔራዊ ኩራታችንን በስደትም ቢሆን ለማስጠበቅ ምን ማድረግ ይገባናል ብለን በደካማ አቅማችን አንዳንድ እቅዶች ለመወጠን በምንጣጣርበት ጊዜ ሰምና ወርቅ መውጣቷን ሰምተን ከየቦታው ተፈላልገን እስከ ሁን የወጡትን እትሞች አግኝተን እነበብናቸው። «እሰየው ያሳድጋችሁ» እያልን በእበሬ ጠላ የበርሀ ጥሙን እንደሚቆርጥ ገበሬም በእርካታ ሲቃ ብዙ ተነፈስን። በውጭ አገር ከተበታተነው «የሀገር ልጅ» ሁሉ የሚበጅ መሠረት ሰምና ወርቅን በመጣላችሁ ተበራተን እኛም በአጋጣሚ ከአምስት ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች የተውጣጣን የኢትዮጵያ ልጆች ነገር ግን ከልጅነታችን ጀምሮ የቅርብ ጓደኞች የሆንን በሦስት የተለያዩ አህጉራት ብንገኝም በያለንበት የስደት

አገርኛ ሐሳቦቻችንን በደብዳቤዎችና በስልክ ጥሪዎች በመለዋወጥ እነሆ አንድ «የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሀገር የወገን ፍቅር፣ የባሕልና የታሪክ ጥናት ክበብ» ብለን የሰየምነውን ትንሽ ነገር መሠረትን። ዓላማዎቻችንም ጥንታዊ አባቶችና እናቶች የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የብሔረሰብ፣ የጎሳ ልዩነቶች ሳያግዷቸው እንደምንም አገራችንን አሁን ያገኘችውን ቅርፅዋን አስይዘው እንዳስተላለፉልንና ለዚሁ ተግባር የከፈሉትንም መሥዋዕትነት ጭምር ለማጥናት ነው። ተጨማሪው ዓላማችን የኢትዮጵያ ታሪክ የአፍሪቃም ታሪክ አካል! እንደመሆኑ የሌሎች አባቶችና እናቶች አፍሪቃውያንን ባሕልና ታሪክ እንዲሁም ፀረ-ቅኝ አገዛዝና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሎቻቸውን በማጥናት የተከሰተልንን እውቀት ሁሉ ከወገን ጋር ሁሉ ለመካፈል ነው። በእርግጥ ይህ ተግባር በምዕራብ ዓለም ከእለታዊ መያተኞች ያልተሸለ (የሽቀላ) ኑሮ ለምንገፋ ግለሰቦች የገንዘብና የጊዜ መስዋዕትነቱ ቀላል ባይሆንም የቻልነውን ያህል ለመጣጣር ወገባችንን ታጥቀን ተነስተናል። «የአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ጉዞ በአንድ እርምጃ ይጀመራል» ሲሉ ስለሰማን በትንሿ ጅማሬአችን አናፍርም።

ቀደም ሲል ለመግለጥ እንደሞከርነው የጂአግራፊ መራራቅ ሳያግደን የዓመት የሥራ ፍቃዳችንን ሁሉ መስዋዕት እያደረግን ባደረግነው ጥረት የከበበችን የመጀመሪያ አስተዋፅኦ የሆነችውን ይህችን «የኢትዮጵያ ረሀብና የአዕራብ ጋዜጦች አስተያየት» የተሰኘች ጽሑፋችንን ስናቀርብላችሁ ደስታችንን እየገለጥን በተለይ በኢትዮጵያ «ጠኔ» ላይ በምታተኩረዋ እትማችሁ የሚቻል ከሆነ ብታወጡዋት ምስጋናችን አክብሮታ የተመሰበት መሆኑን ጭምር በማረጋገጥ ነው። ወደፊት በሰላም እና በአካባቢ (ENVIRONMENT) እንደምታተኩሩ ያለንን ምኞት እንገልጣለን።

ኢትዮጵያዊ/ሐበሻዊ ባሕላችንና ማንነታችን በምዕራባዊያንም ሆነ በምሥራቃውያን ተራ ፕሮፓጋንዳ እንዳይረገጥ ለመታገል ከቆረጡ ወገኖቻችሁ ውስጥ የሆነው፣

እነቆሪቾ ፈይሣ፣
ከሰሜን አሜሪካ፤

<u>ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች</u>
ከጌትነት ቢሆነኝ
አዲስ አበባ

የመጀመሪያዎችን ሶስት እትሞች አንብቤአለሁ። መልካም ጅምር ነው። በአንባቢያን መልዕክት ላይ እንደተመለከተው እንደሌሎች ቀደምት መጽሔቶች ብልጭ ብሎ ድርግም እንዳይል አደራ የጠበቀ ነው።

መጽሔቱ እንደጀመረው የምርምር ይሁን፤ ስሜታዊ አይሁን።

ታሪክ ያጣመመና በአሉባልታ የተሞላ ታሪካዊ አቀራረብ መጽሔቱን ሊያስንቁት ይችላሉ።

አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበት የንቃት ሕሊና ደረጃንም በየጊዜው መገምገሙም ተገቢ ነው። ከንቃተ ሕሊናው በታች የሆነ አቀራረብ መጽሐቱን ያስንቀዋል፤ ከንቃተ ሀሊናው በላይ ከሆነም ተፈላጊነቱ ለተወሰነ የምሁሩ ክልል ብቻ ይሆንና አንባቢው ያንሳል፤ ከዚያም ከገፋ የምሁሩ መከራከሪያና መነታሪኪያ መድረክ ይሆናል። ይህም የራሱ የሆነ ጉድለት ይሆናል።

ዛሬ ሕዝቡ ከትግሉ ብዙ ተምሯል። በኮንትርባንድም በሌላ ባገኘት ሬዲዮ ብዙ ያዳምጣል። በገበሬ ማሕበሩም ሆነ በወጣቱ፤ በከነማው በኩል ስለሶሻሊዝም ስለኅብረት ሥራ ማኅበር፤ ስለልማት ወዘተ አውቋል። የገበሬ የልማትና የአስተዳደር ከድሬ ሥራ አልፈታም አስተምርቷል። ቅድመ ፷፮ የነበረው ሰውም በአዲሱ እየተተከ ነው። መሠረተ ትምሕርት ብዙ ሕዝብ አዳርሷል። ከዚያም ጋር የአከባቢ ጋዜጦች በመጠኑም ቢሆን ብቅ ብቅ ብለዋል። ቴሌቪዥን አሥመራ፤ ጎንደር፤ መቀሌ፤ ባሕር ዳር፤ ማርቆስ፤ አዲስ አበባ፤ ደብረ ዘይት፤ ናዝሬት፤ አዋሽ፤ ሐረር፤ ድሬዳዋ፤ ጎባ፤ አሰላ፤ ሻሸመኔ፤ አዋሳ፤ ይርጋለም፤ አርባ ምንጭ፤ ጅማ፤ ነቀምት፤ ወዘተ..... ስለሚደርስ ቴሌቪዥን መግዛት ደግሞ እንደ ሬዲዮ ስለሆነ በዚህ በኩል ሕዝቡ ምን ያህል እንደሚማር መታወቅ አለበት። በሬዲዮ በኩል በአማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ፣ ትግረ፣ አፋርኛ፣ ሶማልኛ ይነገራሉ። ትምሕርት ቤቶች በጣም ተስፋፍተዋል። ገጠሩ ሁሉ ትምሕርት ቤት ከፍቷል። ታዲያ ይህንን ሕዝብ አሳንሶ ማየት አይቻልም። በሌላ በኩል ፀረ-መንግሥት የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች የበኩላቸውንም ስለሚያደርጉ በዚህ ትግል ውስጥ ያለ ሕዝብ በቀላሉ ሊታይ የሚገባው አይደለም። አንዳንደቹ ግን የሕዝቡ ሥነ ልቦናዊ ዘይቤ መቀየሩን አልተረዱም። እናንተም ይህን እንድትረዱ ያሻል።

ስለአዲሱ ርዕሳችሁ ማለትም ስለድርቅና ጤኔ በዚህች ደብዳቤ መግለጽ ይቸግረኛል። ልቀጥል ብል አንድ መጽሐፍ ይሆንብኛል። ለጊዜው ይህ ችግር በቀንጽልነቱ ብቻ የሚታይ መሆን የለበትም። ሁለንተናዊ ገጽታው ሊዳሰስ ይገባዋል። ለአንድ ሳምንት ቀርበው አጠናንን የሚሉት ፈረንጆች አገሪቱ የኮሙኒስት ሥርአት ስለምትከተል ነው ብለው ይደመድማሉ። ብዙ ቢያትቱም መድምደሚያቸው ያው ነው።

ይህን የተፈጥሮ ችግርና ሌላውንም የኢኮኖሚ ችግራችንን በሚገባ ተገንዝበናል። የምርት ዘመቻ የሚባለው ተጀምሮ እንደነበረ በየጉባዔው «ከዕቅድ በላይ ተመረተ፤ ከዕቅድ በላይ ተሠራ» እየተባለ መሬቱ ሁሉ በወርቅ እንደተነጠፈ እየሆነ ሪፖርት ይቀርብ ነበር።

ምድረ ሹም እውነቱን በመናገሩ ከሥልጣኑ እንዳይወርድ በመፍራት ዋሸ፤ በዚህ ዓመት ግን ሀቁ ወጣ።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ የቆየ ነገር ቀልድ ልናገር።

አንድ ከተሜ ፍሪጅ ነበረው። አንድ ቀን ብድግ አለና ለጓደኛው ፍሪጁን ለመሸጥ እንዳሰበ ይነግረዋል። በዛሬ ጊዜ ፍሪጅ አይገኝም። እንዴት ትሸጠዋለህ ይለዋል ጓደኛው። ፍሪጁ ምን ያደርግልኛል። ሥጋ

የለም፣ ጎመን፣ ድንች፣ ወዘተ  ዋጋው ተወደደ። ምርት የለም ስለዚህ መሸጡ ነው የሚሻለኝ ይለዋል። ጓደኛው ሞኝ ነህ ለምን ሶኬቱን ነቅለህ ከኢትዮጵያ ሬዲዮ ጋር አታገናኘውም! ያን ጊዜ ምርቱ በሽ በሽ ሆኖ ፍሪጅህ ውስጥ ይገባል እለው ይባላል። በእርግጥም በዚያን ወቅት በሬዲዮ የምርት ማደግ በብዛት ይወራ ነበር።

ወደ ዋናው ፍሬ ነገር ለመለስ የድርቅ ችግር በሚለው ርዕስ መታየት የሚገባው ብየ የማምነው። የተፈጠር ችግር ምን ማለት ነው? ከምን ይነሳል፣ የተፈጥሮ ችግርን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች፤

– የአየር መዛባት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ሀሪኬን፣ እሣተ ገሞራ፣ ጦርነት ____

የተፈጥሮ ችግር የሚያጠቃቸው አካባቢዎች? ለምን?

የተፈጥሮ ችግርና ኋላ ቀርነት ያላቸው ግንኙነትና ልዩነት

-መንገድ -አስተራረስ
-ገበያ -ትርፍ አምራችነት

የተፈጥሮ ችግርና የመሬት ይዞታ፣ የልማት ስትራቴጂ፤ ግንኙነት

-ሰፈራ -የመንግሥት እርሻ
-መንገድ መሥራት -የኅብረት ሥራ ማሠራት ሁኔታ
-የመሬት ይዞታ
-ሰውጭ ምንዛሪና ለሃገር ውስጥ ብሌት የሚመረተው ሬሺዮ
-የማኔጅመንት ችግር -የምርት ሥርዓት
-የሕዝብ አገልግሎት ኅብረት ሥ/ማ

የተፈጥሮ ችግርና የአከባቢ ሠላም መታጣት ያላቸው ግንኙነት

-ግንኙነት መቋረጥ -ለማምረት መቸገር
-የሰው ኃይል መቀነስ -ወዘተ

የተፈጥሮ ችግርን ለመቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎች፤

-አፋጣኝ ነፍስ አድን እርምጃዎች
-መሀከለኛ ጊዜ እርምጃዎች
-ዘላቂ መፍትሔ እርምጃዎች

የተፈጥሮ ችግር በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ክስተት ሳይሆን በተለያዩ ጊዜዎች መከሰቱን፣ ጊዜውንና ምን ያህል ጉዳት እንዳደረሰ

እርዳታ የሰጠው ጥቅምና ያስከተለው ችግር

በወቅቱ ነፍስ አድን መሆኑ በዚሁ አጋጣሚ
-ግድብ ተሰርቷል። -ክሊኒክ ተሰርቷል።
-እርከን ተሰርቷል። -ዛፍ ተተክሏል።

ከእርዳታው ጋር አብረው የተከሰቱ
-የእርዳታ ሰጭዎች የበላይነት
-የርዕዮተ ዓለም ብረዛ
-የውስጥ አስተዳደር ጣልቃ መግባት
-የደመወዝ ደረጃዎችን ማዛባት። ለምሳሌ WORLD VISION የተባለው ለሹፌር ብር 850 መክፈል ስለጀመረ በመስሪያ ቤቶች ችግር ፈጥሮ ነበረ።
-እርዳታ አድራሽ ተብሎ የተላከው በሽታ ሌሎች ያልተለመዱ የወሲባዊ ግንኙነቶች ዘዴዎችን ማስገባታቸው
-አንዳንዶቹ ሰላዮች መሆናቸው
-በእደላ ወቅት ሊብነት፣ አድልዎ ወዘተ መከሰት፤ እንዲ ቀጥሮ በመሳሳቱ አዲስ የመጣ መኪና ሞተር ተነቅሎ መርከቶ ገብቷል። ስንዴ የብዙ ሹማምንትን ቤት ሠርታለች፣ መኪና ሆናለች፣ ዊስኪ ሆናለች፣ የፖለቲካ መሣርያ ሆናለች፣ ምን ያልሆነችው አለ? ብሔራዊ ጦርም ሆናለች።
-በኢትዮጵያ የዕግግኮ መቋቋም ለእርዳታ አሰጣጥ አዲስ የአሠራር ብልሀት መሆን።
-ሌሎች እንደ ወሀህት፣ ሸዕቢያ የመሳሰሉት እርዳታ ሰጭ ነን ማለታቸውና ለሕዝቡ ሳይደርሱ በመቅረታቸው፣ መንግሥት ለመግባት ባለመቻሉ ሕዝቡ ለረሀብ መጋለጡና ሲብሰበት ኪላ እየግሰ መምጣቱ 1976-1977።
-በ1979 የእርዳታ አሰጣጥ ከሌላው ጊዜ የተለየው በመጠለያ መቀመጥ መከልከሉና ድርሻውን እየያዘ መመለሱ።
-በሰላም መታጣቱ ምክንያት እህል ወደከተማው የሚገባው መጠን በማነሱ የከተማው ሕዝብም ለእርዳታ ተቀባይነት መቃረቡ የነበረው ክስተት፣ ይህም ለምዝበራ አመችቶ እንደነበር /አሥመራ/
-በ1979 «ሁሉም ነገር ወደጦር ግንባር» በተባለበት ወቅት ከICRC ጋር መንግሥት የገጠመው ውዝግብ ረሃብ-የፖለቲካ መሳሪያ እንዲሆን የተደረገው ጥረትና ውጤት
-ረሃብና ኢትዮጵያ ተመሳሳይነት ሊይዙ መድረሳቸውና የሕዝቡን ብሔራዊ ኩራት መንካት
-ሠፈራ መጀመሩ፣ ወሀህትን ማስቆጣቱ፣ (የሰው ሀይል ይቀንሳል) ይህንም የፖለቲካ መሣሪያ ለማድረግ የተደረገው ጥረት፤ በሰፈራም ወቅት የአሠራርና የአፈጻጸም ችግር
-የሰደተኞች መብዛትና ለፖለቲካ ውዝግብ አመቺ መሆን
-በአንዳንድ ሸቀጦች ላይ የተጣለው የታክስ ጭማሬ ወዘተ
-መደምደሚያው ኢትዮጵያ ሰፊና ሀብታም አገር ነች፤ ኢትዮጵያ በከፊል እንጂ በሙሉ ልትራብ አትችልም። የተፈጥሮ ችግር

ያለጠቃው ሊሰውን ሊረዳ ይችላል። ሆኖም
–የምርት ሀይል ዝቅተኝነት
–የሠለም መታጣት
–የማኔጅመንት ጉድለት ዋናዎቹ ስለሆኑ በእነዚህ በኩል ጥረት መደረግ እንዳለበት ቢጠቀስ መልካም ነው እላለሁ።

ጌትነት ቢሆነኝ
አዲስ አበባ

********************************

## ም ስ ጋ ና

**ሰምና ወርቅ** ቁጥር 4 በማሰራጨት በኩል የረዱንን ሁሉ እናመሰግናለን፦ በተለይም፤

| | |
|---|---|
| ዶ/ር እርቁ ዶመር፤ | ችካጎ |
| አቶ ብንያም ጥላሁን፤ | ሲያትል |
| አቶ እንዳአለም ተፈራ፤ | ካሊፎርኒያ |
| ወ/ት አዚዛ አቅድም፤ | አልበርታ ካናዳ |
| አቶ መሐመድ አሊ፤ | ሳስካቱን ካናዳ |
| ወ/ት ምንትዋብ እርእያ፤ | አትላንታ |
| አቶ መሠረት አስኒ፤ | ቴክሳስ |
| አቶ ተገኝ ሀይሌ፤ | ፍሎሪዳ |
| አቶ ብርሃኑ ነጋሽ፤ | ፈረንሳይ |
| አቶ ታደሰ ዘሪሁን፤ | ስዊድን |
| ወ/ት ሀረገወይን ምሥጋኩ፤ | ዋሽንተን |
| አቶ ፋሲል ይርጉ፤ | ቺካጎ |
| አቶ በድሩ ሱልጣን | ቴክሳስ |

## *ማስታወቂያዎች*

የሚቀጥለው እትም (3ኛ ዓመት ቁጥር 7) መስከረም ፳፪ ዓ.ም ላይ ስለሚወጣ ጽሑፎች ያሏችሁ በቅድሚያ እንድትልኩልን እናሳስባለን።

* * *

በመጽሔቱ ውስጥ ማስታወቂያዎችን ማስገባት ስለወሰንን ማስታወቂያዎች ያሏችሁ ሁሉ በቅድሚያ እንድትልኩልን።

| | |
|---|---|
| ሙሉ ገፅ | $ 160 |
| ግማሽ ገፅ | $ 80 |
| ሩብ ገፅ | $ 40 |

## *ማስታወቂያዎች*

ይህ እትም ዘግይቶ በመውጣቱ ምክንያት አንዳንድ ቀደም ብለው የተላኩ ጽሑፎች ላይ የተመዘገቡ ሀቆች አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ላይጣጣሙ ስለሚችሉ አንባቢዎች ይህን እያስታወሱ እንዲያነቡ እናስገነዝባለን።

* ***** ልዩ ምስጋና******

የዳሽን ኢንጂኔሪንግ ኩባንያ ለዚህ ቁጥር ያደረገውን ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማድነቅ ልዩ ምስጋና እናቀርባለን።

## ሰምና ፡ ወርቅ ፡

## ለአንባብያን ፡ አጭር ፡ ማስታወሻ ፡

<u>ሰምና ወርቅ ድርጅት</u> የመጽሔት አዘጋጅ ድርጅት ነው ። ይህ ድርጅት ለትርፍ የሚሠራ ድርጅት አይደለም ። በሽያጭም ሆነ በስጦታ የሚያገኘውን ማንኛውንም ገቢ በቀጥታ ድርጅቱ ለመጽሔቱ ማስፋፊያ ያውለዋል ። የመጽሔቱ አዘጋጆች ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ያለክፍያ ያገለግላሉ ። ወደፊት መጽሔቱ መክፈል የሚችልበት አቅም ሲደርስ አስፈላጊ ለሆኑ አባላት ተገቢውን ወጪ ያደርጋል ።

በመጽሔቱ ለሚታተሙ ጽሑፎች ድርጅቱ የተወሰነ ኃላፊነት ቢኖረውም ፣ የጽሑፎችን ይዘት አስመልክቶ የሚነሳ ጥያቄ የሚመለሰው በጽሑፉ ደራሲ ነው ።

## ለደራሲያን ፡ አጭር ፡ ማስታወሻ ፡

መጽሔቱ ታትሞ እንዲወጣ ጽሑፍ የሚልኩ ደራስያን የሚከተለውን መመሪያ እንዲገነዘቡ እንጠይቃለን ።

ሀ/ ለመጽሔቱ የሚላክ ማንኛውም ጽሑፍ ለማንበብ የማያስቸግር ፣ ግልጽና ሥርዝ ድልዝ ያልበዛበት መሆን አለበት ።

ለ/ ለመጽሔቱ የሚላክ ጽሑፍ ዋናው ወይንም ግልባጩ ከደራሲው ጋር ቀሪ እንዲሆን ያስፈልጋል ።

ሐ/ ለመጽሔቱ የሚላኩ ጽሑፎች ለመታተም ቅድሚያ የሚሠጣቸው ኢትዮጵያን በሚመለከት ማንኛውም ነጥብ ላይ አዲስ ሀሳብ ፣ አዲስ ዜና ፣ አዲስ ትንተና ወይንም አዲስ መረጃ የያዙ እንደሆነ ነው ።

መ/ ደራሲዎች ጽሑፎቻቸው በሠነድና በማስረጃ የተደገፉ ፣ የምርምርና ጥናት ጽሑፎች እንዲሆኑ ወይንም የምርምርን ባህል የሚያዳብሩ እንዲሆኑ ጥረት እንዲ ያደርጉ ይጠየቃሉ ።

ሠ/ ደራሲዎች የሚልኩት ጽሑፍ ከሺገጽ ያልበለጠ ቢሆን ይመረጣል ። ከፍተኛ ጥናት የሚያደርጉ ደራሲዎች ሥራቸውን በልዩ መልክ ማውጣት እንዲቻል አስቀድመው ከአዘጋጁው ክፍል ጋር በደብዳቤ ግንኙነት ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

ረ/ <u>የሰምና ፡ ወርቅ ፡</u> አዘጋጅ ክፍል ደራሲያን የላኩት ጽሑፍ ላይ አርማትንና የማስተካከል ተግባር ሲፈጸም ደራሲዎች ጽሑፋቸውን እንዲመለከቱት የማድረግ ኀላፊነት አለበት ። ደራሲያን ጽሑፋቸውን ባስቸኳይ መመለስ ይኖርባቸዋል ።

ሰ/ ደራሲያን ያልተለመዱ ቃላትን ማስተዋወቅ በሚፈልጉበት ጊዜ በቃላቱ ሥር መሥመር እንዲያስቀምጡና የቃላቱን ፍቺ በግርጌ ማስታወሻ ወይም በጐኑ እንዲገልጹ ይጠየቃሉ ።

ሸ/ ደራሲዎች ለሚያቀርቡት መረጃ ፣ ዜናና ለጽሑፎቻቸው ይዘት ተጠያቂዎች ናቸው ።

ቀ/ የመጽሔቱ ዕድሜ በሽያጭ ገቢና በሥጦታ(በልግሥና) በሚገኘው ገቢ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ አንባብያን የተቻላቸውን ያህል ድጋፍ እንዲያደርጉ ይጠበቃሉ ።